የቅናት በቀል
ገጽ 11

ለውጥ ከራስ ይጀምራል!
ገጽ 14

የአገልጋይነት ባሕል ለመፍጠር
ገጽ 15


አዲስ ዘመን
83ኛ ዓመት ቁጥር 362 ጳጉሜን 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!











ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እና ፕሬዚዳንት ሺ ጂፒንግ

# የጋራ ተጠቃሚነትን መርህ ያደረገው የቻይና- አፍሪካ ፎረም

**ልጃለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

የቻይና-አፍሪካ ትብብር ፎረም (FOCAC) በቻይናና በአፍሪካ ሀገራት መካከል ውይይት፣ ትብብርና የኢኮኖሚ አጋርነት እንዲያድግ የሚያስችል ቁልፍ መድረክ ነው።

ቻይና የአፍሪካ ትልቁ የንግድ አጋር ስትሆን፣ በየዓመቱ ከአፍሪካ ጋር የምታካሂደው የንግድ ልውውጥ ከ200 ቢሊዮን ዶላር ማለፉ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ፎረሙ የንግድ ሚዛንን ማስጠበቅ፣ በኢንዱስትሪ መስፋፋትና ለአፍሪካ ምርቶች የገበያ መዳረሻዎችን ማመቻቸት ላይ ትኩረቱን እንደሚያደርግም ይነገራል፡፡

የትብብር ትስስሩ የበይ ተመልካች የሌለበት ስለመሆኑም በተለያዩ ጊዜያት አስተያየታቸውን የሚሰጡ

**የጋራ ተጠቃሚነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


ፎቶ ገበዘ ገብሬ

# "ሀገርን በድል ማስቀጠል የተቻለበት ሂደት ለቀጣይ የእድገት ጉዟችን እንደወረት የሚወሰድ ነው"

- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- ሀገርን በድል ማስቀጠል የተቻለበት ሂደት ጠቃሚ ተሞክሮዎች የተገኙበትና ለቀጣይ የእድገት ጉዞ እንደወረት የሚወሰድ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ገለፁ።

የመሻገር ቀን "የመሻገር ጥሪቶች፤ የአዲስ ብርሃን ወረቶች" በሚል መሪ ሃሳብ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ትናንት በሳይንስ ሙዚየም ተከብሯል።

**"ሀገርን በድል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# የትምህርት ስብራቱ ወጌሻ

**አማን ረሺድ**

**ዜና ትንታኔ**

ትምህርት ዓለም አሁን ለደረሰበት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ እድገት መሠረት ብቻ ሳይሆን የቀጣዩ የሰው ልጅ ህልውና ዕጣ ፈንታንም የሚወስን ነው። በኢትዮጵያ በየዘመኑ የነበሩ መንግሥታት ዘመናዊ ትምህርት ለእድገትና ብልጽግና ወሳኝ መሆኑን በመረዳት የየራሳቸውን የትምህርት ፖሊሲ በመቅረጽ ትምህርትን ሲተገብሩ ቆይተዋል።

በየዘመናቱ የነበሩ የዘርፉ ተግዳሮቶችን ለመፍታትም የትምህርት ሚኒስቴር ባለፉት ስድስት ዓመታት የለውጥ (ሪፎርም)

**የትምህርት ስብራቱ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል**

# የአምራች ኢንዱስትሪው ሪፎርም ውጤታማነት

ገጽ 4



# በአዲስ አበባ ለአፍሪካ ከተሞች ተምሳሌት ሊሆኑ የሚችሉ ውጤታማ ሥራዎች ተከናውነዋል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ ለአፍሪካ ከተሞች ተምሳሌት ሊሆኑ የሚችሉ ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸውን የከተማ አስተዳደሩ ምክትል ከንቲባና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ ገለጹ፡፡

ጳጉሜ 1 የመሻገር ቀን የመሻገር ጥሪቶች የአዲስ ብርሃን ወረቶች በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ደረጃ ትናንት ተከብሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ በመርሃግብሩ ላይ ተገኝተው እንደገለጹት፤ 2016 ዓ.ም ለአፍሪካ ከተሞች ተምሳሌት ሊሆኑ የሚችሉ ውጤታማ ሥራዎች የተከናወነበት ዓመት ነው፡፡

አዲስ አበባ ለነገ ተስፋ የሚሰጡ ፕሮጀክቶችን በመከወን በሀገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ተምሳሌት በመሆን ዕቅዷን ያሳካች ከተማ ናት ያሉት አቶ ጃንጥራር፣ በአፍሪካ የመጀመሪያውን የከተሞች ፎረም ማዘጋጀቷ ልዩ ያደርጋታል ብለዋል፡፡

በቱሪዝም፣ በግብርና፣ በቴክኖሎጂ፣ ኢንዱስትሪና በሀገር ደረጃ በሚከወኑ ትልልቅ ፕሮጀክቶች የተገኙ ስኬቶች የመሻገር ምልክት የታየባቸው መሆኑን ገልጸው እራሳችን እየተለወጥን የሀገራችንን ልማት ማፋጠን ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ በብዝሃነት የተዋበች በአብሮነት የደመቀች በሚዳሰሱና በማይዳሰሱ ቅርሶች የተዋበች መሆኑዋን ጠቅሰው በራሷ ዘመን የምትቆጥር ነጻነቷን የጠበቀች በልዩ ልዩ መልኮች የተወከለች ቀለመ ብዙ እናት መሆኑዋን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ውበቷን ሳትበርዝ እያደሰችና እያስዋበች ከዘመን ዘመን በውድ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ መኖሯን ገልጸው የአባቶቻችንን አደራ ጠብቀን የራሳችንን ዐሻራ ጨምረን ለመጪው ትውልድ ማሻገር አለብን ብለዋል።

ኢትዮጵያን ከዓለም ሀገራት ልዩ ከሚያደርጓት እሴቶች መካከል አንዱ የ13 ወር ጸጋ ባለቤት መሆኑዋ ነው ያሉት አቶ ጃንጥራር ጳጉሜን ከከባዱ የክረምት ወራት ወደ ብርሃናማው የመስከረም ወር መሸጋገሪያ ድልድል ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በ13 ወራት ጸጋ የተሸለመች ውብ ሙሽራና የራሷ ዘመን መስፈሪያ ያላት ባለጸጋ እናት ናት ብለዋል።

እንደሀገር በግብርና፣ ደን ልማት፣ ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ዘርፍን ጨምሮ ትልልቅ ፕሮጀክቶች በማጠናቀቅ ወደ ተሻለ ደረጃ መሸጋገር እንደተቻለ ጠቅሰው እንደከተማ በከተማ ግብርና፣ በቱሪዝም፣ የደን ልማት ሥራን ባህል በማድረግ ሽግግር መፈጠሩን ተናግረዋል።

በአሮጌው ዓመት ከተሠሩ ሥራዎችና የተገኙ ስኬቶችን ይበልጥ በማጎልበት አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስ መቀበል እንዲያስፈልግ በመግለጽ፣ ከአስተሳሰብ እንከኖች በመሻገር ባለራዕይ መሆንና በአዲሱ ዓመት አዲስ ሰው መሆን እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

ከአሮጌው ዓመትና ማንነት ወደ አዲሱ ዓመትና ማንነት መሸጋገር አስፈላጊ እንደሆነ የገለጹት ኃላፊዋ፣ የንግግር ብቻ ሳይሆን የተግባር ሰዎች በመሆን ዘመናትን በደስታና በስኬት መሻገር እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

በዕለቱ ባዛርና ኤግዚቢሽንም በመስቀል አደባባይ የተከፈተ ሲሆን በመርሃግብሩ ላይ የከተማ አስተዳደሩ የካቢኔ አባላት፣ አምራቾችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችም ተገኝተዋል፡፡

# ጠንካራ የፍትህ አሠራር - የሀገር ህልውና መጠበቂያ

**ዘሳለም ግዛው**

የፍትህ ዘርፉ ጠንካራ ሆኖ የሀገር ገጽታን መገንባት፣ አስተማማኝ፣ ነጻ እና ገለልተኛ ዳኝነት አለ ወደሚያስብል ደረጃ መድረስ ይገባዋል፡፡ ለአንድ ሀገር ሕልውና በፍትህ ሥርዓትና በተቋማቱ ላይ ጠንካራ አመኔታ ያስፈልጋል፡፡




በርካታ የልማት ሥራዎች እየተሠሩ፣ ኢኮኖሚውም እያደገ በሚገኝበት በዚህ ወቅት ሂደቱን የሚያግዝ የፍትህ ሥርዓት መገንባት እንደሚገባ፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታም ሆነ ለአንድ ሀገር ትልቁ መለኪያ የፍትህ ሥርዓቱ ጥንካሬ መሆኑንም የዘርፉ ባለሙያዎች ያነሳሉ።

ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ወጪ ቆጣቢ የፍትህ አገልግሎት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በለውጡ ማግስት የተጀመሩ ሥራዎች የሚበረታቱ ናቸው፡፡ በተለይ አፋኝ የነበሩ የሕግ ጉዳዮችን በማሻሻል የተሰሩ የሪፎርም ሥራዎች ተጠቃሽ መሆናቸውን ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል እና የፌዴራል ሕግና ፍትህ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ዘካርያስ ኤርኮላ፤ በፍትህ ዘርፉ በተለይም የሕጎች ማሻሻያ መደረጉ፣ ዳኞች በነጻነት የሚሠሩበት ሁኔታ መፍጠሩን በበጎነት ያነሳሉ፡፡

የፍትህ ዘርፉን አስረው ይዘዋል፣ አስቸጋሪ ናቸው፣ ሠብዓዊ መብት ይጥሳሉ የተባሉ ሕጎች በስፋት መሻሻላቸው ለዘርፉ ትልቁ ለውጥ መሆኑንም ያነሳሉ፡፡ ሌሎችም በ1960ዎቹ የወጡ እንደ ንግድ ሕግ ያሉትም እንደገና ተሻሽለዋል ብለዋል፡፡

አቶ ዘካርያስ፤ የዳኝነት አካሉ ከየትኛውም አካል ነጻ ሆኖ በነጻነት መሥራት እንዲችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የዳኝነት ነጻነት፣ ተጠያቂነት እና ገለልተኛነት እንዲጠበቅ ተደርጓል ሲሉም ይጠቁማሉ።

በፍርድ ቤቶችም ሆነ በሌሎቹ የፍትህ አካላት የአሠራር ሥርዓቶችን የማሻሻል፣ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ሁኔታዎች በይበልጥ እየተሠራባቸው ይገኛሉም ይላሉ፡፡

“ነጻ እና ገለልተኛ ዳኝነት መኖር ወሳኝ ነው፤ ዐቃቤ ሕግ፣ ፖሊስ፣ ማረሚያ ቤቶች በተለይ ለሕግ ልዕልና እና ለሕግ የበላይነት ሊቆሙ ይገባቸዋል። የሕግ የበላይነት የተከበረባት ሀገር መፈጠር ይኖርበታል” ሲሉም አቶ ዘካርያስ ያነሳሉ፡፡

ሆኖም በፍትህ ዘርፉ አሁንም የተለያዩ የፍትህ ሥርዓቱ የሚታማባቸው ችግሮች አሉ ሲሉ አቶ ዘካርያስ ያነሳሉ፤ የተገልጋዮች መጉላላት፣ የሕጎች አተረጓጎም ችግር፣ የሙስና ችግር አለ፡፡ አንዳንድ ዳኞች ላይ ከራሳቸውም ሆነ በሌሎች ተጽእኖ ገለልተኛ ያለመሆን ችግር ይስተዋላል፡፡ እነዚህን ውስንነቶች በሂደት የሚስተካከሉ መሆናቸውን ያነሳሉ፡፡

የፌዴራል ሕግና ፍትህ ኢንስቲትዩት በዋናነት የተቋቋመው የፍትህ ሥርዓቱን በሥልጠና፣ በጥናት እና በምርምር ለማገዝ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ዘካርያስ፣ በተለይ በዳኝነት አካሉ የአቅም ችግር ነው ወይስ የሥነምግባር የሚሉትን ችግሮችን ለይቶ በማውጣት በኩል ባግባቡ ሊሠራበት እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡

የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚያያቸው የዲሲፕሊን እና ሌሎች ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት በቁጥጥር እና በክትትል መደገፍ አለባቸው ሲሉም አሳስበዋል፡፡

በተወሰኑ ዐቃቤ ሕጎች የሚነሱ ብዙ የሚያስተቹ ነገሮች አሉና ሊለይ ይገባል፡፡ የሠሯቸውን ፋይሎችን በመመልከት ጭምር ችግሩ መፈታት አለበት፡፡ የባሰ ችግር ያለባቸውንም በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው በተካተተው መሠረት የማጥራት ሥራዎች መሠራት ይገባቸዋል ሲሉም ነው የሚያሳስቡት፡፡

በ+ዘርፉ የማጥራት ሥራ መሠራቱ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በጥብቅ ዲሲፕሊን እየተመሩ የሚሠሩ ንጹህ ዳኞች ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጣም በርካታ ችግሮች ውስጥ እየገቡ የሚሠሩ ሊኖሩ ይችላሉና መጥራት አለባቸው፡፡ ተግባሩ በሂደት መሠራት ያለበት፣ የሕግ ማዕቀፍም የሚፈልግ ነው ባይ ናቸው፡፡

“የማስቻያ ቦታዎችን ጨምሮ በዘርፉ አስፈላጊ ግብዓቶችና መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ በጀትም መድቦ እየሠራ ይገኛል፡፡ በስፋትም መሠራት፤ አለበት ለምሳሌ አንዳንድ ቦታ የማስቻያ ሥፍራዎች በኪራይ የሚጠቀሙበት ሁኔታ አለ” ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

ፍርድ ቤቶች የራሳቸው የሆነ መሠረተ ልማት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ህንጻ መገንባት አለባቸው፡፡ የተሻለ የሥራ አካባቢም መኖር አለበት፡፡ እነዚህ ችግሮች ወደ ክልል ሲኬድ በጣም የሰፉ ናቸው፡፡ በመሆኑም እንደሁኔታው ቅድሚያ እየሰጡ፣ ያለውን ሀብት ባግባቡ እየተጠቀሙ መፍታት ይገባል፡፡

ቴክኖሎጂን በመጠቀም ረገድ በፌዴራል ደረጃ የተሻለ እንቅስቃሴ አለ፡፡ በክልሎችም ሊተገበር ይገባል፡፡ የፍትህ ዘርፉ ጠንካራ ሲሆን ነው የሀገር ውስጥ፣ የውጭ ኢንቨስትመንቱም የሚንቀሳቀሰው፡፡ እውቀቱም ሀብቱም ሥራ ላይ መዋል የሚችለው ሰላም ሲሰፍንና ጸጥታ ሲኖር፣ ደህንነት ሲሰማ ነው ብለዋል፡፡

ይህ ሊረጋገጥ የሚችለው የፍትህ ዘርፉ ላይ ትኩረት ተሠጥቶት ሲሠራ ነው፡፡ ለሕግ መቅረብ ያለባቸው ወንጀል የሚሠሩ፣ ለልማትም ለሥራም እንቅፋት የሚሆኑ ሰዎች ለሕግ ሲቀርቡ፣ ሲቀጡ፣ የሕግ የበላይነት ሲኖር ነው ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ መግባት የሚቻለው፡፡ ካለዚያ ስጋት ውስጥ ይከታል ሲሉም አክለዋል፡፡

ሀገራዊ ሪፎርሙ ከመንግሥት ፖሊሲ አንጻር በመሠረታዊነት የዜጎችን የፍትህ ጥያቄ መመለስ አለበት፡፡ መንግሥት በሀገር ደረጃ ሰላም እንዲሰፍን፣ ብልጽግና እንዲመጣ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም የፍትህ ዘርፉ ተግባር ሰው የበለጠ ወደ ሥራ የሚገባበት፣ በነጻነት መሥራት የሚችልበት ምቹ የሥራ ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል ብለዋል፡፡

# በመዲናዋ በ137 ቦታዎች የበዓል ዋዜማ ድረስ የሚቆይ ባዛር ተከፈተ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ለዘመን መለወጫ በዓል ፍጆታ የሚሆኑ ምርቶችን በቀላሉ ለሸማች ማህበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ የበዓል ዋዜማ ድረስ የሚቆይ ባዛር በ137 ቦታዎች ላይ መከፈቱን የአዲስ አበባ ኀብረት ሥራ ኮሚሽን ገለጸ።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ልዕልቲ ግደይ ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ፤ ከባዛሮቹ በተጨማሪ በአንድ ሺህ 500 የኀብረት ሥራ ማህበራት ሱቆች የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እንዲሁም የፍጆታ እቃዎች በስፋት መኖራቸውንም ገልጸዋል።

“በዘመን መለወጫ በዓል የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር ከሶስት ወር በፊት የዝግጅት ሥራ ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህም በከተማዋ ባሉት 11 ዩኒየኖች አማካኝነት 33 የገበያ ትስስር ተፈጥሯል” ያሉት ኮሚሽነሯ፤ ከክልል አምራቾች፣ ከኢንዱስትሪ ባለቤቶች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜም በመዲናዋ ለበዓል ፍጆታ የሚሆኑ ምርቶችን ለሸማቹ ተደራሽ ለማድረግ በ137 ቦታዎች ባዛር ተከፍቷል። ይህም የምርት አቅርቦቱን በማሻሻል ፍትሐዊ ስርጭት እንዲኖር ያደርጋል ያሉት ኮሚሽነር ልዕልቲ፤ ኀብረተሰቡ 239 በሚሆኑ ሉካንዳ ቤቶች የበሬ ስጋ ማግኘት እንደሚችልም ገልጸዋል።

በባዛሮቹ የአትክልት፣ የሰብል፣ የእንስሳት ተዋፅኦ እንዲሁም የፋብሪካ ምርቶች በብዛት በመቅረብ ላይ እንደሚገኙ ኢፕድ ባዛሮቹን ቦታው ድረስ ሄዶ መመልከት ችሏል።

በገበያዎቹ ቀይ ሽንኩርት ከ85-88 ብር ፣ ቲማቲም 55 ብር ፣ ፈሳሽ ዘይት ባለ 5 ሊትር ከ1060-1080 ብር፣ እንቁላል 10 ብር ፣ ማር 500 ብር ፣ የጠጅ ማር 450 ብር፣ ቂቤ በኪሎ ከ650-700 ብር እንዲሁም ዱቄት በኪሎ 88 ብር በመሸጥ ላይ ይገኛል።

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የኀብረት ሥራ ዩኒየን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮሐንስ በላይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ለበዓል ፍጆታ የሚውሉ የተለያዩ ምርቶችን በብዛት የማቅረብ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የዋጋ ጭማሪ እና የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይፈጠር በቂ ምርት ማቅረብ ላይ በትኩረት እየሠሩ መሆኑን የገለጹት አቶ ዮሐንስ፤ ዩኒየኑ ለማህበራቱ 100 ኪሎ ጤፍ ከዘጠኝ ሺህ 450 እስከ 11 ሺህ 200 ድረስ እያቀረበ መሆኑን ገልጸዋል።

የስንዴ ዱቄት በኪሎ ከ83 ብር እስከ 85 ብር እያከፋፈል ሲሆን የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና ሌሎች መሠረታዊ ፍጆታዎች በስፋት ተረክቦ ለማህበራት ሱቆች ማሰራጨቱን ተናግረዋል።

# የአፍሪካ ከተሞች ገጽታ እና የቤት ሥራዎቻቸው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

**ዜና ሀተታ**

የከተሞች እድገትና መስፋፋት የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑ እሙን ነው። "ዘላቂ የከተሞች ልማት ለአፍሪካ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ 2063" በሚል መሪ ቃል በዓድዋ ድል መታሰቢያ እየተካሄደ በሚገኘው የመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም የተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች ተሞክሮአቸውን አቅርበዋል።

በዚህም ከተሞች ውጤታማ በሆነ መንገድ ከተመሩ ትልቅ የልማት አቅም፣ የኢንዱስትሪና የሥራ ዕድል ፈጠራ ማዕከላት እንደሚሆኑ የተጠቆመ ሲሆን፤ ይሁን እንጂ ዛሬ ላይ ከተሞች በቂ ያልሆነ መሠረተ ልማት፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ ሥራ አጥነትና የአካባቢ ብክለትን ጨምሮ በርካታ ችግሮችን እያስተናገዱ መሆኑ ተነስቷል።

የኢትዮጵያ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ እንደሚናገሩት፤ በአፍሪካ ፈጣን የከተሞች እድገት እየተስተዋለ ይገኛል። በዚህም በአመት በአፍሪካ 3 ነጥብ 5 በመቶ እንዲሁም በኢትዮጵያ 5 ነጥብ 4 በመቶ የከተሞች እድገት ይታያል።

እድገቱ የከተማና የገጠር ምጥጥንን የሚቀይር ማሳያ በመሆኑ አፍሪካ እንደአህጉር በርካታ የከተማነት አጀንዳዎች አሏት ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከተሞች ሲስፋፉ በቂ የመሠረተ ልማት መስፋፋት እጅጉን አስፈላጊ ነው። ከተሞቻችንን ለማሻገር ለዜጎች ምቹ መኖሪያ እንዲሆኑ ለማድረግ በጋራ መሥራት አለብን ይላሉ።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ የከትመት ምጣኔ እድገት የአንድን ሀገር የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሀብት፣ የማህበራዊ፣ የቴክኖሎጂና ሌሎች ጉዳዮች እድገትን የሚያመላክት ነው። ይህም በከተማ የሚኖረው ሕዝብ እያደገ የሚሄድበትና ለሀገር ውስጥ አመታዊ ምርት(ጂዲፒ) እንዲሁም አጠቃላይ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያደርግበትን እድል ይፈጥራል።

በዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት የከተሞች መስፋፋት ለኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ሙሉ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በሚያስችል መልኩ ከተሞችን ለመምራት የሚያስችሉ ርምጃዎችን እየወሰደ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከተሞችን ምቹ የመኖሪያ፣ የመንቀሳቀሻ፣ የምርታማነት አካባቢ በማድረግ የምጣኔ ሀብት ማዕከል ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ናቸው ብለዋል።



ፎቶ በረሁን ታደሰ

የደቡብ አፍሪካ የሰፈራ ምክትል ሚኒስቴር ታንዲ ማሀምባህላላ እንደሚሉት፤ አፍሪካ ፈጣን የከተሞች እድገት የምታስተናግድ አህጉር ናት። በዚህም ወደከተሞች የሚደረገው የዜጎች ፍልሰት ከተሞች እራሳቸውን በመሠረተ ልማት ግንባታ ሊያበቁ እንደሚገባ አመላካች ነው።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ የከተማነት ምጣኔ ማደጉ የከተሞችን ሽግግር ያፋጥናል። እንዲሁም የባህልና የእውቀት ልውውጡን በማሳለጥ ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ሥራ አጥነትን፣ ድህነትንና የአካባቢ መራቆትን የሚያስከትል በመሆኑ ለዜጎች መኖሪያ የሚሆኑ ምቹ ከተማዎችን ለመገንባት የተቀናጀ ሥራ ያስፈልጋል። ግብርናን በማዘመንና ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚን በመገንባት በከተሞች አካባቢ ያለውን የሥራ እድል ፈጠራ ማጠናከር አስፈላጊ እንደሆነና ደቡብ አፍሪካም በዚህ ረገድ የተዋጣለት ተግባር እየሠራች መሆኑን ሚኒስትሯ ይገልፃሉ።

የግብፅ የቤቶች አገልግሎት ሚኒስቴር አምባሳደር ሀሰን ኢልላኢቲ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚህ አይነት የተሳካ መድረክ በማዘጋጀቱ አመስግነው፤ የግብፅ መንግሥት በከተሞች ልማት የሚደረገውን የትኛውንም አይነት ፕሮጀክት ለመደገፍ ዝግጁ መሆኑን ነው የገለፁት።

ግብጽ በከተሞች ልማት እያከናወነች ባለው ተግባር በርካታ ለውጦችን አስመዝግባለች። የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን በመተግበር ለነዋሪዎች ተመጣጣኝ የቤት አቅርቦት፣ በዘላቂ የአየር ንብረት ለውጥ ላይ በመሥራትና አካታች የዲጂታላይዜሽን አማራጮችን በመተግበር ከተሞች ፈጣን እድገት እንዲያስመዘግቡ ማድረግ መቻሉን አምባሳደር ሀሰን ይጠቁማሉ።

በዚህም ግብፅ ያስመዘገበችውን ለውጦች ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት በማካፈልና በመቀበል የአህጉሪቱን የጋራ እድገት ለማፋጠን ዝግጁ ናት የሚሉት አምባሳደር ሀሰን፤ እንዲሁም የግብፅ መንግሥት በአጀንዳ 2063 የተቀመጡ እሳቤዎችን ለማሳካት የሚጠበቅበትን ለማድረግ ከመቼውም በበለጠ ዝግጁ መሆኑን ሚኒስትሩ አንስተዋል።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኬንያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ግሬስ አካራ እንደሚናገሩት፤ ከተሜነት በአፍሪካ ሁሉንም የኢኮኖሚ ገፅታዎች እየቀረጸ ነው። ይህ ፎረም የአፍሪካ ከተሞችን አሁናዊ ገጽታ ከማስተጋባት ባለፈ በአጀንዳ 2063 የተቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት ያለንን ቁርጠኝነት የምናረጋግጥበት እድል የሚሰጥ ነው።

አምባሳደሯ አክለውም በአሁኑ ወቅት ከተሞች 55 በመቶ ለሚሆነው የዓለም ሕዝብ መኖሪያ ሲሆኑ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2050 ይህ ምጣኔ 68 በመቶ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል ነው የሚሉት።

እ.አ.አ በ2019 የኬንያ የከተማ ሕዝብ ብዛት 31 ነጥብ 2 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2030 ወደ 50 በመቶ ያድጋል ተብሎ እንደሚጠበቅ የሚያነሱት አምባሳደር ግሬስ፤ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትና የሕዝብ ቁጥር መጨመር ለከተሞች መስፋፋት በዋናነት ይጠቀሳል ይላሉ።

ይህም በጤና ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶች እና እንደገበያ ማዕከላት ባሉ መሠረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች ላይ ጫና መፍጠር የሚችል ሲሆን ይህም በከተማ በሚኖሩ ዜጎች ላይ ተግዳሮቶችን እንደሚያስከትል አምባሳደሯ ይገልፃሉ።

እንደ አምባሳደር ግሬስ ገለፃ፤ እኩልነት ማጣት፣ የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የከተማ ኢ-መደበኛነት እና የድህነት ደረጃ መጨመር። እነዚህ ተግዳሮቶች እንዳሉ ሆኖ የከተሞች መስፋፋት ውስጣዊ እሴቱ ለመዋቅራዊ ለውጥ፣ ለዕድገት መፋጠን እና ለጋራ ብልጽግና የሚውል አዎንታዊ ኃይል ነው።

የከተሞች መስፋፋት ፈተናዎችን ለመፍታት የኬንያ መንግሥት የተለያዩ ኢንሼቲቮችንና ስትራቴጂዎችን በመተግበር ትልቅ እመርታ አምጥቷል የሚሉት አምባሳደሯ፤ በተጨማሪም አቅም ለሌላቸው ኬንያውያን ጥሩ መኖሪያ ቤቶች እንዲኖራቸው ለማስቻል ለተመጣጣኝ የቤቶች ግንባታ ፕሮግራም ቅድሚያ ተሠጥቷል። በፕሮግራሙ በዓመት 250 ሺህ መኖሪያ ቤቶችን ለማቅረብ እየተሠራ ነው ይላሉ።

የሶማሊያ ሪፐብሊክ የኮንስትራክሽን እና ቤቶች ሚኒስትር አብዱሰላም አብዲ እንደሚገልጹት፤ ይህ ፎረም በአፍሪካ አህጉር ውስጥ አካታችና አሳታፊ የሆነ የዜጎች አሰፋፈር እና መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚደግፍ ነው። ሁሉን አቀፍና ቀጣይነት ያለው የከተማ ልማት ለማምጣት ከከተማ ልማት ጋር የተያያዙ ሃሳቦችን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን መለዋወጥ ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው።

የከተሞች መስፋፋት የባህል፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችና የመሠረተ ልማት መዘመንን በማጠናከር የዜጎችን መሠረታዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ነው የሚሉት ሚኒስትሩ፤ የሶማሊያ ሪፐብሊክ የመኖሪያ ቤት፣ የትምህርት፣ የጤና እና የመሠረተ ልማት አገልግሎት ማስፋፋትን እንደ ቁልፍ የከተማ ልማት ቅድሚያ ተሰጥቶ እየሠራበት መሆኑን ይገልፃሉ።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ፖሊሲዎችን እና ተዛማጅ ሕጎችን መከለስ፣ ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር በአነስተኛ የመኖሪያ መንደሮች ላይ ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ግብዓት ማቅረብ፣ ከተሞችን፣ ማዘጋጃ ቤቶችን በተለያዩ መንገዶች ለማሳደግ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ጫልቱ ሳኒ በተመራው በዚህ መድረክ በተመሳሳይ መልኩ የሶማሊያ፣ የማዳጋስካር፣ ዩጋንዳ፣ ሴኔጋል፣ ዚምባዋብዌ፣ ኬንያና ሌሎችም የአፍሪካ ሀገራት ልምዶቻቸውን ያካፈሉ ሲሆን ይህንኑ ፎረም እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ለዜጎች ምቹና የበለፀገች አፍሪካን ለመፍጠር በጋራ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል።

# የትምህርት ስብራቱ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አጀንዳዎችን ቀርጾ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። ሪፎርም በአንድ ወቅት ተጀምሮ የሚያልቅ ሥራ ሳይሆን ቀጣይነት ያለውና በየጊዜው እየተገመገመ ማስተካከያ የሚያስፈልገው ተግባር መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

በተለይም የትምህርት ተደራሽነትን፣ ፍትሃዊነትን ፣ተገቢነትን እና የጥራት ችግሮችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም ሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽና የተለያዩ ሪፎርሞችን በመተግበር በትምህርት ሥርዓቱ ያጋጠሙ ስብራቶችን ለመጠገን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በተሠራው ሥራ ተስፋ ሰጪ ምልክቶች እየታዩ ቢሆንም የአጠቃላይ ትምህርትን ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነትና ጥራት ማረጋገጥ አሁንም ፈተና መሆኑ ይገለጻል።

ባለፉት ዓመታት በትምህርት ዘርፉ የተከናወኑ የሪፎርም ተግባራትና የተወሰዱ ርምጃዎችን በተመለከተ የዘርፉን ባለሙያዎችን ጠይቀን ሃሳባቸውን ሰጥተውናል፡፡

በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና ሥነ ባህሪ ኮሌጅ ዲን የሆኑት ሳሙኤል አሰፋ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት የትምህርት ጥራት ሳይሆን ለትምህርት ቤቶችና ለተማሪ ብዛት ትኩረት በመሰጠቱ የትምህርት ጥራትን ጎድቶታል፡፡

የትምህርት ዘርፍ ብዙ ሪፎርም የሚያስፈልገው ዘርፍ መሆኑን የሚናገሩት ሳሙኤል (ዶ/ር)፤ ከፈተና ጋር በተገናኘ ከዚህ ቀደም በነበረው የፈተና አሰጣጥ ተማሪዎች በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ ፈተናውን አልፈው ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበትና የሚመረቁበት ሁኔታ እንደነበር ያወሳሉ፡፡

አሁን ላይ ትምህርት ሚኒስቴር በፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱ እንዲሁም በአጠቃላይ በትምህርት ዘርፉ ላይ እየወሰደ ያለው የሪፎርም ሥራ ጥሩ መሆኑን ገልጸው፤ ሪፎርሙ ውጤታማ እንዲሆንና የትምህት ጥራት እንዲረጋገጥ ባለድርሻ አካላት በኃላፊነት መስራት እንደሚገባቸው ይገልጻሉ፡፡

«ኩረጃን ለመከላከል የፈተና አሰጣጡን ማጠናከር ጥሩ ቢሆንም ብቻውን ግን የትምህርት ሥርዓቱን መጠገን አያስችልም» የሚሉት ሳሙኤል(ዶ/ር)፤ ከታች ጀምሮ ትምህርት ቤቶችና የመምህራን አቅም ግንባታ ላይ ጠንካራ የሪፎርም ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፡፡

መንግሥት በትምህርት ዘርፉ እያደረገ ባለው ሪፎርም ከፍተኛ ወጪ ቢያስወጣውም የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ህብረተሰቡን ባሳተፈ መንገድ እስከመጨረሻው መሄድ ከተቻለ ወደፊት ውጤት እንደሚመጣ ይገልጻሉ፡፡

የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ላይ የተደረገው የሪፎርም ትግበራ አስፈላጊ መሆኑን አውስተው፤ በዚህም በሚዘጋጁ መጽሐፍት ሀገር በቀል እውቀቶች እንዲካተቱ፣ ከተማሪው አቅም እና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖር አስችሏል ነው ያሉት፡፡ የተጀመረው ሪፎርሙ ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ እንዲሆንም ከፖለቲካዊ ጫናዎች ነጻ መሆን ይኖርበታልም ይላሉ፡፡

የዩኒቨርሲቲዎች ራስገዝነትን በተመለከተ በሌሎች ሀገራት የሚገኙ የዩኒቨርሲቲዎች ራስገዝ መሆናቸውን አውስተው፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ራስ ገዝ እንዲሆኑ መደረጉ የኢኮኖሚያዊ ነጻነት ብቻ ሳይሆን አካዳሚያዊ ነጻነት እንዲኖራቸው ስለሚረዳ የሚበረታታ ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስገዝ መሆኑን አውስተው፤ ነገር ግን ነጻነቱን ተከትሎ ገቢ ለማመንጨት ሲባል ክፍያ ላይ ጭማሪ ሊኖር ስለሚችል በተማሪዎች ወይም በተማሪ ቤተሰብ ላይ ጫና እንዳይፈጥር ስጋት እንዳላቸውም ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ኮሚቴ ተዋቅሮ የጥድፊያ ነገር መመልከታቸውን ጠቁመው ፤መሰል አካሄዶች ታርመው በጥንቃቄና በጊዜ ሂደት ወደ ራስ ገዝ አሠራር መግባት እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ር) ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከልም ተቋማዊ ነጻነት፤ የሀብት ነጻነትና አካዳሚያዊ ነጻነት እንደሚገኙበት ይጠቅሳሉ፡፡

እንደ ሳሙኤል (ዶ/ር) ገለጻ፤ ዩኒቨርሲቲዎች ራስገዝ ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ሀብት እንደሚተዳደሩና ለዚህም ሁሉም ተማሪዎች ለትምህርት የሚያስፈልገውን ወጪ ከፍለው የሚማሩ ስለሆነ የኢኮኖሚ አቅም የሌላቸው ተማሪዎች በእነዚህ ራስገዝ ዩኒቨርሲቲዎች አይማሩም በሚል የሚነሳ ሃሳብ ስህተት ነው ብለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ራስገዝ ይሆናሉ ማለት ሥርዓት አልበኛ ይሆናሉ ማለት አይደለም ያሉት ሳሙኤል (ዶ/ር)፤ ሕግና ሥርዓትን ተከትለው በነጻነት ይሠራሉ ማለት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲዎች ገቢን በተመለከተ ከላይ እንደተገለጸው ራሳቸው በሚያመነጩትና ከመንግሥት በብሎግራንት (በድጎማ መልክ) በሚያገኙት ሀብት የሚተዳደሩ ይሆናሉ፡፡ መንግሥት በአዋጁ ውስጥ በግልጽ እንዳስቀመጠው ከፍለው መማር ለማይችሉ ብቃትና አቅም ላላቸው ተማሪዎች መንግሥት ይከፍላል ነው ያሉት።

የትምህርት ሚኒስትሩ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) 33ኛውን ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባዔ አስመልክተው እንደተናገሩት፤ የትምህርት ሥርዓቱን በአዲስና በጠንካራ መሠረት ላይ ለመገንባት ባለፉት ዓመታት የሪፎርም ሥራዎች መሬት እንዲይዙ በማድረግ ጉልህ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡

በዋነኝነት ትኩረት ተሰጥቶ የተተገበረው የመምህራን እና የርዕሰ-መምህራንን የሙያ ብቃት ማረጋገጥ ሲሆን ለ52 ሺህ 300 የሁለተኛ ደረጃ መምህራንና ለ8070 ርዕሰ-መምህራን በ28 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥልጠና መሰጠቱን ያነሳሉ፡፡

የሪፎርሙ አካል የሆነው ሀገር-አቀፍ በ12ኛ ክፍል ፈተና በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በወረቀትና በበይነ-መረብ ፈተናን ጎን ለጎን መስጠት ተችሏል፡፡ የመሠረተ ልማት ሥራን እና የኮምፒዩተሮች አቅርቦትን አጠናክሮ በማስቀጠል በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሙሉ በሙሉ በበይነመረብ ለመስጠት እየተሠራ እንደሚገኝ ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም በትምህርት ለትውልድ እንቅስቃሴ ከ27 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ በማሰባሰብ የትምህርት ቤት መሠረተ ልማቶች እንዲሻሻሉ ተደርጓል፡፡ ከደረጃ በታች የሆኑ ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻል የተጀመረውን የትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ በ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

ሌላኛው የሪፎርም አካል ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሲሆን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተቋማዊ ነፃነት ደንብ ጸድቆ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ ተቋማዊ ነፃነትን ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ለማስፋት የሚያስችል ሥራ በቀጣይነት እንደሚተገበር አመላክተዋል፡፡ የትምህርት ፕሮግራሞች ዩኒቨርሲቲዎች ከተሰጣቸው ተልዕኮ እና ልየታ መስክ መሠረት የሚከለሱ ይሆናል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ በሰፊው የሚታዩትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎቻችን ከአካባቢያዊነት የወጡ፣ በእውነት ሀገራዊ የዕውቀት ተቋማት እንዲሆኑ፣ የማስቻል ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር አስተዳደራዊ ሥራዎች ላይ ማሻሻያን ማድረግ ሌላው የለውጡ ተግባር ነው፡፡ ትምህርት ሚኒስቴርን እንደተቋም ለሠራተኞች እና ለተገልጋዮች ውብ፣ ማራኪ፣ ምቹና ደህንነቱ የተረጋገጠ እንዲሆን የተጀመሩ ዓበይት ተግባራት መኖራቸውን አውስተዋል፡፡

የተጀመረው የሪፎርም ሥራ የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ የበለጸገች፣ ፍትሃዊና ሰላም የሰፈነባት፣ ለልማትና እድገት የምትተጋ ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚችል ትውልድ ማፍራትን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ይህን ዓላማ የትምህርት ማህበረሰቡና አጋር ድርጅቶችን በጋራ ሆነን ልናሳካው ይገባል ነው ያሉት፡፡

በሥነ ምግባሩ የታነፀ ብቁና ተመራማሪ ትውልድ ለማፍራት የአጠቃላይ ትምህርትን ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጥራትና ተገቢነት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ደረጃዎች መሠረት በመሆኑ ልዩ ትኩረት በመስጠት ሕፃናትን ሀገር ገንቢ ትውልድ አድርጎ መቅረጽ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

# የአምራች ኢንዱስትሪው ሪፎርም ውጤታማነት

**አዲሱ ገረመው**

መንግሥት በወሰዳቸው የኢኮኖሚ ማሻሻያ የፖሊሲ ርምጃዎች የአምራች ኢንዱስትሪ ዓመታዊ ዕድገት እየጨመረ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚ የሆነው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሪፎርም የአምራች ዘርፉን በምን መልኩ ደገፈው? ውጤቱስ ምንድነው?

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል እንደሚሉት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት በኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪውን ለማሻሻልና በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ በርካታ የሪፎርም ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥም የፖሊሲና አሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዘርፉ ትልቅ ለውጥ የሚያመጡ ውሳኔዎች የተወሰኑትም ባለፉት የለውጥ ዓመታት ውስጥ ነው፡፡ በዚህም የኢንዱስትሪ፣ የግብርና፣ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ሪፎርሞች፣ ለአምራች ዘርፉ አጋዥ የሆኑና ከዲጂታላይዜሽን ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች ተወስነዋል፡፡ ለአምራች ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ያለው ከሎጀስቲክ ጋር ተያይዞ ያለው አገልግሎት የላቀ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የፋይናንስ አቅርቦቱን በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪው የተሻለ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የለውጥ ሥራዎች በብሔራዊ ባንክ በኩል ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡

እነዚህ የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ድጋፎች ዓለም አቀፋዊውንም ሆነ ሀገራዊውን የአምራች ኢንዱስትሪ ማነቆዎች ለመፍታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ መሆናቸውን አቶ መላኩ ገልጸዋል፡፡ ለአምራች ዘርፉ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ችግሮችን በመፍታት ረገድም የማሻሻያ ፖሊሰዎች አዎንታዊ ሚና እንደነበራቸው አንስተዋል፡፡

በዚህ ውስጥም የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ቀደም ሲል ዘጠኝ ያህል ከነበሩት የኢንዱስትሪ ፓርኮች የግል ሴክተሩን ጨምሮ ወደ 22 ማሳደግ የተቻለበት፤ በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪው የመሠረተ ልማት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት የተቻለበት ሁኔታ መፈጠሩን ይጠቅሳሉ፡፡

የሃይል አቅርቦት የአምራች ኢንዱስትሪው ከሚፈልጋቸው ነገሮች አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህ ረገድ ባለፉት ስድስት የለውጥ ዓመታት መሠረታዊ የሚባሉ ሥራዎች መከናወናቸውን ያብራራሉ፡፡ በዚህም ቀደም ሲል እስከ ፈረቃ ድረስ ደርሶ የነበረው የሃይል አቅርቦት አሁን በተሻለ ሁኔታ እየተስተካከለ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ በሃይል አቅርቦት ከኢትዮጵያ አልፎ ለጎረቤት ሀገራትም መድረስ እንደተቻለ ነው የገለጹት፡፡

ከመንገድና ከባቡር ጋር ተያይዞ ያለው የሎጀስቲክ ሁኔታ ባለፉት ዓመታት ልዩ ትኩረት ተሠጥቶት እየተሠራ እንዳለ የጠቆሙት አቶ መላኩ፤ ለውጡ ሲጀመር ወደ 167 ሺህ ኪሎ ሜትር የነበረው መንገድ አሁን ቁጥሩ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ በመጪዎቹ አስር ዓመታት ወደ 245 ሺህ ኪሎ ሜትር ለማድረስ ታስቦ እየተሠራ እንዳለም ነው ያመላከቱት፡፡ ይህ አጠቃላይ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ምርታማነት ማሳደግ እንዳስቻለም አብራርተዋል፡፡ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እና የማሻሻያ ፖሊሲዎች በአምራች ኢንዱስትሪዎች ይስተዋሉ የነበሩ ማነቆዎችን ለመቅረፍ ከፍተኛ ሚና ነበራቸውም ብለዋል፡፡

አቶ መላኩ እንደሚሉት፤ “ቀደም ሲል የማምረት አቅማችን ዝቅ ያለ ነበር፡፡ አሁን ላይ ከፍ ብሏል፡፡ በሀገር ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የነበረው የገበያ ድርሻ ዝቅ ያለ ነበር፡፡ ይህንንም ከፍ ለማድረግ ተችሏል” ፤ እነዚህ በሙሉ ተደምረው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዓመታዊ ዕድገቱ ወደ 10 ነጥብ አንድ በመቶ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የግብርና ውጤቶችን የምታመርት ሀገር ናት ያሉት አቶ መላኩ፤ በ2016 ኤክስፖርት ካደረገችው አጠቃላይ ምርት ውስጥ 78 በመቶ የሚሆነው በጥሬው ኤክስፖርት የተደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ይህ እሴት ተጨምሮበት ተቀነባብሮ ለገበያው መቅረብ እንደነበረበት ጠቅሰው፣ ይህንን ለማድረግ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በሙሉ አቅማቸው መሥራት እንዳለባቸውና ተጨማሪ ባለሀብቶች በዚህ ዘርፍ ላይ መሠማራት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ትልልቅ የኢኮኖሚ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን በማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረች እንደምትገኝ ጠቁመዋል፡፡

ላለፉት አስር ዓመታት ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ እንዳለች በመጥቀስ፤ በመጪዎቹ አስር ዓመታትም በፍጥነት ያድጋሉ ተብለው ከሚጠበቁ ሀገራት መካከልም አንዷ ናት ብለዋል፡፡ ይህም በሪፎርም ሥራዎች የመጣ ውጤት እንደሆነ አንስተዋል፡፡ ዓለም ችግር ላይ በነበረችበት፣ እንደ ሀገርም የፖለቲካ አለመረጋጋት በነበረበት ወቅትም ጭምር በርካታ የፖሊሲ፣ የአሠራር ማሻሻያዎች በመሠራታቸው ለኢኮኖሚ የተመቸ ሁኔታ ተፈጥሯል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

መሠረተ ልማትን ለማሟላት የተሠሩ ሥራዎች፣ የኢኮኖሚ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ ርምጃዎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም ነው ያሉት፡፡ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት የተሠሩ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ላይ የተቀመጡትን ሴክተሮች ዘላቂ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አስችሏል ብለዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ እንደሚሉት፤ በተሰሩ የሪፎርም ሥራዎች ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት እያሳዩ ካሉት ሀገራት ኢትዮጵያ አንዷ ሆናለች፡፡ በአፍሪካ አምስተኛው ትልቁ ኢኮኖሚ የኢትዮጵያ ሆኗል፡፡ ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገራት ደግሞ በሶስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ የተመዘገበውም በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም የግል ሴክተሩ ተሳትፎ አነስተኛ ነበር ያሉት አቶ ዘመዴነህ ማሻሻያዎች ከተሠሩ በኋላ የግል ሴክተሩ በኢኮኖሚው ላይ በስፋት መንቀሳቀስ መቻሉን ጠቁመዋል፡፡ ይህም የአምራች ዘርፉ ማጠናከር እንደቻለና በዚህም ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ የኬንያን ኢኮኖሚ ጭምር ሁለት እጥፍ ማደጓን ገልጸዋል፡፡ በቴሌኮም፣ በባንክና መሰል ሴክተሮች የተወሰዱ ማሻሻያዎች ለሀገሪቷ ኢኮኖሚ ማደግና ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ውጤታማነት ከፍተኛ አበርክቶ እንደነበራቸውም አንስተዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሰሃ ይታገሱ (ዶ/ር)፤ በሪፎርም ሥራው በርካታ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መውጣታቸውንና ፖሊሲዎቹ ለባለሀብቶች ትልቅ አንድምታ እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንዳብራሩት፤ ለውጡ ካመጣቸው ጉዳዮች አንዱ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የታዩ ውጤቶች ናቸው፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በሀገሪቱ 13 ፓርኮችን የሚያስተዳድር ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ አንዱ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ነው፡፡ ፓርኮቹ መንግሥት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ያቀረበባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ ቀደም ባለሀብቶች መሬት ይቸግራቸው ነበር፡፡ መሬት ካገኙ በኋላም መብራትና ውሃን ጨምሮ የመሠረተ ልማት ማሟላት ጊዜ ይወስድባቸው ነበር፡፡ ችግሮቹን ለመፍታት በአንድ መስኮት አገልግሎት የአምራች ዘርፉ በመሠረተ ልማቱ ውስጥ ብዙ ችግር ሳያጋጥመው እንዲተገበር ተደርጓል፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነትን ከሚያመላክቱ ሂደቶች ውስጥ አንዱ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ መሆኑን የሚያነሱት ባለሙያዎቹ፤ ኢትዮጵያ በመጪዎቹ ዓመታት ወደ በለፀገና የማይበገር ኢኮኖሚ የምታደርገውን ለውጥ የማስቀጠል አቅሟን በአግባቡ እንድትጠቀም ተግዳሮቶችን የሚቀርፉ ማሻሻያዎችን አጠናክሮ መተግበር እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

# የጋራ ተጠቃሚነትን መርህ ያደረገው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ባለድርሻዎችና የዘርፉ ባለሙያዎች ያረጋግጣሉ፡፡ የባቡር ሐዲዶች፣ ወደቦች እንዲሁም የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ላይ የተሠሩት ሥራዎች የአፍሪካን መገናኛ አውታሮች እና ኢኮኖሚያዊ ውህደትን የቻይና -አፍሪካ የትብብር ፎረም ፍሬዎች ስለመሆናቸውም አጠራጣሪ አይሆንም፡፡

የትብብር ፎረሙ የጋራ ተጠቃሚነትን መርሁ አድርጎ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች የተለያዩ ሥራዎች መሥራት ከተጀመሩ ጥቂት የማይባሉ ዓመታት ነጉደዋል፡፡ ከሁለት ቀናት በፊትም የቻይና የአፍሪካ ሀገራትን የትብብር መስከ ወደ ላቀ ደረጃ የሚያደርስ ዘጠነኛው የቻይና-አፍሪካ የትብብር ፎረም በቻይናዋ መዲና ቤጂንግ ተካሂዷል፡፡

በዚሁ ጊዜ ታዲያ ቻይና ከአጋሮቿ ጋር ያላትን ትብብር ይበልጥ ማሳደግ የሚያስችላት አስር ዘርፎችን ይፋ አድርጋለች። ከነዚህም ንግድ፣ ኢንዱስትሪ ፣ ጤና፣ ግብርና፣ መገናኛ አውታሮች ልማት፣ አረንጓዴ ልማትና ደህንነት ይገኙበታል። በዚሁ ጊዜም ነው ቻይና ለአንድ ሚሊዮን አፍሪካውያን የሥራ እድል እንደምትፈጥር ለአጋሮቿ ቃል የገባችው፡፡

በቤጂንግ በተካሄደው የቻይና አፍሪካ ትብብር ፎረም ላይ የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ ዢን ፒንግ 50 ቢሊዮን ዶላር በመመደብ በብድር እና በድጋፍ መልኩ የሥራ እድልን እንደሚፈጥሩ አስታውቀዋል፡፡ ከአሕጉሪቱ ጋር ያላትን ትስስር ለማጠናከርም 30 የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ትስስሯን እንደምታጠናክርም ገልጸዋል፡፡

እነዚህ የትብብር መስኮችም ኢትዮጵያን ከትብብር ማእቀፉ እንድትጠቀም የሚያስችሉ ስለመሆናቸውም በጉባዔው ላይ የጠሳተፉት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

ከቤጂንጉ የቻይና አፍሪካ የትብብር ፎረም ጎን ለጎን ከቻይናው አቻቸው ፕሬዚዳንት ሺ ጂንፒንግ ጋር የመከሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያና ቻይና በ17 ዘርፎች በትብብር ለመሥራት የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸውን ገልጸዋል፡፡

ስምምነቱ በኢትዮጵያና ቻይና ላለው በሁሉም ሁኔታ ለማይለዋወጠው ስትራቴጂያዊ ትብብር ዓይነተኛ ማሳያ መሆኑን በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በተለይም ምርታማነትን ለማሳካት ሥራዎች በሚዘምኑበት የግብርና ትብብር መንገድ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ልማትና በዲጂታላይዜሽን ሥራዎቻችን ላይ ድጋፍ ስለሚገኝበት ሁኔታ የጋራ ውይይት ማድረጋቸውን አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም ትብብሩ በኢንቨስትመንት፣ በአረንጓዴ ኢኮኖሚ እድገትና አዲስ የኃይል ምንጭ ልማት ላይ ለማጠናከር እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ በበኩላቸው ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላት የትብብር ግንኙነት ሰፊና ጠንካራ መሠረት ያለው መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር በወንድማማችነትና በሰጥቶ መቀበል መርሕ ላይ የተመሠረተ ዘላቂ የትብብር ግንኙነት እንዲኖር የሁልጊዜም ፍላጎቷ እንደሆነ ገልጻለች ያሉት አምባሳደር ታዬ፣ ሁለቱ ሀገራት በጥንት ሥልጣኔ ሰፊ ተሞክሮ እንዲሁም የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ግንኙነት ያላቸው ሀገራት በመሆናቸው ይህንን አጠናክሮ ለማስቀጠልም ሰፊ ምክክር መደረጉን ገልጸዋል፡፡

ከልማት ተነሳሽነት መርህ አንጻርም ከቻይና በርካታ ተሞክሮና የልማት ትብብሮች ለማሳደግም ፍሬያማ ውይይት ተደርጓል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም መሪዎቹ በግብርና፣ በቱሪዝም፣ በማዕድንና በተፈጥሮ ሀብት ልማት በጋራ መሥራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መወያየታቸውን ጠቅሰው ኢትዮጵያ ለእድገቷ እና ለደህንነቷ የባህር በር እንደሚያስፈልጋትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በውይይታቸው ማንሳታቸውን አምባሳደር ታዬ ጠቅሰዋል፡፡

ከቻይና አፍሪካ የትብብር ፎረም ጎን ለጎን የቻይናና የኢትዮጵያ መሪዎች ባደረጉት ውይይት፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ያላት ተሰሚነት፣ በሰላምና ጸጥታ ዙሪያ የምታደርገው አስተዋጽኦ እንዲሁም በኢኮኖሚው ዘርፍ ካላት ከፍተኛ አቅም አኳያ ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ትብብር ለማድረግ ፍላጎት እንዳለት የተገለጸበት ነው ያሉት ደግሞ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ተከትሎ የቻይና ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ግፊት እንደሚያደርጉ የቻይናው ፕሬዚዳንት አስታውቀዋል ያሉት አቶ አህመድ፤ የእዳ ሽግሽግ እንዲደረግ ቻይና የበኩሏን አስተዋጽኦ እንደምታበረክት ከስምምነት መደረሱን ያብራራሉ፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በሁለቱ መሪዎች መካከል የተደረገው ውይይት በተለይ የኢኮኖሚ ትብብር የበለጠ ትኩረት እንዲኖረው፣ በብርና በዩዋን መለዋወጥ እንዲቻል፣ የቻይና የፋይናንስ ተቋማት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው እንዲሠሩ እንዲሁም ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና ተጨማሪ ድጋፍ የሚገኝበት ነው፡፡ በተጨማሪም ቻይና ለኢትዮጵያ ከአራት መቶ ሚሊዮን ዩዋን በላይ ድጋፍ እንደምታደርግ ያረጋገጠችበት ነው፡፡

ኢትዮጵያ የፖሊሲ ነጻነቷን ተጠቅማ የኢኮኖሚ ማሻሻያዋን ተግባራዊ በማድረግ ወደተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መግባቷ እንዲሁም ከዚያ በፊት በተደረጉ የሪፎርም ሥራዎች ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባቷ ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር የኢኮኖሚ ትብብሯን እንድታሳድግ ማድረጉንም ያክላሉ፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ(ዶ/ር) የቻይና አፍሪካ ትብብር ፎረም ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይናገራሉ፡፡

ፎረሙ ቴክኖሎጂ ሊሰጥ የሚችለውን ጠቀሜታ ለማግኘትና የሀገሪቱን አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ትልቅ እድል ይዞ የሚመጣ ነው የሚሉት ዶክተር በለጠ፤ ከአስሩ የትብብር መስኮች የቴክኖሎጂ ዘርፍ አንዱ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የጤና ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ በበኩላቸው ቻይና ሆስፒታሎችን መገንባት፣ የሕክምና ባለሙያዎችን እና የሕክምና መሣሪያዎችን ማቅረብን ጨምሮ በተለያዩ የጤና ዘርፍ ማሻሻያዎች ላይ በትብብር ለመሥራት ስምምነት ተደርጓል ይላሉ፡፡

እንደ ዶክተር መቅደስ ገለጻ፤ በቻይና አፍሪካ የትብብር ፎረም ከተደረጉ አስር ስምምነቶች አንዱ ጤና ዘርፍ ነው ያሉ ሲሆን ለኢትዮጵያም ለወባ በሽታ የሚሆኑ ድጋፎችን ከቻይና እንዲሰጡ ከስምምነት ተደርሷል ብለዋል፡፡ ስምምነቱ በተለይ የጤና ኢንዱስትሪውን ለማሳደግና የተለያዩ የህክምና ግብዓቶች ለማግኘት የሚያስችል እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

# “ሀገርን በድል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ በመርሃግብሩ ላይ፤ “ባለፉት ስድስት ዓመታት እንደ ሀገር በርካታ ውስብስብ ፈተናዎች ቢያጋጥሙንም ፈተናዎቹን በመቋቋም አንፀባራቂ ድል ማስመዝገብ ችለናል። ሪፎርም ሲጀመር አታካች ቢመስልም በሂደት እየፈካ እንደሚሄድ በለውጥ ጉዟችን አረጋግጠናል” ብለዋል።

በተለያዩ የልማት መስኮች የተጀመሩ ሰፋፊ ሥራዎችና የተገኙ ድሎች የመንግሥትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ትክክለኛነት እና የሀገራዊ ብልፅግና ፍኖቱ የኢትዮጵያን ራዕይ እንደሚያሳካ የሚያመላክቱ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

በግብርናው ዘርፍ በስንዴ ልማት የታየው ለውጥ የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የአርሶ አደሩን ሕይወት በማሻሻል፣ የግብርና ኢኮኖሚውን በማጎልበትና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ረገድ ጉልህ ድርሻን አበርክቷል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በውጤቱም ኢትዮጵያ ለረጅም ዓመታት ከምትታወቅበት የስንዴ ልመና ወጥታ የውስጥ ፍላጎትን በማሟላት ስንዴ ለውጭ ገበያ መላክ ወደቻለችበት ታሪካዊ ምዕራፍ መሸጋገሯን አንስተዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የቱሪዝም ዘርፉ የመንግሥት ቀዳሚ የትኩረት መስክ ሆኖ በገበታ ለሸገር፣ በገበታ ለሀገርና በገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ፀጋ የሚመጥኑ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማልማት መቻሉንም አመላክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የአምራች ዘርፉ ተወዳዳሪነት እንዲጠናከር፣ የኤክስፖርት ንግድ እንዲስፋፋ እና ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ በማድረግ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል እንደፈጠረ የገለጹት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በተለያዩ ምክንያቶች ማምረት ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደተሟላ የማምረት እንቅስቃሴ በማስገባትና አቅማቸውን በማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት ረገድ የታየው እመርታዊ ሽግግር ትምህርት የሚወሰድበትና ላስቀመጥነው ሀገራዊ ራዕይ ስንቅ ሆኖ የሚያለግል ነው ብለዋል፡፡

የሁሉም ኢትዮጵያውያን ዐሻራ ያረፈበትና የትውልዱ የቃልኪዳን ሃውልት የሆነው ዓባይ ግድብ በአሠራርና በአመራር ውስንነት ምክንያት ተንገራግጮ ከቆመበት፣ ብልሃት በተመላ ቆራጥ ውሳኔ እና አመራር ሃይል ወደሚያመነጭበት ደረጃ እንዲሸጋገር በማድረግ የሉዓላዊነት መገለጫ እንዲሆን መደረጉንም አመላክተዋል።

ካለፉት ፈታኝ ጉዞዎች ትምህርቶችንና ተሞክሮዎችን በመውሰድ ለቀጣይ ድሎች መታጠቅና ተስፋን መሰነቅ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፣ አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋ የሚሰነቅበት፣ በጎ ጅማሮ የሚበሰርበትና አዲስ ምዕራፍ የሚታወጅበት እንደመሆኑ መጠን መንግሥትና ሕዝብ በታደሰ ቁርጠኝነትና በጠነከረ የትብብር መንፈስ ለላቀ ስኬትና ድል መዘጋጀት ይኖርባቸዋል ነው ያሉት፡፡

በተገኙ ድሎች ሳንኩራራና በሚገጥሙን ፈታናዎች ሳንደናቀፍ በጀመርነው የእድገትና ብልፅግና ሂደት በፍጥነት በመጓዝ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ ይገባናል። ለዚህም ሁሉም ዜጋ ሀገርንና ሕዝብን በቅንነት፣ በታታሪነትና በፍፁም ቁርጠኝነት ማገልገልና ለላቀ ሀገራዊ ድል መዘጋጀት አለበት ሲሉ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት በፈታኝ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ውስጥ ብታልፍም በአማካይ ሰባት ነጥብ ስድስት በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ፣ ከሰሃራ በታች ሦስተኛ ከምስራቅ አፍሪካ ደግሞ አንደኛ የሆነ ግዙፍ ኢኮኖሚ ያላት ሀገር ሆናለች ብለዋል።

በመድረኩ በተለያዩ ዘርፎች በተከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች የተገኙ ውጤቶች፣ ተግዳሮቶችና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን የሚዳስስ ዘጋቢ ፊልም ቀርቧል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት ያጋጠሟትን ፈተናዎች ተሻግራ ዛሬ ላይ እንድትደርስ ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል ለተባሉ በኢነርጂ፣ በግብርና እና በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች አስተዋፅኦ ላበረከቱ የተለያዩ አካላትም እውቅና ተሠጥቷል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የውስጥ ገጾች


## «አገልጋይነት የተለወጠ አስተሳሰብን ይጠይቃል»



- አቶ ሰለሞን ተስፋዬ
የሥራ አመራር ባለሙያ

ገጽ 7-8

wudassie
Diagnostic Center

‹‹ጳጉሜን ለጤና››

ገጽ 9



ሕዝብን የማገልገል ኃላፊነት በውጤትና በስኬት

ገጽ 10

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ማገልገል ክብር የሆነበት ሀገር ለመገንባት

ታምራት ተስፋዬ

የአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትም ሆነ ውድቀት ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። የአገልግሎት አሰጣጥ ተፅዕኖ ሊወሰን የሚችለው ደግሞ በአገልግሎት አሰጣጥ መኖር አለመኖር ሳይሆን በተዋቀረበትና በሚተገበርበት ሂደት ላይ ነው። ውጤታማ አገልግሎት ደግሞ ግልጋሎት ፈላጊው የሚጠይቀውን፣ የሚፈልገውን በትክክል፣ መረዳት፣ አገልግሎቱን በትክክል ማቅረብ ፍላጎቱን ማሟላትና አማራጮችን ማቅረብ ይጠይቃል።

በአሁን ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ የግልም ሆነ መንግሥታዊ አገልግሎት ሰጪና አቅራቢዎች ደንበኞችን ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማስደሰት በተጧጧፈ ውድድር ውስጥ ናቸው። ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሠጡ ተቋማት በውድድሩ እየቀናቸው ሲሆን ከዚህ በተቃራኒ የሚጋዙት ደግሞ ከውድድሩ ተገፍተረው እየወጡ ናቸው።

ብዙዎቹ እንደሚገምቱት አገልጋይነት፣ አገልግሎቶችን ወይም ዕቃዎችን ለተገልጋይ ኅብረተሰብ ማቅረብ ብቻ አይደለም። ይህ ጥበብ አገልግሎት ፈልጐ ወደ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመጣውን ወይም የሚመጣውን ግለሰብ ወይም ድርጅት (ተቋም) የሚፈልገውን ለይቶ በማወቅ የተሟላ መስተንግዶ (አገልግሎት) መስጠትን ያጠቃልላል። ጥራት ያለው አገልግሎት አሰጣጥ የአንድ ሰሞን ሥራ ብቻ አይደለም። ይህ ጥበብ የማያቋርጥ ሂደት ነው።

ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥና የአገልጋይነት ሥነልቦናና አቅም ትልቅ ጥበብን ይጠይቃል። የደንበኞችን ፍላጎት መገንዘብ፣ አመለካከታቸውን መረዳት፣ ለችግራቸው መፍትሔ መስጠት፣ ታማኝነትን መፍጠር፣ ሁልጊዜ ለማገልገል ዝግጁ መሆን የግድ ይላል። ከዚህ ባሻገር የላቀ አገልግሎት መስጠትን፣ ተነጫናጭና ቁጡ ደንበኞችን በትዕግስት ማስተናገድ መቻልን፣ በአገልግሎታችን የሚረኩ ደንበኞች ማፍራትን፣ ቅሬታዎችን በአግባቡ አድምጦ መፍትሔ መፈለግን፣ በደንበኞች ጫማ ሆኖ ነገሮችን መመልከትን፣ ግጭቶችን በአግባቡ መያዝን ይጨምራል። በዚህም ብቻ አይወሰንም። የባለቤትነት ስሜትን መኖርን፣ ኃላፊነት መውሰድን፣ መወነጃጀልን ማስወገድ መቻልና ስሜትን መቆጣጠርን፣ እንዲሁም ጊዜን በአግባቡ መጠቀምና ሌሎች ወሳኝ ጥበቦችን ይጠይቃል።

አንዳንድ ተቋማት ብሎም ሀገራት በሁሉ ረገድ ሲወድቁ የማያውቁትም በዚህ ደረጃ አገልግሎት አሰጣጣቸው ጤናማ ይሁን አይሁን በጊዜው መርምረው ጥንካሬያቸውን ማስቀጠል እንዲሁም ድክመታቸውን ለማስተካከል የሚያግዝ መድኃኒት ባለመዋጣቸው መሆኑም የሚያከራክር አይደለም።

በአገልግሎት ጥራት ልኬት መነፅር የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከት ታዲያ የምናገኘው ምስል ብዥ ያለ ነው። በሀገሪቱ በተለይ በመንግሥት ተቋማት የሚስተዋለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ለሁላችንም ግልፅ ነው። በሀገሪቱ ከውስን ተቋማት በስተቀር አብዛኞቹ አገልግሎት አሰጣጥ በቀርፋፋነት ወይም ቀልጣፋ ባለመሆንና በውጤታማነት ማነስ ትችት የሚሰነዘርበት ነው። አገልግሎት አሰጣጡ እየጨመረ ከመጣው አገልግሎት ፈላጊ እንዲሁም ለፈጣንና ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ራሱን ያዘጋጀ እንዳልሆነም የአደባባይ ሃቅ ነው።

በተለያዩ ተቋማት ‹እሺ› ከማለት ይልቅ ‹‹እንቢ›› ማለት የሚቀላቸው ባለሙያዎችን መመልከት የተለመደ ነው። በተለይ አንዳንድ አመራሮች አገልግሎት አሰጣጥ በማንሻፈፍ ዜጎችና ባለጉዳዮች እንዲማረሩ በማድረጉ በኩል የተካኑ ናቸው።

በርግጥ የለውጡ መንግሥት አገልግሎት አሰጣጡን “ለማዘመን” ባደረገው ጥረት ብዙ ለውጦች ተደርገዋል። ውጤት የታየባቸውም አካባቢዎችም በርካቶች ናቸው። ይሁንና ለውጡ ተገልጋዩ ኅብረተሰብ የሚፈልገውን ቀልጣፋ፣ በባለሙያ የተሞላ፣ ተጠያቂነት

**በኢትዮጵያ የተለያዩ ተቋማት መሰል ክስተቶች በሚገጥማቸው ወቅት ‹‹የተበሳጨበት ምክንያት ገብቶኛል በችግሩ መፈጠር ብዙ መድከሞትንም እረዳለሁ፣ ሁኔታው እኔም ላይ ቢደርስ ከዚህ የተለየ ስሜት አይኖረኝም›› የሚሉ አግባቢ አስተያየቶችን በመስጠት አገልግሎት ፈላጊን አግባብተው የሚያስተናግዱ ባለሙያዎች እንዳሉም የሚካድ አይደለም። በተቃራኒው በተለያዩ ተቋማት በትንሽ በትልቁ ‹‹ውሃ ቀጠነ›› በሚል ሰበብ ስሜታዊነትን የሚያንፀባርቁ አገልግሎት ሰጪዎችም አሉ**

የሰፈነበት ሥርዓትን በማስፈን ረገድ ብዙ እንደሚቀር ለክርክር የሚያስቀምጥ አጀንዳ አይደለም።

የአንድን ሀገር አገልግሎት አሰጣጥ በሁሉ ረገድ ውጤታማ ለማድረግ ወሳኝ ከሆኑ መፍትሔዎች መካከልም የአገልጋይነት ሥነልቦና እንዲሁም ባህሪ ቀዳሚ ሆኖ የሚቀመጥ ነው። በዘመናዊው ሕብረተሰብ ውስጥ የአገልጋይነት ጽንሰ ሃሳብ፣ በገንዘብና በንብረት ጥቅም የሚለካ ሳይሆን ከራስ ፍላጎት ይልቅ የሌሎችን ፍላጎት ያስቀደመ፣ ከመቀበል ይልቅ በመስጠት ላይ ያተኮረ ሌሎችን አክብሮ ከሚሰጥ የላቀ አገልግሎትና ከተገልጋይ እርካታ የሚገኝ ሐሴት ነው።

አገልጋይነትም ሥጋዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሕሊናዊና ስብዕናዊ እርካታዎችን የሚያጎናጽፍ እሴት ወይም የማንነት መገለጫ ነው። አገልጋይነት በብዙ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ተቀባይነት ያለው ነው። አገልጋይነት በውልና በስምምነት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን ከራስ በጎ የማድረግ ሃሳብ የሚመነጭ በመሆኑ ገደብ የሌለው ጽንሰ ሃሳብ ያደርገዋል። በመሠረቱ፣ አገልጋይነት የሌሎችን ፍላጎት ከራስ ማስቀደምና ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መንገድ በትህትና የማገልገል ባህሪይና ተግባር ነው።

የአገልጋይነት አላባውያን ተብለው ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ ትህትና ነው። አገልጋይ ለሥራው ትኩረትን ወይም እውቅናን ሳይፈልግ ማገልገልን ብቻ ቀዳሚ ተግባሩ ያደረገ ነው። ሌላኛው የአገልጋይነት ገጽታ ራስን መስጠት ነው። ይህ ማለት ሌላ ሰውን ለመርዳት ጊዜን፣ ሀብትን ወይም የራስን ምቾት መተውን ያካትታል። ከራስ በላይ ሌሎችን ለማስቀደም ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል። አገልጋይነት ርህራሄና መተሳሰብ ነው። እውነተኛ አገልጋይ የሌሎችን ፍላጎት የሚረዳና ችግራቸውን ለማቃለል የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው።

በኢትዮጵያ ሌሎችን ለመርዳት ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በሚሰጡ በጎ ፈቃደኞች፣ የታመሙትን ለመንከባከብ ራሳቸውን ለአደጋ በሚያጋልጡ የጤና ባለሙያዎች፣ የሀገር ሉዓላዊነት የሚያስጠብቁ የፀጥታ ባለሙያዎችና ነገን በቀጣይ ትውልድ ላይ የሚሰሩ መምህራኖች እንዲሁም በየደረጃው በርካታ ድንቅ አገልጋዮች አሉ። ከእነዚህ አገልጋዮች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የአገልጋይነት ምግባሩም ተግባሩም የማይገልፃቸው መኖራቸው የሚካድ አይደለም።

እንደሚታወቀው፣ የአገልግሎት አሳጣጥን ውጤታማ ለማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ መርሆችን ያከበረ፣ ያገናዘበ፣ የደንበኛ እርካታን የሚጨምር፣ የተቋምን ስምና ዝና የሚጠብቅና ቅሬታና የሚቀንስ ባለሙያ ወይንም አገልጋይ እጅጉን ወሳኝ ነው።

በpublic administration ስር public service ላይ የተሰነዱ ጽሑፎችና ጥናቶች እንደሚያሳዩትና የዘርፉ ምሁራን ሲገልጹ እንደሚሰማው አገልግሎት የተለያዩ ባህሪያት አሉት። አንደኛው ባህሪው አገልግሎት በደንበኛ ዓይን ሲታይ ነው። ለምሳሌ ትናንት ወደ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ሄዶ ባገኛው አገልግሎት ረክቶና ተደስቶ የተመለሰ ደንበኛ ወይም ተገልጋይ ዛሬ ባገኘው ተመሳሳይ አገልግሎት ጥራትና ደረጃ ላይረካ ይችላል። በተለይም

ሁለተኛው የአገልግሎት ባህሪ በደንበኞች ሚዛን የሚለካ መሆኑ ነው። ይህ ማለት የአገልግሎት እርካታ ከደንበኛ ደንበኛ የሚለያይና ሳብጀክቲቭ መሆኑ ነው። ለአብነት ሁለት የተለያዩ ደንበኞች ወደ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሄደው የሚፈልጉትን አገልግሎት አግኝተው ቢመለሱና ስሜታቸውን ቢጠየቁ የሚመልሱት ተመሳሳይ አይሆንም።

የተገልጋዮች እርካታ በሌለበት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት አይኖርም። ጥሩ የመግባባት ችሎታ፣ የላቀ የሥራ ተነሳሽነትና ብቃት ያላቸው አገልጋዮች በተገልጋዮች ዘንድ መልካም ገፅታና የላቀ የአገልግሎት አሰጣጥ እንደሚኖራቸው እሙን ነው።

‹‹ከፍትፍቱ ፊቱ›› እንደሚባለው ፊት ያቀርባል ወይም ያርቃል። ተስፋ ይሰጣል ወይም ቅስም ይሰብራል። ፊት ያስደስታል ወይም ያበሳጫል። አገልጋይነት ከበር ጀምሮ ደስ ከሚል ፈገግታና ሰላምታ ጋር “እንኳን ደህና መጣችሁ! ምን ልርዳችሁ?”፣ ወደየት ቢሮ መሄድ ፈለጋችሁ?” ብሎ ከመጠይቅ የሚጀምር ነው።

ወደ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመጡ ተገልጋዮች ከሚጠብቁትና ወይም ከሚገምቱት በታች የሆነ አገልግሎት ሲገጥማቸው እጅጉን ቅር ያሰኛሉ። ተገልጋዮች አገልግሎት ፈልገው በሚመጡበት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ሊበሳጩ፣ ከአገልግሎት ሰጪው ጋር ያላቸው ግንኙነት አስቸጋሪ፣ በቁጣና በብስጭት የተሞላ ሊሆንም ይችላል።

በኢትዮጵያ የተለያዩ ተቋማት መሰል ክስተቶች በሚገጥማቸው ወቅት ‹‹የተበሳጩበት ምክንያት ገብቶኛል በችግሩ መፈጠር ብዙ መድከሞትንም እረዳለሁ፣ ሁኔታው እኔም ላይ ቢደርስ ከዚህ የተለየ ስሜት አይኖረኝም›› የሚሉ አግባቢ አስተያየቶችን በመስጠት አገልግሎት ፈላጊን አግባብተው የሚያስተናግዱ ባለሙያዎች እንዳሉም የሚካድ አይደለም። በተቃራኒው በተለያዩ ተቋማት በትንሽ በትልቁ ‹‹ውሃ ቀጠነ›› በሚል ሰበብ ስሜታዊነትን የሚያንፀባርቁ አገልግሎት ሰጪዎችም አሉ። በርግጥ ከግለሰብ ባህሪ ባሻገር ብቸኛ ሆኖ ለብዙ ደንበኞች አገልግሎት መስጠት መሰል ስሜታዊነትን ሊፈጥር እንደሚችል መገመት አይከብድም።

በተቋም ውስጥ የእርስ በእርስ ግንኙነት ሰላማዊ መሆንም መሰል ስሜታዊነትን የማስቀረት አቅሙ ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም የቅርብ የሥራ ባልደረባቸው እንዲሁም ከአለቃቸው ጋር ጥሩ ተግባቦት የሌላቸው እንዲሁም በአለቃቸው ተገቢው ክብር የማይሠጣቸው አገልጋዮች ለተገልጋዮች ፈገግታ፣ ክብርና ትህትና ይሠጣሉ ብሎ መጠበቅ ትልቅ ስህተት ስለሆነ ነው።

ከአገልጋይነት እሳቤ ጋር ሲመዘን ይህ ትልቅ ድክመት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። መሰል የአገልግሎት አሰጣጥ ድክመት የሀገርን ሁለንተናዊ እድገት ከመጎተት ባሻገር ሕዝብ በመንግሥት ተቋማት ላይ ያለውን አመኔታ እንዲሸረሸር ከፍ ሲልም እንዲሟጠጥ ያደርጋል።

በኢትዮጵያ ምድር ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ሲታሰብ መሰል ድክመቶችን ማረም የግድ ነው። የሀገር ገጽታን ከሚያጨልሙ ችግሮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ጉዳይ ካልታሰበበት አሳሳቢ ነው። ልፋቶችን በሙሉ በዜሮ ያባዛል። በአሁን ወቅትም አገልግሎት አሰጣጥን በአግባቡ መምራት ማስኬድና መግዛት ትኩረት ከሚሠጣቸው ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ማድረግ አማራጭ ሳይሆን የግድ ነው።

እየጨመረ ከመጣው አገልግሎት ፈላጊ ጋር ሊጣጣም የሚችል ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ጠንካራ ተቋማት የአሰራር ሥርዓት ሊኖር የግድ ነው። የአገልግሎት አሰጣጥን ችግሮች ከስር መሰረታቸው ለማስተካከል መንግሥት አገልግሎት አሰጣጡም እንዲሁም የአገልጋይነት መንፈስን ትራንስፎርም ማድረግ ይኖርበታል። በተለይ የአገልጋይነት ስሜትና እውቀቱ የጎደላቸውን፣ ሕዝብን የሚያስለቅሱ፣ የሚበድሉ፣ የሚመዘብሩ፣ ፍትህን የሚረግጡ፣ ሲያሻቸውም በመንግሥት መመሪያ ስም እያጭበረበሩ ሲላቸውም የጠሉትን ለመበቀል የወደዱትን ለመጥቀም የሚራወጡ አመራሮችን አድኖ ከወንበራቸው ማስነሳት አለበት።

ተቋማትም ውስጣዊ አሰራራቸውን በመፈተሽ ዘመናዊና ከዓለም ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በተወዳዳሪነት ለመራመድ የሚችል የአገልግሎት አሰጣጥን ማጎልበትና የአገልጋይነት መንፈስን በቅጡ የተረዱና በአግባቡ መተግበር የሚችሉ ባለሙያዎችን ማፍራት ይኖርባቸዋል።

ዘመናዊ የአገልግሎት ባሕልና ባለሙያዊነትን ከማዳበር ባሻገር በጊዜው ለአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ልኬት በራቸውን ክፍት ማድረግም እጅጉን ወሳኝ መፍትሔ ነው። በሀገሪቱ ከሚገኙ አገልግሎት አሰጣጥ ሁለንተናዊ ጥራት ስማቸው ከሚገኙ ተቋማት ልምድ መቀመርም ለውጤታማነት ወሳኝ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው።

በአጠቃላይ የአገልጋይነት ቀን ስናከብር ‹‹እኔ በተሰማራሁበት መስክ፣ በያዝኩት የሥራ መደብ የሚጠበቅብኝን ኃላፊነት እየተወጣሁ ነኝ? ብሎ ከመጠየቅ ባሻገር በተለይ በቀጣዩ ዓመት በየተሠማራንበት የሥራ መስክ አገልግሎት በምንሠጥበት ወቅት በትህትና፣ በደግነትና በሥራ ወዳድነትና በአገልጋይነት መንፈስ በማገልገል ለሀገር እድገትና ብልፅግና የራሳቸው ድርሻ ለመወጣት ቃል ልንገባ ይገባል። አጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ቆርጠን መነሳት፣ በደረጃው ከመቀበል ይልቅ በመስጠት ላይ ያተኮረ የአገልጋይነት አስተሳሰብና እምነት በሕዝብ ውስጥ ማስረፅም ይኖርብናል።

ከዚህ ባሻገር በቅንነትና በታማኝነት ሀገራቸውን ያገለገሉትንና በማገልገል ላይ ያሉትን ዜጎች በማመስገንና ማገልገል ክብር የሆነበት ሀገር ለመገንባት ትኩረት ልንሰጥ ይገባል። በሚጠበቅባቸው ልክ ያልተወጡትን ደግሞ መውቀስና መገሰጽም ይኖርብናል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «አገልጋይነት የተለወጠ አስተሳሰብን ይጠይቃል»

- አቶ ሰለሞን ተስፋዬ
የሥራ አመራር ባለሙያ

አመለወርቅ ከበደ



አመራርነት አገልጋይነት ነው። በአዲስ አስተሳሰብ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ማገልገል ነው። መሪዎች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት ይዘው ሕዝብን ወይም ተቋምን ሲያገለግሉ እንደ ተቋም ሆነ እንደ ሀገር ለውጥ ይመጣል።

በዛሬው የዘመን እንግዳ ገጽ በአገልግሎት አሰጣጥና በመሪነት ውስጥ ያለ አገልጋይነትን በተመለከተ ከዛሬው እንግዳችን አቶ ሰለሞን ተስፋዬ ጋር አዲስ ዘመን ቆይታ አድርጓል።

አቶ ሰለሞን ተወልደው ያደጉት በአዲስ አበባ ከተማ መስፍን ሐረር መንገድ ወይም አዲሱ ገበያ አካባቢ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በዳግማዊ ምኒልክ፤ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተከታትለዋል።

በሕግ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ እና በአካውንቲንግ ዲፕሎማ፤ በንግድ ሥራና አስተዳደር ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው። በተጨማሪም በኢንፎሜሽን ሲስተም አስተዳደር እና በትምህርት አስተዳደር የሁለተኛ ዲግሪቸውን ሰርተዋል።

በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች በአመራርነት የሰሩ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ለአስራ ሶስት ዓመታት በመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነው አገልግለዋል።

በአጠቃላይ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ለ41 ዓመታት በሥራ ላይ ቆይተዋል። በ2013 ዓ.ም በጡረታ ከሥራ የወጡ ቢሆንም አሁን ላይ በአንድ የግል መሥሪያ ቤት በጊዜያዊነት ተቀጥረው እያገለገሉ ይገኛል። በአጠቃለይ ከእኚህ ጉምቱ ባለሙያ ጋር የነበረን ቆይታ እንደሚከተለው ተጠናቅሯል።

**አዲስ ዘመን፡- አመራር ስንል ምን ማለት ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አመራር ግልጽ የሆነ ራዕይ ይዞ ተቋሙን እና ፈጻሚውን በመለወጥ አሰራርን መቀየር ነው። አመራር ክህሎት ይጠይቃል፤ ስለዚህ በአመራር አሰራሮችን እንቀይራለን።

አመራር ሥራንና ሥራን ብቻ ማዕከል ያደረገ፤ ሰውን እና ሥራን እየመራ ከለውጥ ማድረስ ነው። ከፈጻሚዎቹ ጋር አብሮ እየሰራ፣ ቁርጠኛ እንዲሆኑ እያበረታታ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል ነው። አመራር የሚሆኑት መሪዎች ናቸው። መሪ ስንል የሃይማኖት መሪ አለ፣ የተቋም፣ የሀገር እና የተለያዩ ተቋማት መሪዎች አሉ። በመሪነታቸውም ብዙ ኃላፊነቶች የመወጣት ኃላፊነት አለባቸው።

‹‹ለውጥ የለውጥ ካፒቴን ይሻል ይላል›› ማይክ ራመር፤ ስለዚህ ለአንድ ተቋም መሪ ወሳኝ ነው። ለተቋሙ ውድቀት ሆነ መነሳት የመሪው ተግባር ነው የሚወስነው። ይህን ማድረግ የሚችል ሰው ነው እንደመሪ የሚቆጠረው።

መሪ ከራዕይ ይጀምራል። እሴቶች፣ ግቦች፣ እቅዶች እና አሰራሮች ያማከለ ነው መሆን ያለበት። የትምህርት ዝግጅት ስላለው እና ለፖለቲካ ታማኝ ስለሆነ ብቻ መሪ መሆን አይችልም። ክህሎት ይጠይቃል፤ ልምድ ይጠይቃል።

እነዚህ መስፈርቶች ባለመሟላታቸው ነው ብዙ ጊዜ አንድ ሰው ሥልጣን ላይ ከተቀመጠ በኋላ ውድቀት የሚያጋጥመው። መጀመሪያ አንድ ሰው ሲሾም የኋላ ታሪኩ መታየት አለበት። ለህብረተሰቡ፣ ለሀገር ያበረከተው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? እውቀቱስ ምን ይመስላል የሚለው መታየት አለበት።

ብዙ ጊዜ ትምህርት ነው የሚታየው፣ ነገር ግን ትምህርቱ ያን ሰው ይገልጸዋል ወይ? የሚለው መታየት አለበት። በሥራ ዓለም ሆነ በሌሎች አጋጣሚዎች እንደተመለከትኩት፤ እራሳቸውን መግለጽ የሚያቅታቸው ብዙ መሪዎች አሉ። ለዚህ ነው አንድ መሪ፤ መሪ ነው ለመባል እውቀትና ታማኝነቱ ብቻ በቂ አይደለም የምለው። እውቀት እና ልምድ ያስፈልጋል ለማለት ፈልጌ ነው።

አንዳንድ ተቋማት ላይ እንደምንመለከተው መሪዎች በሰሩት ጥሩ ሥራ እና በትምህርት ደረጃቸው ወደ ኃላፊነት ይመጣሉ። በተቃራኒው ደግሞ በትውውቅ ብቻ የሚመጡ አሉ። እናም ችግሩ ያለው እሱ ጋር ነው። መሪነት ልምድና ክህሎት ይጠይቃል የምለው ለዚህ ነው።

ለምንድነው በየቦታው ስንሄድ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር የምናየው? ህብረተሰቡ ለምን ይንገላታል? የሚለውን ስንፈትሽ ከአመራር ጥበብ ጋር ይያያዛል። እዚያ ቦታ ላይ መሪ እስካለ ድረስ፤ ሰው የሚጉላላው ለምንድነው? ያ ሰው መሪ ነው ለማለት ህብረተሰቡ ጋር ያለው መጉላላት ብቻ ማየት በቂ ነው።

ወደ በርካታ ተቋማት ሲኬድ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴት ተለጥፎ እናያለን። በተጨማሪ ደግሞ የሥነ ምግባር መርሆች እናያለን። እነዚህ ነገሮች አመራሩም ሆነ ፈጻሚው በአግባቡ ይረዳቸዋል ወይ የሚለው ጥያቄ ያጭርብኛል።

እንደዚህ የምለው በየቦታው ያለውን መጉላላት ስመለከት ነው። አገልግሎት ሰጪ ተቋሞቻችን ደንበኛን አክብረው ማስተናገድ ይጠበቅባቸዋል። አመራር ሁልጊዜ የተገልጋይ ርካታን የህልውና ጉዳይ አድርጎ መውሰድ አለበት። ችግሮች መኖራቸው አይቀርም ያሉትን ችግሮች እንዴት ነው መቅረፍ የሚቻለው የሚለውን ቁጭ ብሎ ማሰብ መቻል አለበት።

አልበርት አንስታይ በዚህ ዙሪያ የጻፋቸው በርካታ ነገሮች አሉ። አሁን ‹‹ያሉብንን ችግሮች መቅረፍ የምንችለው፤ ችግሮችን በፈጠረው አስተሳሰብ ሳይሆን፤ በአዲስ አስተሳሰብ ነው›› ይላል። አመራር ሆኖ ሲመረጥ አንድ ሰው የኋላ ታሪኩ መጠናት አለበት። የቤት ሥራዎቹን መሥራት አለበት። ምንድነው መሥራት ያለብኝ? ያለውን የአረጀና ያፈጀ አሰራር እንዴት ነው የምቀይረው? የሚሉ ነገሮችን በማሰብ ወደ ተግባር መቀየር አለበት።

ለውጥ ብዙ ጊዜ ተግዳሮቶች አሉት። ለውጥ የመጣለት ሲደሰት፤ ለውጥ የመጣበት ያለቅሳል። የሚከፉበት ምክንያት በአረጀ አሰራር ተጠቃሚ የሆነ ሰው የሚቀርበት ነገር ስላለ መከፋቱ አይቀርም። አዲስ አሰራር የመጣለት ሰው ደግሞ መደሰቱ አይቀሬ ነው።

ስለዚህ አንድ ሰው ወደ ሹመት ከመሄዱ በፊት ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለውን ነገር መቅረፍ አለበት። ለውጥ የህልውና ጉዳይ አድርጎ መውሰድ፣ በራስ መተማመን፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ወደ ሥራ ለማስገባት ከሌሎች መኮረጅ ያስፈልጋል። መኮረጅ በራሱ ለእኔ እውቀት ነው። በዚህ ረገድ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) በጣም ነው የማመሰግናቸው፤ ወደ ተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች ሲሄድ ትልቅ ለውጥ ነው የሚታየው። ይህን ነገር አምጥቶ ሥራ ላይ ማዋል በራሱ ትልቅ ነገር ነው።

በእንግሊዝኛ አጠራሩ ቤንች ማርክ የምንለው እኮ ከሌሎች ተሞክሮ መውሰድን ነው። እኔ አሁን ራስ ደስታ ላይ የግል ህክምና መስጫ ለማቋቋም፤ ኦሮሚያ ሄጄ ነው ልምድ የቀሰምኩት። ቢሾፍቱ ሆስፒታል ላይ ተቋቁሞ ስለነበር የግል ህክምና መስጫ እዛ ሄጄ ቤንች ማርክ አደረኩ። በኋላም አዲስ አበባ አምጥቼ በሁሉም ሆስፒታሎች እንዲተገበር አደረግኩ።

"መጥፎ ጎረቤት እቃ ያስገዛል" ይባላል። ይህ ማለት አንድ ጎረቤት ሁልግዜ እየመጣ እቃ ልዋስ ብሎ የሚጠይቅ ከሆነ፤ የሚያውሰው ጎረቤት በመሰላቸት የለም ይላል። ያን ጊዜ የሚዋሰው ሰውዬ በቁጭት የሚያስፈልገውን እቃ ይገዛል። ለዚህ ነው፤ ቁጭት ሁልጊዜ የለውጥ መንስኤ ነው የሚባለው።

ከወዳጆቻችን መልካም ነገሮችን ስናይ ያን ነገር ለማድረግ በቁጭት እንነሳለን። ከዛን እናደርገዋለን። ቁጭት የለውጥ መንስኤ ነው የሚባለው ለዚህ ነው። ለዚህ ነው አመራር ቁርጠኛ መሆን አለበት የሚባለው።

**የአዲስ ዘመን፡- የአንድ መሪ የአስተዳደግ መንገድ በመሪነት ሥራው ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ይችላል? ምን ዓይነት ተጽዕኖ ነው የሚያሳድረው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በእድገት የሚያጋጥም ነገር ይኖራል፤ ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገሮች ከእድገት ጋር ተያይዘው ሊንጸባረቁ ይችላሉ። ነገር ግን ይህ ነገር በትምህርት ይቀየራል። በተለያዩ መንገድ የሚያድጉ ልጆች 12ኛ ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ይገባሉ። በከፍተኛ ትምህት ቆይታቸው እንደተማሩበት የትምህርት መስክ ዕውቀት ይገበያሉ፤ የሕይወታቸውም አካል ያደርጉታል። ለአብነት የአስተዳደር ትምህርት ከተከታተለ አስተዳደራዊ እውቀት ይዞ ነው የሚወጣው።

**ለውጥ ብዙ ጊዜ ተግዳሮቶች አሉት። ለውጥ የመጣለት ሲደሰት፤ ለውጥ የመጣበት ያለቅሳል። የሚከፋበት ምክንያት በአረጀ አሰራር ተጠቃሚ የሆነ ሰው የሚቀርበት ነገር ስላለ መከፋቱ አይቀርም። አዲስ አሰራር የመጣለት ሰው ደግሞ መደሰቱ አይቀሬ ነው**

ያገኘው እውቀት ከክህሎት ጋር ሲታከል ያ ግለሰብ በቂ መሪ ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ከከፍተኛ ትምህርት በአካውንቲንግ የተመረቀ ሰው መጀመሪያ የሚማረው ንድፈ ሃሳቡን ነው። አጠቃላይ ስለወጪ፣ ገቢ እና ሌሎች ነገሮች፤ ክህሎት የሚኖረው ወደ ሥራ ከገባ በኋላ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ክህሎት ያስፈልጋል ሲባል በኑሮ ያዳበረው ወይስ በሥራ ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አመራርነት በመወለድ የምናገኘው ነገር አይደለም። ምናልባት በሩህሩህነት፣ አስተዋይነት እና የመሪነት ባህሪ በተፈጥሮ ሊኖር ይችላል። እድገት የሚሰጠው ነገር የአመራርነት ሂደቱን ሊያፋጥነው ይችላል። የሚዳብረው ግን በትምህርት ነው።

ጋዜጣዎች ላይ የሥራ ቅጥር ሲወጣ ይሄን ያህል ዓመት የሥራ ልምድ ይላል። ይህም ክህሎትና ልምድ ያለው ሰው ስለሚፈለግ ነው። ጀማሪ ሰው ተቀጥሮ አመራር ሊሆን አይችልም።

ትምህርቱን ነው እንጂ የወሰደው ሰውም ሆነ ሥራ እንዴት እንደሚመራ አያውቅም። ሥራ ላይ በቆየ ቁጥር ከጓደኞቹ እና ከአለቆቹ ያለውን አሰራር እየተማረ ይሄዳል።

ለምሳሌ ከቤተሰብ አንድ ቤተሰብ ቤቱን የሚያስተዳድርበት መንገድ፤ እንዴት ነው? አባት ቤተሰቡን የሚያስተዳድረው ከሚለው ስንነሳ፤ ለአንድ መሪ ተጨማሪ እውቀት ይሰጣል። የኑሮ ክህሎት ከሰብዓዊነት ጋር ነው የሚገናኘው፣ በተፈጥሮም የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ የሃይማኖት መሪነት ከሃይማኖት ትምህርት ጋር የሚመጣ ነው። በተጨማሪም ከእድገታቸው ጋር የሚመጣ አለ። ሆኖም ትምህርት እና ልምድ ወሳኝ ነው።

አንድ መሪ መጀመሪያ ከላይ ከአስተዳደር ሆነ ከተቆጣጣሪ አካላት ልምድ እያዳበረ ሲመጣ ነው ብቁ መሪ ሊሆን የሚችለው። የቀረውን ደግሞ እያነበበ ይሞላዋል። አንድ ጊዜ ከትምህርት ቤት ተወጣ ተብሎ ንባብ መተው አይገባም። ሁልጊዜ እራስን ለማሸነፍ መማር ያስፈልጋል። በተከታታይ የትምህርት ሂደቶች

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «አገልጋይነት የተለወጠ አስተሳሰብን...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

አንድ ሰው ብቁ ይሆናል። እናም በብዙ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች አንዱ ክፍተታቸው እራሳቸውን እያበቁ አለመሄዳቸው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጣችን ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ከአመራር ክፍተት ብቻ ነው ብለን መውሰድ እንችላለን?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ሙሉ ለሙሉ ነው ማለት ባይቻልም በአብዛኛው ግን ከአመራር ክፍተት ጋር የሚያያዝ ነው። ብዙ ጊዜ ምን ሰራ?፣ ለሀገር ምን አስተዋጽኦ አደረገ?፣ የት መሥሪያ ቤት ሆኖ ምን ውጤት አስመዘገበ?፣ የአመራር ብቃቱ ምን ይመስላል ? የሚለው ሲታይ አንድ ሰው ወደ ሹመት ይመጣል።

እኔ ለ13 ዓመታት በአዲስ አበባ ምክር ቤት አባል እና የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ነበርኩ። በእነዚህ ዓመታት እይታዬ ብዙ ሰው ሾመናል። አንድ ሰው ይሄ ሹመት አይመጥነኝም፤ ለዚህ ሹመት ብቁ አይደለሁም የሚል ተሿሚ አይቼ አላውቅም።

ምክንያቱም የሚታያቸው በሥልጣኑ ምክንያት የሚያገኙት ጥቅም፣ ክብር ብቻ ስለሚታያቸው ነው። የሕዝብና የመንግሥት አደራ እየተሸከሙ መሆኑን አይረዱም። ለዚህ ነው አንዳንድ ተሿሚዎች በተሾሙ በስድስት ወር ውስጥ ከሥልጣን ሲወርዱ የምናያቸው። ወደ ወረዳ ወይም አንድ አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ሲኬድ ሰው ሲጉላላ ይታያል። ለዚህ ለምን ከተባለ መሪው ትክክል ስላልሆነ ነው። ህብረተሰቡ የሚያዝነው በሾመው አካል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የምክር ቤቱ አባል እንደመሆኖ አንድ ሰው ለሹመት ሲቀርብ ግምገማ አታደርጉም?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የሚሾሙ አመራሮችን የሚሾመው አካል እገሌ ለዚህ ቦታ የተሻለ ነው ብሎ ያመጣቸዋል። እኛ ደግሞ ስለተሿሚው የቀረበውን ገለጻ አድምጠን ሃሳብ እንሰጣለን። ያመጣው አካል አምኖበት ስለሆነ ያመጣው በሚል ድጋፍ ይሰጣል። ለዛ ነው የተሾመው አካል ለውጥ ካላመጣ የሾመውን አካል አንገት ያስደፋል ያልኩት።

ቅድም እንዳልኩት አንድ ሰው ወደ አመራር ሲመጣ ብቃቱ ታይቶ አይደለም። በትውውቅ የሚመጡ ብዙ ናቸው። ይህ ደግሞ ሀገርን ይገድላል፤ ሕዝብን ያማርራል።

**አዲስ ዘመን፡- አንድ አመራር ራሱን ለማሳደግና የህብረተሰቡን ጥያቄ ለማርካት ምን ማድረግ አለበት?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አመራር በማያቋርጥ ሁኔታ ራሱን እያሻሻለ መሄድ አለበት። የትላንት እውቀት ለዛሬ አይረዳም። ስለዚህም ሁልጊዜ ራሱን ለማሻሻልና ለመለወጥ መጣጣር አለበት። የሚያከናውናቸው ነገሮች ምን ያህል ህብረተሰቡን እያረኩ ነው ብሎ ዘወትር መፈተሽ አለበት።

ይህን ለማድረግ ደግሞ ማንኛውንም መጽሐፍ ማንበብ አለበት። ነገር ግን አቅሙን ለማሳደግ አመራርነት ላይ የተጻፉ መጻሕፍትን የበለጠ ቢያነብ፤ አዳዲስ እውቀቶችን ያገኛል፤ ሌሎችንም ይቀይራል። ከባዱ ነገር ሰው መምራት ነው፤ ሰው ላይ ደግሞ ሥራ አለ። ሁለቱን አቀናጅቶ መምራት ለአንድ መሪ ትልቅ ክህሎት የሚጠይቅ ነው።

አመራር እኮ ማለት ማዘዝ እና መፈረም ብቻ አይደለም። አብሮ መሥራት አለበት፤ ስለሥራው ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ከስር ያሉ ሠራተኞች ስለሚሰሩት ሥራ ሲጠየቅ፤ ምላሽ መስጠት ካልቻለ እሱ መሪ አይደለም። ትክክለኛውን ሰው፤ በትክክለኛ የሥራ ቦታ ማስቀመጥ መቻል አለበት የሚባለው ለዚህ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አንድ አመራር በተቋሙ ሲሾም፣ ሁሉንም ነባር አሰራሮች መቀየር አለበት? ይሄ ነገር የአሰራር ግንባታ ከሚለው ሃሳብ ጋር አይጣረስም?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ነባር አሰራሮች ሁሉም መቀየር አለባቸው አይባልም። እስከዛሬ ሲሰራ የነበረው ሥራ ሁሉም ስህተት ነው ማለትም አይቻልም። የነበሩ ጥሩ አሰራሮች ማጠናከር ይገባል። ስህተት ሆነው ነገር ግን ያልታዩ ነገሮች መታረም አለባቸው።

ለምሳሌ በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ፤ አንድ ሰው ለማስተናገድ 10 ደቂቃ የሚወስድ ከሆነ፤ አመራሩ ወደ አምስት ደቂቃ ዝቅ እንዲል ውሳኔ በማስተላለፍ



ይሰራበታል። ለውጥ ማለት አንዱ ይሄ ነው። ጊዜ ውድ ነገር እንደሆነ በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል። ስለዚህ ጊዜ በአግባቡ አለመጠቀም፤ በተዘዋዋሪ ገንዘብ እንደማባከን ይቆጠራል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ ነባሩ አሰራር ከመቀየሩ በፊት፤ አንድ አመራር ምን መሥራት አለበት?**

**አቶ ሰለሞን፡-** መጀመሪያ ከስር ያሉ አመራሮች ሰብስቦ በዘርፉ ያሉ ሥራዎችን እየጠየቀ ካደመጠ በኋላ በሁሉም አሰራሮች ዙሪያ በቂ እውቀት መጨበጥ ይኖርበታል። ከዛ በኋላ ያሉትን ሥራዎች እየዞረ መመልከት ይኖርበታል። ተዘዋውሮ በሚመለከትበት ወቅት የሚያያቸውን ክፍተቶች በመያዝ የመፍትሔ አሰራር ይዘረጋል።

አንዴ አሰራር ተዘርግቷል ተብሎ፤ እስከ እድሜ ልክ መቆየት የለበትም። ያለውን ክፍተት ካጠና በኋላ፤ ከስር ያሉ አመራሮችን በመጥራት ያሉትን ጥሩ ነገሮችን በመግለጽ፤ ክፍተቶችን ለመቀየር ደግሞ መወያየት ያስፈልጋል። የእያንዳንዱ ሰው አስተሳሰብ የተለያየ ስለሆነ ሃሳብ መቀበል እና ያሉትን ክፍተቶች መዝጋት ተገቢ ነው።

አመራር ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን አለበት። እሱ የሚናገረውንና ሊተገብር ያሰበውን ሌሎች አምነውበት ሊቀበሉት ይገባል። ተጽዕኖ መፍጠር የማይችል አመራር አዲስ አስተሳሰብ ፈጥሮ ሌሎችን ወደ ሥራ ማስገባት አይችልም።

ለውጥ ለማምጣት ዝም ብሎ ብቻውን መሮጥ አይደለም። መጀመሪያ ለውጥ የሚመጣበትን መንገድ ማየት ያስፈልጋል። ከስር ያሉ ፈጻሚዎችን ማገዝ፤ የሚያስፈልገውን ነገር ማሟላት፤ ጥያቄዎችን መመለስ አለበት። በአጠቃላይ ችግር ፈቺ እና ውሳኔ ሰጪ መሆን አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- የአንድ መሪ የአስተዳደር መንገድ ከስር ባሉ ፈጻሚዎች ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል? ካለስ በምን መልኩ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የራሱን ክህሎት እና እውቀት ከስር ያለው ሠራተኛ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት። በሥራ ላይ እና ከሥራ ውጭ በሚሰጡ ሥልጠናዎች አማካኝነት እገዛ ሊያደርግላቸው ይገባል። መሪው የሚያውቀውን ያህል ሠራተኛው እንዲያውቅ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

ዲፕሎማ ያለውን ሠራተኛ ዲግሪ ማስተር፣ ዲግሪ ያለው ደግሞ ማስተርስ እንዲማር በማድረግ፤ ተቋሙ የኔ ነው የሚል ስሜት እንዲሰማው ማድረግ አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- የአንድ አመራር አቅም የሚፈተነው ተቋሙ ችግር ላይ ሲወድቅ፤ ለችግሩ በሰጠው ምላሽ ነው ይባላል። ይሄን ሃሳብ እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የምቀበለው ሃሳብ ነው። የአመራር ክፍተት ካለ፤ ብቁ መሪ ካልሆነ፣ የትምህርት ዝግጅቱ እና የፖለቲካ ቁርጠኝነቱን ብቻ አይተን የምናመጣው ከሆነ፤ የተበተኑ ነገሮችን ማደራጀት ያቅተዋል። ከስህተት ያለመማር ሁኔታም ይፈጠራል። ችግሮች ሲፈጠሩ በቅጣት የሚያምን ነው የሚሆነው። አመራር ብቁ ካልሆነ ተቋም ነው የሚፈርሰው። መሪነት ማለት ተዳሮቶችን አልፎ ውጤት ማስመዝገብ ነው።

**ተጽዕኖ መፍጠር የማይችል አመራር አዲስ አስተሳሰብ ፈጥሮ ሌሎችን ወደ ሥራ ማስገባት አይችልም**

አመራር ስናመጣ ሁልጊዜ ጭንቅላታችን ማሰብ ያለበት ህብረተሰቡን ነው። በምሳሌ የምጠቅሰው መንጃ ፈቃድ ለማሳደስ ስንሄድ በአስር ደቂቃ ውስጥ የምንመለስበት ሁኔታ ነው ያለው። ስለዚህ ይህን አሰራር ወደ ሌሎች ማምጣት ያስፈልጋል። እንደዚህ ሲሆን ጊዜ አይባክንም፤ እነሱም ሥራቸውን ይሰራሉ እኔም ሥራዬን እሰራለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ወደ አንዳንድ ተቋማት ሲኬድ አመራሩም ሆነ ሠራተኛው በቢሮ አይገኙም። በዚህ ሁኔታ በቂ አገልግሎት መስጠት ይቻላል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አሁን አሁን በሥራ ቦታ ላይ አለመገኘት ለአገልግሎት አሰጣጡ ትልቅ ተግዳሮት እየሆነ ነው። አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች በሱስና በተለያዩ የግል ጉዳዮች ቢሮ የማይገኙበት ሁኔታ ሰፊ ነው። ግለሰቡ የተለያየ ሱስ ያለበት ከሆነ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። የማውቃቸው ሰዎች አሉ፤ ሥራቸውን ጠንቅቀው ይሰራሉ። ነገር ግን ጫት ለመቃም ከሥራ ገበታቸው ይጠፋሉ። አንድ ሰው አብዝቶ ከጠጣ ይታመማል። እንደዛ ሲሆን ደግሞ ከሥራ ይቀራል። ስለዚህ ሥራው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

እንደዚህ ዓይነት ሠራተኞችም ካሉ መሪው ሰብስቦ በማወያየት፤ ለሰውዬው ሕይወትም ሆነ ለተቋሙ ስለማይበጅ ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመጣ ማድረግ አንዱ የአመራሩ ኃላፊነት ነው።

በራሳቸው ገቢ የሚንቀሳቀሱ ልማት ድርጅቶችም ሆኑ በመንግሥት በጀት የሚንቀሳቀሱ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞቻቸው ተገቢ አገልግሎት መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ብዙ ጊዜ ክፍተቶች የሚስተዋሉት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ ነው። ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ ክፍተቶች የሚታዩት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ ነው።

ለዚህ ምክንያቱ መሥሪያ ቤቱን የሚያስተዳድረው መሪ የህብረተሰቡን ርካታ እየመዘነ ስለማይመጣ ነው። በዕለት ሥራዎች በመጠመድ ጊዜውን ያሳልፋል። ሰዎች ተሰልፈው ሲንገላቱ እየተመለከተ ችግሩን ለመፍታት የሚያደርገው ጥረት የለም። የሕዝብ እንግልት ግድ አይሰጠውም። እንደዚህ ዓይነት አመራር ደግሞ መንግሥትን ያሳዝናል፤ እራሱንም ያዋርዳል።

**አዲስ ዘመን፡- በአመራርነት ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት እና ቀጣይ ሀገርን በተገቢው መልኩ የሚያገለግል ብቁ ትውልድ ለማፍራት ምን ይሰራ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ትውልዱ ብቁ አገልጋይ እንዲሆን ከስር መሰራት አለበት። የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅ፤ የማንበብ ልማድ እንዲኖረው ማድረግ፤ በራስ መተማመን እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ የሚጀምረው ከስር ካሉት ትምህርት ቤቶች ነው።

በኋላም እነዚህ ልጆች ወደ ሥልጣን ለመምጣት የሚያስችላቸውን እውቀት ራሳቸውን በማስተማር ሊያዳብሩ ይገባል። አንድ ደራሲ በመጻፉ ላይ "አዕምሮህ አንተ ከምታስበው በላይ ነው" ይላል። ብዙ ሰው ትንሽ ችግር ሲገጥመው ‹‹ምን አስጨነቀኝ›› ይልና ይተወዋል። በዛን ወቅት አዕምሮውን እየዘጋ ነው። አዕምሮን ካሰራነው መሥራት የሚገባውን ያህል ይሰራል ማለት ነው። አሁን ግን ከአቅም በታች ነው እየሰራን ያለው።

በመንግሥት በኩል ደግሞ ወደ አመራር የሚመጡ ሰዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ሕዝብን የማገልገል ፍላጎትና እና ተነሳሽነት ያላቸው ሰዎች ብቻ ወደ አመራር እንዲመጡ ማድረግ አለበት። ይህ ሲሆን የሕዝብን ጥያቄ መመለስ ይቻላል፤ ህብረተሰቡም በመንግሥት ላይ ያለው መተማመን እንዲጨምር ይረዳል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ሰለሞን፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ‹‹ጳጉሜን ለጤና››

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የጤና ችግር ሲያገጥማቸው ወደ ሐኪም ቤት ሄደው መታከም አይችሉም። ከፍተኛ ህመም ከገጠማቸውማ የሚሞቱበትን ጊዜ ከመቁጠር ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖራቸውም። እንዲያም ሆኖ ግን በጤና መድህን አገልግሎት አማካኝነት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከሚያገኙት ገቢ ላይ በመጠኑ በመቆጠብ ህመም ሲያጋጥማቸው ወደ ሐኪም ቤት ሄደው የሕክምና ወጪያቸውን መሸፈን ችለዋል። ይህ ለእነርሱ ጥሩ እፎይታን የፈጠረ ቢሆንም ከፍተኛ ምርመራ የሚጠይቁ ህመሞች ሲያጋጥሟቸው ግን አሁንም መቸገራቸው አልቀረም።

በተለይ እንደ ሲቲ ስካን፣ ኤም አር አይ፣ አልትራሳውንድ፣ ራጅና ሌሎችም መሰል ምርመራዎችን በአቅም ውስንነት ምክንያት ለማድረግ ሲቸገሩ ይስተዋላል። ይህን ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ ነው ውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከል ላለፉት አስራ አራት ዓመታት ‹‹ጳጉሜን ለጤና›› በሚል መሪ ሃሳብ አነስተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የሕክምና ምርመራ አገልግሎት ዘመቻ ሲያካሄድ የቆየው። አልፎ አልፎም በምርመራ ውጤት ለሚገኙ ህመሞች ሕክምናና መድኃኒት ለህሙማን እስከ ማቅረብ የሚደርስ ሥራ አከናውኗል። ይህም ህብረተሰብን የማገልገል ትልቅ ተግባር ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ዓመቱን ሙሉ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ድርጅቱ ከሚመጡ ተገልጋዮች መክፈል ያልቻሉ ታካሚዎችን በመለየት አገልግሎቱን በነፃ እንዲገኙ አድርጓል። ባለፉት አሥራ አራት ዓመታትም በ‹‹ጳጉሜን ለጤና›› የሕክምና ምርመራ አገልግሎት ዘመቻ እስካሁን ድረስ ከ54 ሺ. በላይ የሚሆኑ ዜጎች የነፃ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል።

በሌላ በኩል ማዕከሉ ድንገተኛ አደጋ ለደረሰባቸው ወገኖች አምቡላንሶችን በመላክና ተጎጂዎችን ወደ ሕክምና ተቋም በማድረስ ከተጎጂዎች ጎን በመቆም ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። ማዕከሉ በሚገኝበት አራዳ ክፍለ ከተማ ላሉ ነዋሪዎች መታወቂያቸውን በማየት ብቻ ለምርመራ ሲመጡ በፐርሰንት ቅናሽ በማድረግ የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል። ዘንድሮም 15ኛ ዓመቱን በማስመልከት አምስቱን የጳጉሜን ቀናት የነፃ ምርመራ ዘመቻን ጨምሮ የተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራትን ለማድረግ ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ ሥራ ገብቷል። በዚህ ዘመቻም ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ ዜጎች የሲቲ ስካን፣ ኤም አር አይ፣ አልትራሳውንድ፣ ላብራቶሪና ሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከል ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ዳዊት ኃይሉ እንደሚናገሩት ማዕከሉ የተሟላ የዲያግኖስቲክ ኢሜጂንግ አገልግሎት፣ አድቫንስድ ከላብራቶሪና ፓቶሎጂ አገልግሎት እንዲሁም የጋስትሮኢንትሎጂ፣ ዩሮሎጂና ካርዲዮሎጂ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል። እነዚህን አገልግሎቶችንም ነው ‹‹በጳጉሜን ለጤና›› የምርመራ ዘመቻ ዝቀተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በነፃ የሚያቀርበው። እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎቱን ሊያገኙ የሚችሉትም በቅድሚያ 9888፣ 0940040404 ወይም 0940050505 ስልክ ቁጥሮች ደውሎ በመመዝገብ ነው።

አገልግሎቱን ፈልገው ለምርመራ የሚመጡ ሰዎች ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሆን ዘመቻው ትክክለኛ አላማውን ማሳካት ይችላል። ምክንያቱም የጳጉሜን ለጤና ዘመቻ ዋነኛ አላማ ነፃ ምርመራ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አቅም የሌላቸው ነገር ግን የሲቲ ስካን፣ ኤም አር አይ፣ አልትራ ሳውንድና የተለያዩ የላብራቶሪ ምርመራዎች የጂ አይ ኮሎኖስኮፒና ኢንዶስኮፒ ምርመራዎች ለሚያስፈልጋቸው ለማድረስ ነው።

እንደ አቶ ዳዊት ማብራሪያ የጳጉሜን ለጤና የምርመራ ዘመቻ የተጀመረው ማዕከሉ ገና እንደተመሰረተ ከዛሬ አስራ አራት ዓመት በፊት ነው። የዘንድሮው ደግሞ አስራ አምስተኛ ዓመት ዘመቻ ነው።

> ‹‹የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት በተጠናከረ መልኩ መሰጠት ከጀመረ ስድስት ዓመታትን አስቆጥሯል። የበጎ ፍቃድ ሥራ ከሚከናወንባቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ጤና ነው። በጤናው ዘርፍ በየዓመቱ በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች በወጣቶችና፣ ባለሀብቶችና በሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ይከናወናሉ››

በወቅቱ ማዕከሉ ይህን በጎ ተግባር ያኔ የጀመረው ገና በደንብ ሳይቋቋምና በእጁ ላይ በቂ ገንዘብ ሳይኖረው ነው። ዘንድሮ ይህ ዘመቻ ለአስራ አምስተኛ ጊዜ ሲደረግ ሌሎች በጎ ተግባራቶችም ተካተው ነው። ከጳጉሜን አንድ እስከ አምስት ድረስ ማዕከሉ የሚሰጣቸውን ምርመራ አገልግሎቶች ሁሉ በነፃ ይሰጣል።

ከዚህ ውጭ ግን ማዕከሉ ሌሎች የበጎ ሥራዎችን ያከናውናል። ለምሳሌ በዘንድሮው ዓመት ለተቸገሩ የጎዳና ተዳዳሪዎች ብርድ ልብስ ያበረክታል። የዓይን ምርመራና ሕክምና የሚያደርግበትና መነጽርና መድኃኒት የሚሰጥበት መርሃ ግብርም አለው። በካንሰር ከተጠቁ ወገኖች ጋር ማሳለፍ ፕሮግራምም ይዟል። ሌሎች በጎ ሥራዎችንም ያከናውናል። ማዕከሉ ከሚሰጠው ነፃ የምርመራ አገልግሎት በተጨማሪ በሌሎች የበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ የተሰማራው ጳጉሜን ለጤና የሚለውን መርህን ይበልጥ አስፍቶ ለማስቀጠል ነው።

የጳጉሜን ወር በጎ በጎ ነገሮች የሚሸተቱበት፣ ከአሮጌው ወደ አዲሱ ዓመት ሽግግር የሚደረግበት፣ አዲስ እቅድ የሚያዝበት፣ ከመጥፎ ሱስ እውጣለሁ ብለው ቃል የሚገቡበት፣ አገባለሁ፤ እወልዳለሁ የሚሉበት፣ እማራለሁ የሚሉበት ነው። ከዚህ አንፃር ውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከል በየዓመቱ ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ነፃ ምርመራ እንዲያገኙ በማድረግ በጎ ተግባር ይፈፅማል። ይህ በጎ ተግባር ሌሎችም በየራሳቸው እንዲፈፅሙ የሚያነሳሳም ነው።

ከጳጉሜን 1 እስከ 5/2016 ዓ.ም በሚካሄደው የጳጉሜን ለጤና የምርመራ ዘመቻ ከዚህ በፊት ከነበረው ልምድ በመነሳት አምና የተመረመረውን 1 ሺ. 500 ሰው ዘንድሮም ከዚህም በላይ ቁጥሩን በማሳደግ እስከ 2 ሺ. ሰው ለመመርመር ዕቅድ ተይዟል። ነገር ግን ሰዎች ምዝገባውን አካሂደው እንደ ኬዛቸው አስቸኳይነት ለምርመራ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ደግሞ ከጳጉሜም አልፎ እስከ ታኅሣሥ ድረስ ምርመራቸው ሊካሄድ ይችላል። ስለዚህ ሰዎቹ ተመዝገበው በየወረፋቸው ነፃ የምርመራ አገልግሎቱን ያገኛሉ። አገልግሎቱም በአዲስ አበባ በማዕከሉ በሚገኙ ሰባት ቅርንጫፎች ላይ ይሰጣል። በዋናነት ግን አገልግሎቱ በወዳጅነት ፓርክ ጀርባ በሚገኙ የውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከል ይሰጣል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ማዕከሉ በዚህ ዓመት ሰዎች አስቀድመው ጤንነታቸውን እንዲያውቁ ሶስት ዋና ዋና የጤና ጥቅሎችን አዘጋጅቷል። እነዚህ የጤና ጥቅሎች አንደኛው ለጤናዎ ይነሳሱ/be motivated/፣ ሁለተኛው ጤናዎን ያረጋግጡ/be reassured/ እና ሶስተኛው ለጤናዎ ይቅደሙ/be ahead/ የሚሉ ናቸው። እነዚህ የጤና ጥቅሎች አንድ ሰው ምንም ሳይሆን ጤነኛ እያለ በራሱ ተነሳሽነት ጤናውን በየጊዜው እንዲያረጋግጥ የሚያስችሉ፣ ምንም ነገር ከመጀመሩ በፊት በቤተሰብ ውስጥ የነበሩ የጤና ችግሮች ካወቁ በኋላ እነዚህን በሽታዎች ለመመርመር የሚረዱና በመጨረሻ የጤና እክሎች ከመከሰታቸው በፊት ትንንሽ ችግሮችን በማየት እነዛን ችግሮች ቀድሞ በመንቃት ምርመራዎችን ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው።

የራዲዮሎጂ ሕክምና ስፔሻሊስት ዶክተር ተስፋዬ ከበደ በበኩላቸው እንደሚሉት ማዕከሉ ይህን ነፃ የምርመራ እድል ሲያመቻች በምርመራ ወቅት ጨረር የሚያመነጩ መሳሪያዎች ስለሚኖሩና ሁልጊዜ ደግሞ ምርመራ የራሱ የሆነ የጎንዮሽ ጉዳት ያለው በመሆኑ ይህን ከግምት ውስጥ አስገብተው ወደ ምርመራ ቦታ መምጣት ይጠበቅባቸዋል። ለአብነት ሲቲ ስካንና ኤክስሬ ጨረር የሚያመነጩ መሳሪያዎች ናቸው። ሐኪም ምርመራው ያስፈልጋል ብሎ ፅፎ ካላዘዘ በስተቀር ሰዎች መጥተው ጤንነታችንን ማወቅ እንፈልጋለን ብለው ሊመረመሩ አይገባም።

ስለዚህ የሲ ቲ እስካንና የኤክስሬ ምርመራ ለማድረግ ወደ ማዕከሉ የሚመጡ ሰዎች ከሐኪም የታዘዘ ወረቀት ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል። አልትራሳውንድ፣ ኤም አር አይ፣ ኮሎኖስኮፒ፣ ላብራቶሪ ምርመራ ፈልገው ሰዎች ወደ ማዕከሉ ቢመጡ ሊሰራላቸው ይችላል። አቅም ሳይኖራቸው በሐኪም የታዘዘ ወረቀት ይዘው ወደ ማዕከሉ መጥተው ግን ሲቲ ስካን ወይም ኤክስሬይ መነሳት ለአደጋ ሊያጋልጣቸው ስለሚችል ለመመርመር የሚመጡ ሰዎች ይህን መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

በተለይ ሕፃናትና ነብሰ ጡሮች በጣም አስፈላጊ ካልሆነና በሐኪም ካልታዘዘ በስተቀር ጨረር ከሚያመነጩ መሳሪያዎች መራቅ ወይም ባይጠቀሙ ይመረጣል። ህብረተሰቡ ቢችል ከሐኪም የታዘዘ ወረቀት ይዞ መምጣት የሚችልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። ምርመራ ቦታ ላይ ያለውን የህክምና ባለሞያ ማማከርም ያስፈልጋል። አንዳንድ ሴቶች ነብሰ ጡር መሆናቸውን የሚጠራጠሩ ከሆነ ለሐኪም መንገር ተገቢ ነው። የኤም አር አይ ምርመራዎች ማግኔት ያላቸውና ብረት ነገሮችን የሚስቡ በመሆናቸው በሰውነት ውስጥ በሕክምናም ይሁን ለሌላ ነገር ብረት ነክ ነገሮች የተቀበሩላቸው ሰዎች ለሐኪሞች ቀርበው መናገር አለባቸው። የጭንቅላት፣ የልብ ሕክምና ተደርጎልኛል። ውስጥ የተቀመጠ ነገር አለ ማለት አለባቸው።

በነፃ ለሚደረጉ ምርመራዎች አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በገቢ ዝቅተኛ እንደመሆኑ መጨናነቆች ይፈጠራሉ። ስለዚህ ሰዎች ምርመራውን ካገኙ በኋላ በተለያዩ መንገዶች ባሉበት ቦታ ውጤት እንዲደርሳቸው ማዕከሉ ይህንን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት። አብዛኛው ሰው የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚ እንደመሆኑ ውጤታቸውን ባሉበት ቦታ ሆነው እንዲደርስና ተመልሰው እንዳይመጡ ይህን የሶሻል ሚዲያ ፕላትፎርም መጠቀም ይገባል።

በጤና ሚኒስቴር የሚንስትሯ ከፍተኛ አማካሪ ዶክተር አስቻለው ወርቁ እንደሚሉት አንድ ሰው ጤናማ ሆኖ ለመኖር ሲያስብ ቅድመ ጤና ምርመራ ሊያደርግ ይችላል። አመጋገቡን ሊያስተካክል ይችላል። የአካል ብቃት እንቅስቃሴም ያደርጋል። በውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከል እየተከናወነ ያለው የጳጉሜን ለጤና ነፃ የምርመራ ዘመቻ ይህን ያጠናክራል፤ በጎ ተግባርም ነው።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት በተጠናከረ መልኩ መሰጠት ከጀመረ ስድስት ዓመታትን አስቆጥሯል። የበጎ ፍቃድ ሥራ ከሚከናወንባቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ጤና ነው። በጤናው ዘርፍ በየዓመቱ በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች በወጣቶችና፣ ባለሀብቶችና በሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ይከናወናሉ። ባለፉት ስድስት ዓመታትም ሆስፒታሎችን የማደስ፣ ታካሚዎችን የማገዝ፣ ሐኪሞችን የመደገፍ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። ውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከልም መንግሥት በሚጠራቸው የተለያዩ የጤና የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ላይ በንቃት ሲሳተፍ ቆይቷል።

ጤና ሚኒስቴርም ይህንኑ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሥራ በስፋት እያከናወነ ይገኛል። በተለይ በክረምት ወቅት በየዓመቱ የልየታ ሥራ ይሰራል። የታመሙትን ያክማል። ትምህርት ይሰጣል። ችግኝ ተከላ ያካሂዳል። በዚህ ዓመት ደግሞ ሁለት ባለሞያዎችን ለሙከራ ከውጭ ሀገር በማስመጣት ጳውሎስ፣ አለርትና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች ውስጥ ውድ የሆኑና በሀገር ውስጥ በቀላሉ ሊሰጡ የማይችሉ ሕክምናዎችን በበጎ ፍቃደኞች የሕክምና መሳሪያውንም ሆነ ክህሎቱን ይዞ በመምጣት ሥልጠናና የሕክምና አገልግሎት ሰጥተው ተመልሰዋል።

አሁን ደግሞ 16 አባላት ያሉት የልብ ቀዶ ሕክምና ባለሞያዎች መጥተው 90 ለሚደረሱ የልብ ህመም ላለባቸው ታካሚዎች ነፃ የልብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት ሰጥተዋል። ስለዚህ የጤና በጎ ፍቃድ አገልግሎቱ እየሰፋ መጥቷል። ጤና ሚኒስቴርም ይህን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በይበልጥ አጠናክሮ አስቀጥሏል። በሌላ በኩል ደግሞ የተበላሹ የሕክምና እቃዎችን ሜዲካል ኢንጂነሮችን ከህንድ ሀገር በማስመጣት የማስጠገን ሥራዎች ተከናውነዋል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት



የኮሪደር ልማት ከፊል ገጽታ

# ሕዝብን የማገልገል ኃላፊነት በውጤትና በስኬት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ቀደምት ታሪክ ካላቸው ሀገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች። የራሷ ባሕል፣ ወግ፣ ልምድ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ባሕል እና የዘመን አቆጣጠር ያላት የተለየች ሀገር ናት። በተለይም በዘመን አቆጣጠሯ ለየት ባለው የ13 ወር ጸጋዋ ትታወቃለች። ይህም የክረምት የበጋ ባለጸጋዋን ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ብሎም በዓለም ካሉ ሀገራት በሙሉ ልዩ ያደርጋታል።

የኢትዮጵያውያን ብቻ የሆነችው 13ኛዋ ወርሃ ጳጉሜን በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ስድስት ቀናት ሲኖራት ከዛው ውጭ ግን አምስት ቀናት ያሏት ትንሿ ወር ናት። የክረምቱን መጠናቀቅ አብሳሪ ለአዲሱ ዓመት መግባት ደግሞ ድልድይ የሆነችው ጳጉሜን በተለያዩ ስያሜዎች ተቀብሎ ማክበር ከተጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። ዘንድሮም አሮጌው ዓመት አልፎ ወደ አዲሱ ዓመት የምታሸጋግረን ወርሃ ጳጉሜን ተራዋን ጠብቃ መጥታለች። ታዲያ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ የጳጉሜን ቀናት በተለያዩ ስያሜዎች ተወክለዋል።

በዚሁ መሠረት ጳጉሜን አንድ የመሻገር ቀን "የመሻገር ጥሪቶች፤ የአዲስ ብርሃን ወረቶች"፣ ጳጉሜን ሁለት፣ የሪፎርም ቀን "ሪፎርም ለላቀ አገልግሎት"፣ ጳጉሜን ሶስት የሉዓላዊነት ቀን "ኅብር ለሁለንተናዊ ሉዓላዊነት"፣ ጳጉሜን አራት የኅብር ቀን "ኅብራችን ለሰላማችን"፣ ጳጉሜን አምስት የነገ ቀን "የዛሬ ትጋት፤ ለነገ ትሩፋት" በሚሉ ስያሜዎች አምስቱ የጳጉሜን ቀናት ተሰይመዋል።

በመሆኑም ዛሬ ጳጉሜን 2 ቀን 2016 ዓ.ም የሪፎርም ቀን "ሪፎርም ለላቀ አገልግሎት" በሚል መሪ ሃሳብ ቀኑ ሲታሰብ ትኩረታችን በለውጡ መንግሥት በስኬትና በውጤት የተከናወኑ ተግባራትን በመዳሰስ ይሆናል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ ሥልጣን ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በውጭ ግንኙነትና በማኅበራዊ ጉዳዮች መጠነ ሰፊ ማሻሻያዎችን ለማድረግ በገቡት ቃል መሠረት ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል። በሪፎርም ሥራዎቻቸው መሠረትም በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በማህበራዊ ዘርፍ መሻሻሎችና አዳዲስ ለውጦች ተመዝግበዋል። በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ ሰው ተኮር የሆኑ ሥራዎችን ሰርተው በማሰራት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል። ሰው ተኮር ከሆኑ ሥራዎቻቸው መካከልም ማዕድ ማጋራትና የአቅመ ደካሞችን መኖሪያ ቤት ማደስ ተጠቃሽ ናቸው።

ማዕድ ማጋራትን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለሕዝቡ እንካችሁ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በተለይም ያዘመሙ የአቅመ ደካማ እናቶችን ጎጆ በማቅናት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ሥራዎችን ሰርተው አሰርተዋል። በዚህም ጥቂት የማይባሉ አቅመ ደካማ እናቶችም ካቀረቀሩበት ቀና ብለው በብዙ ተስፋ ተሞልተዋል። በእርሳቸው ተነሳሽነት የተጀመረው የበጎ ፈቃድ አገልግሎትም ዛሬም ድረስ ቀጥሏል። በመሆኑም የሀገሪቷ ዋና ከተማ ከሆነችው አዲስ አበባ ከተማ አልፎ በክልል ከተሞች ጭምር ባሕል ሆኖ መቀጠል የቻለ ተግባር ነው።

ኢትዮጵያ በበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች እየተፈተነች የመጣችና አሁንም በብዙ ፈተና ውስጥ እያለፈች ቢሆንም፤ በመንግሥት መሪነት ከፈተናዎቿ ጋር እየታገለች ትርጉም ያለውና ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ሥራዎችን እየሰራች ትገኛለች። ለዚህም መንግሥት የአንበሳውን ድርሻ ሲወስድ ሕዝቡም የላቀ ድርሻ አለው። ወደ ሥልጣን በመጡ ማግሥት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳታፊ ሆነው ትርጉም ያለው ሥራ እየሰሩ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ በተለይም የአቅመ ደካማ እናቶችን ቤት የማደስ ሥራን በቋሚነት በመያዝ ላለፉት ስድስት ዓመታት ያዘመሙ ጎጆዎችን በአዲስ ቀይረዋል።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተነሳሽነት የተጀመረው በጎ ተግባርና አገልግሎት በሌሎችም ተጋብቶ በተለይም ከተማ አስተዳደሩ በበጀት ዓመቱ የግል ባለሀብቶችን እንዲሁም ተቋማትን ጭምር በማስተባበር ማዕድ በማጋራትና የአቅመ ደካማ ዜጎችን ደሳሳ ጎጆ በማቅናት ትርጉም ያለው ሥራ ሲሰራ ቆይቷል። በመሆኑም ከተማ አስተዳደሩ በኑሮ ውድነትና በቤት እጦት የሚሰቃየውን ሕዝብ በሚችለው ሁሉ ለማገልገል ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በጥረቱም የሕዝቡን ተስፋ በማለምለም በርካታ የልማት ሥራዎችን በውጤትና በስኬት ማጠናቀቅ ችሏል።

መንግሥት ከመደበኛ ሥራው በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ ጥቂት ወራት ውስጥ ጀምሮ በስኬት ካጠናቀቃቸው የልማት ሥራዎች አንዱ የኮሪደር ልማት ተጠቃሽ ነው። በኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስ የማድረግ ራዕይን ሰንቆ በርካታ አገልግሎቶችን ለሕዝቡ በማቅረብ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል። ለከተማዋ ውበትን በማጎናጸፍ እውነትም ‹‹አዲስ አበባ›› ያስባለው ይህ የኮሪደር ልማት አንዱና ዋነኛው ለሕዝብ የተሰጠ አገልግሎት ነው። መንግሥት በኮሪደር ልማት እየሰራ ያለው ሥራ ለትውልድ የሚተርፍ ዘመን ተሻጋሪና ድንቅ ሥራ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ከቢሮ እስከ ከተማ አለፍ ሲልም እስከ ሀገር በሚል መርህ ኢትዮጵያን መቀየርና ገጽታዋን ማሳደግ ከሀገራዊ ለውጡ ማግስት የተጀመረ የመንግሥት ዋንኛ ተግባር ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀገር የመምራት ኃላፊነታቸውን እንደተረከቡ ቅድሚያ የሰጡት ታሪካዊውን ጽሕፈት ቤታቸውን መቀየር ሲሆን፤ ከዛም በገበታ ለሸገር በሚል ፕሮጀክቶች አዲስ አበባን ያስዋቡ ዋና ዋና ፕሮጀክቶችን ገሃድ አውጥተዋል። ገበታ ለሀገርና ገበታ ለትውልድ በሚል ሀገራዊ ገጽታን በያዙ ፕሮጀክቶችም እንዲሁ አዲስ አበባን ማስዋብ ሥራ አበረታች ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል።

የኢትዮጵያን ገጽታ ማየት የሚቻልባት አዲስ አበባ ክብርና ሞገሷ ሞልቶ ለኢትዮጵያ ተምሳሌት እንድትሆን፤ በኮሪደር ልማት ገጽታዋ እንዲዋብና በዚህ እሳቤም ስሟ ግብሯን እንዲመጥን ታጭታ ተሞሽራለች። ለዚህም በከተማዋ በተመረጡ አምስት የኮሪደር መስመሮች የልማት ሥራው በስኬት ተጠናቅቋል። ከሶስት እስከ አራት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የተሰራው ሥራም ከተማዋን እንደ ስሟ አዲስ ማድረግ የቻለና ብዙዎችን ያስደመመ ነበር። ታጭታ ለተሞሸረችው አዲስ አበባ ድል ያለ ድግስ የደገሱ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ ነዋሪዎቿም የነበራቸው አበርክቶ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

ከሰሞኑም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በከተማዋ በመጀመሪያው ዙር ለተከናወነው የኮሪደር ልማት ስኬቶች አስተዋጽኦ ላደረጉና ለተሳተፉ አካላት ዕውቅና ሰጥተዋል። ታጭታ ለተሞሸረችው አዲስ አበባ ከተማ በመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት ስኬት የተጉና የተሳተፉ አካላት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ዕውቅናን አግኝተዋል። ዕውቅና ካገኙት መካከልም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤን ጨምሮ በየደረጃው ያሉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የኮሪደር ልማቱ አስተባባሪዎች ይገኙበታል።

በኮሪደር ልማቱ ስኬት ተሳትፎ የነበራቸውና ዕውቅና የተቸራቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ካለፈው ትምህርት ወስደው በቀጣይም የበለጠ ማገልገልና ስኬት ማስመዝገብ የሚጠበቅባቸው መሆኑን ያሳሰቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ የኮሪደር ልማት እሳቤ ሕዝብን ለመጪው ዘመን ማዘጋጀትና መጪውን ዘመን ለሕዝብ ማዘጋጀት እንደሆነ ነው የተናገሩት። እሳቸው እንዳሉት፤ የኮሪደር ልማት ዋነኛ ዓላማና እሳቤ ሕዝቡን ለመጪው ዘመን ማዘጋጀትና መጪውን ዘመን ለሕዝቡ ማዘጋጀት ነው። አሁን ያለው ሕዝብ ለመጪው ዘመን መዘጋጀት አለበት። መጪው ዘመንም ከተሜነት የተስፋፋበት፣ ቴክኖሎጂ ያደገበት፣ የሰው ልጅ ክብር የሚያገኝበት ሥራ ውሎ ወደ ቤቱ ሲመለስ ከነበረበት ከባቢ ወጥቶ በሚሄድበት ከባቢ አዳዲስ ነገሮችን እያየና ከተፈጥሮ ጋር እየተስማማ ማረፍ ቢያስፈልገው እያረፈ በሰው ልጅ ክብር ልክ እየተጸዳዳ የሚንቀሳቀስበትን ከተማና ከባቢ መፍጠር የመጪው ዘመን ትልም ነው።

ያ ትልም ለዚያ የሚመጥን ሰዎችን አብሮ ማዘጋጀት ይፈልጋል። የእግረኛ መንገድን ለይቶ መጓዝ የሚችል፣ መኪኖች ለሰው ልጅ ቅድሚያ የሚሰጡ፣ ለእግረኛ ቅድሚያ የሚሰጡ፣ ሥርዓትና ሕግ የሚያከብሩ እንዲሆኑ አድርጎ መቅረጽ፣ ውኃን ዛፍን፣ ንጹሕ ከባቢን በከተማችን ማየት መጠበቅ የሚያስችል ባሕል መገንባት ያስፈልጋል። የኮሪደር ልማቱ ከዚህ አንጻር የእሳቤው መሠረት ሕዝቡን ለመጪው ዘመን ማዘጋጀት፤ ዘመንን ደግሞ ለሕዝብ ማዘጋጀት ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በምርጫ እምነት አሳድሮ ይሁንታውን የሰጠው አስተዳደር ከተማዋን የማልማትና ለኑሮ ምቹ የማድረግ ኃላፊነቱን ከዚህም በላይ በመወጣት መሥራትና ሕዝቡን ማገልገል እንዳለበት አሳስበዋል። ‹‹ሕዝቡ መንግሥትን አምኖ ለሰጠው ይሁንታ አሁን የተደረገው አገልግሎትና የተሰራው የኮሪደር ልማት ሥራ ያንስበት ከሆነ እንጂ አይበዛበትም›› በማለት መንግሥት ሕዝቡን ለማገልገል በቁርጠኝነት እየሰራ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

የመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት በስኬትና በውጤት ተጠናቅቆ ለነዋሪዎች አገልግሎት እየሰጠ ባለበት በዚህ ወቅት ሁለተኛው ዙር የኮሪደር ልማት መጀመሩንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብስረዋል። አጠቃላይ የመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት አሀዛዊ መረጃን በሚመለከት ከፒያሳ ዓድዋ ድልድይ ተነስቶ ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚወስደው የመንገድ ኮሪደር ልማት አጠቃላይ ከ48 ኪሎ ሜትር በላይ የተሽከርካሪ መንገድ፣ 96 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገድ፣ 100 ኪሎ ሜትር የብስክሌት መንገድ፣ አራት የመሬት ውስጥ እግረኞች መንገድና አጠቃላይ ከ240 ኪሎ ሜትር የመንገድ መሠረተ ልማቶች ተሰርተዋል።

ከዚሁ ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዘው የተሰሩ የሕዝብ መዝናኛ ሥፍራዎችንና የመዝናኛ አማራጮችም እንዲሁ በተለያዩ አካባቢዎች ተሰርተው ለነዋሪዎች አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። አጠቃላይ መዲናዋ በኮሪደር ልማቱ 32 የውሃ ፏፏቴዎች ወይም ደግሞ ፋውንቴኖች፣ የተቀናጀ የወንዝ ልማት እየተከናወነባቸው ያሉ ስምንት ወንዞች፣ 120 የሚደርሱ የመንገድ ዳር መጸዳጃዎች እና አጠቃላይ 70 የሚደርሱ የሕዝብ መናፈሻ ሥፍራዎች አግኝታለች። ከእነዚህ በተጨማሪም ለከተማዋ ድምቀት የሆኑ ዘመናዊና የደህንነት ካሜራ የተገጠመላቸው የኤሌክትሪክ መስመሮች ጭምር ተዘርግተውላታል።

ከተማዋ በአሁን ወቅት የመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት አጠናቅቃ ወደ ሁለተኛው ዙር የተሸጋገረች ሲሆን፤ ከመጀመሪያው ዙር የኮሪደር ልማት ልምድና ዕውቀት በመቅሰም የተሻለ ሥራ መሰራት እንዳለበት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስተዋል። ሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት አንደኛው መነሻውን ካዛንቺስ አካባቢ በማድረግ ከቤተ መንግሥት ጀምሮ፣ አቧሬ፣ መስቀል አደባባይ ሜክሲኮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ዓድዋ ድል መታሰቢያ የሚመለስ ይሆናል። ይህ የኮሪደር ልማት ሥራ ቀደም ሲል ከተሰራው የኮሪደር ልማት ሥራ ጋር እንዲናበብ በማድረግ ተጨማሪ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን የሚያከናውን እንደሆነ መረጃው ያመላክታል።

ሁለተኛው ከሳወዝጌት- መገናኛ፣ ከመገናኛ-መስቀል አደባባይ ሲሆን ሶስተኛው ከጣልያን ኤምባሲ ጀምሮ፣ ግንፍሌ፣ ቀበናንና አቧሬን የሚያካትት የወንዝ ዳርቻ ልማት ይሆናል። አራተኛው ከአዲስ አፍሪካ ኮንቬንሽን ሴንተር- ጎሮ የሚደርስ ነው። ሌላው ከአራት ኪሎ በሽሮሜዳ እንጦጦ - ጉለሌ እጽዋት ማዕከል የሚደርስ ይሆናል። አጠቃላይ እነዚህን የኮሪደር ልማቶች ከመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ጋር የሚተሳሰሩ ሲሆን ልማቱ የከተማዋን ገጽታ ከፍ በማድረግ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል። ለዚህም ሥራውን በኃላፊነት የሚመሩት የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የመጀመሪያውን የኮሪደር ልማት በስኬትና በውጤት እንዳጠናቀቁ ሁሉ ሁለተኛውን ምዕራፍም እንዲሁ በስኬትና በውጤት እንደሚያጠናቅቁ ይጠበቃል።

በመጨረሻም ኢትዮጵያውያን ከዘመን ዘመን እየተሸጋገሩ ያለው በአንድነት፣ አብሮነትና በመተሳሰብ እንደመሆኑ አዲሱ ዓመትም አንዳችን ለአንዳችን ደጀን የምንሆንበት፣ አንዳችን ሌላውን የምናገለግልበት፣ የምንከባበርበትና የምንደማመጥበት የሰላም፣ የፍቅርና የብልጽግና ዓመት እንዲሆን እየተመኘን በዚሁ አበቃን ሰላም!

# ተናጋሪው ዶሴ

# የቅናት በቀል

**ምሕረት ሞገስ**



ዝናቡ ያለማቋረጥ እየዘነበ አካባቢውን ከማረስረስ አልፎ አጨቅይቶታል። ዝናብ እና ብርዱ ቆፈን ያስያዘው ታደሰ መላኩ፤ ክረምቱን እንደለመደው ደጃኔ ግሮሰሪ ሄዶ በማርታ እቅፍ ውስጥ ለማሳለፍ አሰፍስፏል። በሐምሌ 05 ቀን 2015 ዓ.ም ታደሰ አዘውትሮ ወደሚመላለስበት በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ልዩ ስሙ አረቄ ሠፈር ተብሎ ወደሚጠራው መንደር ገባ።

ደጃኔ ግሮሰሪ ሲደርስ ማርታ በፈገግታ ተቀበለችው። ማርታ ቀጠን ያለች ዓይነ ትልልቅ ለግላጋ ወጣት ናት። ማርታ እና ታደሰ አብረው ቁጭ ብለው እየጠጡ መጨዋወት ጀመሩ። እየመሸ ሲሔድ ወደ ግሮሰሪው የሚገባው ሰው ቁጥር ጨመረ። ጫጫታውና ሁካታው ደመቀ። ማርታ ለአሥር ደቂቃ ከታደሰ ጋር ከተቀመጠች፤ ተነስታ ደግሞ ለሃያ ደቂቃ ሌሎች ሰዎችን እየታዘዘች እና እያነጋገረች ዞር ዞር ብላ ወደ ታደሰ መለስ ትላለች። ታደሰ የማርታ መለስ ቀለስ ማለት ብዙ አላሳሰበውም፤ አብራው እንደምታድር ርግጠኛ ነው።

ታደሰ እየጠጣ ሞቅ እያለው ቢሔድም፤ መጠጡን ከመደጋገም ይልቅ ከማርታ ጋር ከግሮሰሪው እስከሚወጣ ቸኩሏል። የማርታ ወጣትነት እና ውበት እየሳባቸው ታደሰ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የግሮሰሪው ተጠቃሚዎች አብረዋት እንዲያድሩ እየጠየቋት ነው።

**የወጣቷ ሕይወት**

ማርታ ሥራውን እንደጀመረች ከአንድ ወንድ ጋር እሺ ካለች፤ ለሌሎቹ ወንዶች ተይዣለሁ የሚል መልስ ትሰጣለች። ለሁሉም ያላት ስሜት ተመሳሳይ ነው። ሥራ ሆኖባት እንጂ ለየትኞቹም ፍቅር የላትም። አንዳንዴ አብረን እንሁን አብረሽን ተቀመጪ ሲሏት ይቀፋታል። ነገር ግን ዕጣ ፈንታ ሆኖባት ከቀፈፉዋት ሰዎች ጋር አብራ አንሶላ ትጋፈፋለች።

ሳትወድ ሕይወት አስገድዷት የገባችበትን ሥራ አትወደውም። እንደውም የሰዎች ጭካኔ እና ግፍ እያንገፈገፋት የእርሷም አመል ተቀይሯል። አሁን አሁን ወደ ሥራው የገባችው ለገንዘብ ስትል በመሆኑ፤ ከፍተኛ ገንዘብ የሰጣትን ሰው አስቀድማ ታገለግላለች። በርግጥ አንዳንዶች ከስሜታቸው ማብረጃነት አልፈው ፍቅር ውስጥ መውደቃቸውን ቢነግሯትም አታምናቸውም። ነገር ግን ለሁሉም ጥርሷን እያሳየች፤ ‹‹አይደል›› ትላለች።

ከታደሰ ጋር ከተዋወቁ ረዥም ጊዜ አስቆጥረዋል። ደጋግሞ በፍቅሯ እንደወደቀ ቢነግራትም አላመነችውም። እርሱም አንድ ወንድ አንዲት ሴትን ሲወድ ማድረግ ያለበትን እያደረገላት አይደለም። ባለው አቅም ሊያኖራት እና ከሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ሊያላቅቃት ጥረት ሲያደርግ አይታይም። እንደሌሎቹ ወንዶች ሁሉ ሲፈልግ ይመጣል። አብሯት ያድራል። በዚህ ምክንያት ማርታም ታደሰን ከሌሎች ወንዶች ለይታ አታየውም። አንዳንዴ ‹‹ እወድሻለሁ›› ሲላት ግን እንደሌሎቹ ወንዶች ጥርሷን አታሳየውም፤ እንደውም ትበሳጭበታለች።

ታደሰ በበኩሉ ምንም እንኳ ማርታን ከሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ባያወጣትም ደጋግሞ እንደሚወዳት ይናገራል። ነገር ግን ደፍሮ ሊያገባት አይፈልግም። ከእርሷ ጋር ትዳር መስርቶ ልጆች ለመውለድ ድፍረቱን አጣ። ስለዚህ እርሷን ከሌሎች ጋር እየተጋራ መኖርን መረጠ። በሐምሌ 3 ቀን 2015 ዓ.ም እንደለመደው ታደሰ ማርታ ጋር ሲሔድ ገንዘብ ፈልጋ ስለነበር በደስታ ተቀበለችው። አብረው ለማደር ተስማሙ።

**አታሳይዋ**

ታደሰ ‹‹አብረን እናድራለን›› ሲላት፤ እሺታዋን ገልፃለታለች። ነገር ግን ከታደሰ ጋር አብራ ለማደር ብትስማማም፤ በየመሃሉ ከታደሰ ጠረጴዛ ርቃ ወደ ሌላ ጠረጴዛ ስትሔድ ከፍተኛ ገንዘብ የሚከፍል ደንበኛ አገኘች። አላቅማማችም ከዚህኛው ጋርም አብራ ለማደር ተስማማች። ሁለቱም ጠረጴዛ ላይ ወዲያ እና ወዲህ እያለች ቀኑ መሸ። ሶስት ሰዓት ሲሆን፤ ለታደሰ አልጋ ቤት እንዲከራይ መከረችው። እንደነገረችው ሔዶ እዛው ከደጃኔ ግሮሰሪ ብዙም ሳይርቅ አልጋ ቤት ተከራየ።

ማርታ ታደሰን አታላ ከፍተኛ ብር ሊከፍላት ከተስማማው ሰው ጋር ከግሮሰሪው ወጣች። ታደሰ አልጋ ቤት ተከራይቶ ወደ ደጃኔ ግሮሰሪ ሲመለስ ማርታ የለችም። ምንም እንኳ ቢጠራጠርም ቁጭ ብሎ ጠበቃት። ማርታ ብቅ ብላ አልታየችውም። ደጋግሞ ስልክ ቢደውልላትም ስልኳ አይሠራም። ቁጭ ብሎ መጠጣቱን ቀጠለ። ትመጣለች ብሎ ቢጠብቅም ማርታን ማግኘት አልቻለም። እየጠጣ ከመስከር ይልቅ፤ እየተናደደ መብሰክሰክ ጀመረ።

የማርታን ጓደኛ አስጠርቶ የት እንደሔደች ጠየቀ። ጓደኛዋ ከሌላ ወንድ ጋር መውጣቷን ነገረችው። እርሱ ሌሊቱን አጋምሶ እየጠበቃት ከሌላ ወንድ ጋር ለማደር መውጣቷ በጣም አበሳጨው። ተስፋ አልቆረጠም፤ ግሮሰሪው እስከሚዘጋ እስከ ሌሊት ስድስት ሰዓት ድረስ ቢቆይም ማርታ አልተመለሰችም።

እየተብሰከሰከ ብቻውን ሊያድር ወደ ተከራየው አልጋ ቤት አመራ። የተከራየው አልጋ ቤት ሄዶ ዕንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር በንዴት ጨጓራው እየነደደ አደረ። ጠዋት ሶስት ሰዓት አካባቢ ከተከራየበት አልጋ ቤት ወጥቶ ወደ ደጃኔ ግሮሰሪ ሔደ። ማርታ መመለሷን ሲጠይቅ በእዛው ማደሯን እና ወደ ግሮሰሪው ተመልሳ እንዳልመጣች ተነገረው። ቀኑን ሙሉ እዛው አካባቢ ሲያንዣብብ ዋለ።

**የማርታ ዕጣ ፈንታ**

ታደሰ በማርታ መታለሉ እያንገበገበው ንዴቱ ሳይበርድለት ዋለ። 10 ሰዓት አካባቢ ወደ ግሮሰሪው መምጣቷን ሰማ። በጃኬቱ የግራ ኪሱ ውስጥ ቢላዋ ከቶ ወደ ደጃኔ ግሮሰሪ ገባ። በሰዓቱ ማርታ አላየችውም። ከአንድ ወንድ ጋር ቁጭ ብላ ስታወራ፤ እርሱ በቅርብ ርቀት ኮርነር ስር ተቀመጠ። ቢራ አዞ እየጠጣ ቆየ። ትንሽ ቆይቶ የሚጠጣውን ከቢራ ወደ አረቄ አስቀየረ። ማርታ ገና ስላልመሸ እና ብዙም ጠጪ ስለሌለ አብራው ከተቀመጠችው ሰውዬ ጋር ተመስጣ ታወራለች።

ታደሰ በደንብ ሞቅ ሲለው እጁን በጃኬቱ የግራ ኪስ ውስጥ ጨመረ። የቢላዋውን እጀታ አጥብቆ ይዞ ተነሳ። ማርታ ከደንበኛዋ ጋር ተጠግታ ስታወራ፤ ታደሰ የያዘውን ቢላዋ ከኪሱ አውጥቶ እያሳያት ፊት ለፊቷ ቆመ። ማርታ በድንጋጤ ከመቀመጫዋ ተነሳች፤ በያዘው ቢላዋ ሆዷን ወጋት። ማንም ሊከለክለው አልቻለም። ትከሻዋን፣ ደረቷን እና አገጯን ደጋግሞ በመውጋት እዛው ሕይወቷ እንዲያልፍ አድርጎ ሮጦ ወጣ። ታደሰ ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላ እየሮጠ ከአካባቢው ራቀ። ሊይዘው የሞከረ አልነበረም።

ማርታ ማንም ሳይከላከልላት ገና በወጣትነት ዕድሜዋ በአጭሩ ተቀጨች። ሰዎች ተጯጯሁ። ገሚሱ ‹‹ፖሊስ ይጠራ፤ ሞታለች ኡኡኡ....››፤ ሲል ገሚሱ፤ ‹‹ሐኪም ቤት... እንውሰዳት፤ አልሞተችም...›› እያሉ ተተራመሱ። ‹‹አትንኳት በኋላ ችግር ነው›› እየተባባለ ማንም ሳይጠጋት እንዲሁ ሲጯጯሁ በመሃል በአካባቢው የነበሩ ፖሊሶች ደረሱ። ታደሰ ከግሮሰሪው መሮጥ የጀመረ ጎሮ ፖሊስ ጣቢያ ሲደርስ ቆመ፤ ወደ ፖሊስ ጣቢያው ገብቶ እጁን ሰጠ።

**የፖሊስ ምርመራ**

በሐምሌ 03 ቀን 2015 ዓ.ም ከምሽቱ 11:30 ሲሆን፤ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ልዩ ቦታው አረቄ ሰፈር ደጃኔ ግሮሰሪ ውስጥ ወንጀል መፈፀሙን በአካባቢው በመዘዋወር ላይ የነበሩ ፖሊሶች ጥቆማ ሰጡ። የፖሊስ ምርመራ ቡድን ቦታው ላይ ሲደርስ የወጣት ማርታ ሕይወት አልፏል። የምርመራ ቡድኑ አስከሬኑን በጥንቃቄ በማንሳት ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ላከ።

በአካባቢው ከወንጀሉ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በሙሉ ሰበሰበ። በሰዓቱ ወንጀሉ ሲፈፀም የተመለከቱትን ሰዎች ስም እና አድራሻ መዘገበ። ፖሊስ ባካሔደው የማጣራት ሥራ ተጠርጣሪ ታደሰ መላኩ ነዋሪነቱ ኦሮሚያ ክልል ገላን ከተማ ሲሆን፤ የቤት ቁጥር አዲስ በሚል የተመዘገበ መሆኑን አወቀ። ሟች ማርታ በሴተኛ አዳሪነት እንደምትተዳደር አጣራ።

የምርመራ ቡድኑ ታደሰ መላኩ ሰውን ለመግደል በማሰብ የሴተኛ አዳሪነት ሥራ የምትሠራዋን እና የፍቅር ጓደኛው የሆነችውን ሟች ማርታ ታደሰን ጨካኝነቱን እና ነውረኛነቱን በሚያሳይ ሁኔታ ቢላዋውን በጃኬቱ በመያዝ ግሮሰሪ ከገባ በኋላ ሆዷን፣ ደረቷን፣ አንገቷን፣ ትከሻዋን እንዲሁም ክንዷን እና ፊቷን በተደጋጋሚ ወግቶ የገደላት መሆኑን የሚያሳውቅ ሙሉ ማረጋገጫ አገኘ።

የምርመራ ቡድኑ የወንጀሉን አፈፃፀም ሁኔታ የሚገልፁ እና ተጠርጣሪው መግደሉን በተመለከተ የሚመሰክሩ የ10 ሰዎችን ምስክርነት እንዲሁም ተጠርጣሪው ወንጀሉን እንደፈፀመ የሰጠውን የእምነት ክህደት ቃል አደራጀ። የሟች ማርታ ጓደኛ በሰጠችው የምስክርነት ቃል ላይ እንደተናገረችው፤ ሁለቱም አብረው ቆይተው አብረው እንደሚያድሩ ተነጋግረው ነበር። ይህንን ተከትሎ ታደሰ ደግሞ ግሮሰሪ አልጋ ተከራይቶ ሲጠብቃት፤ እርሷ ግን ወደ ሌላ ቦታ ሔዳለች። እየጠጣ ሲጠብቃት ቢያመሽም እንዳልመጣች እንዲሁም በዛ ተበሳጭቶ በማግስቱ መጥቶ በቢላዋ ወግቶ እንደገደላት ተናገረች።

ይህንን ምስክርነት እና ሌሎችም የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የአስክሬን የምርመራ ውጤትን እና ገላጭ ፎቶግራፎችን ጨምሮ የፖሊስ የምርመራ ቡድኑ ዓቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሠርት አስተላለፈ።

የዓቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያስረዳው ተከሳሽ ታደሰ መላኩ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 540ን ተላልፎ ተገኝቷል በማለት፤ የወንጀሉ መነሻ ከእኔ ጋር ለማደር ተስማምተሽ ለምን ጥለሽኝ ሄድሽ የሚል መሆኑን ጠቁሞ፤ ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ወንጀለኛ መሆኑን አረጋግጦ የቅጣት ውሳኔ እንዲያስተላልፍ ሲል ክስ መሰረተ።

## ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት የዓቃቤ ሕግ እና የተከሳሽ ታደሰ መላኩን ክርክር ሲያዳምጥ ቆይቶ በግንቦት 21 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት፤ ተከሳሽ ታደሰ መላኩ በሰው መግደል ወንጀል ጉዳይ ለቀረበበት ክስ ውሳኔ ሰጥቷል። ፍርድ ቤቱ ሕጉን እንዲሁም ክስ እና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ ተከሳሹን ያርማል ሌሎችንም ያስተምራል በማለት በ16 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ውሳኔ አሳለፈ።

መዝናኛ

## ማረፊያ/ ትዝብት

# መለወጥ (ሪፎርም) ማለት ምን ማለት ነው?

ዋለልኝ አየለ

በምሁራን ይተንተን ከተባለ ሰፊ ማብራሪያ እና ጥልቅ ትርጓሜዎች ሊኖሩት ይችላል። ለማንም ሰው ግልጽ በሆነ መንገድ በአጭሩ ይገለጽ ከተባለ ግን መለወጥ ማለት መሻሻል ማለት ነው። ከዘመኑ ጋር መሄድ ማለት ነው። ከኋላቀር አመለካከትና አሠራር ወደ ዘመናዊ አመለካከትና አሠራር መለወጥ ማለት ነው።

ዛሬ የ‹‹ሪፎርም›› ቀን ነው ተብሏል። ቃሉ የእንግሊዝኛ ሲሆን የተዋወቀው ከኢህአዴግ ጊዜ ጀምሮ ነው። በእንግሊዝኛ ሲሆን ምናልባት የተለየ ውበት እና ክብደት ያለው ሊመስለን ይችላል። በራሳችን ቋንቋ መለወጥ፣ መሻሻል፣ መዘመን... ማለት ነው። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ የመለወጥ ቀን እያልን እንቀጥላለን።

ይህ ቀን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን በጣም ያስፈልገናል። እንዲያውም በዓመት ቢያንስ ስድስት ጊዜ ቢከበር እና ቢታወስ ጥሩ ነበር። ምክንያቱም የሁሉም ችግሮቻችን መነሻው አለመለወጣችን ስለሆነ! ‹‹Re-form›› የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል እንደገና መሠራት፣ እንደገና መታደስ፣ እንደገና መመሥረት.... የሚል ትርጉም ይሰጠናል። በዚህ መሠረት ከሄድን በዋናነት የሚያገለግለው ለተቋማት ነው። ለመንግሥታዊ አደረጃጀት ነው። በተደጋጋሚ ከመንግሥት አፍ የምንሰማውም ለዚህ ነው። ያም ሆኖ ግን እንደ ኢትዮጵያ ደግሞ መለወጥ (reform) የሚያስፈልገን እንደ ግለሰብ ጭምር ነው። እንደ ግለሰብ ሲባል በዋናነት ታዋቂ ፖለቲከኞችንና ምሁራንን የያዘ ማለት ነው። እንደ መንግሥትም ሆነ እንደ ሕዝብ ለውጥ (ሪፎርም) ካላደረግን ወደ አደገኛ ችግሮች እየገባን ነው። ለውጥ ያላደረግንባቸውን ችግሮቻችንን እንታዘብ!

ዓለም ከሰው ልጅ መብት አልፎ የእንስሳትና ጥቃቅን ነፍሳት መብት ጥበቃ ላይ ደርሷል። የአውሮፓ ሀገራት በመካከላቸው ያለው ድንበር በአራዳ ክፍለ ከተማ እና በጉለሌ ክፍለ ከተማ እንዳለው ልዩነት ማለት ነው። አንድ ሰው ከአዲሱ ገበያ ወደ ፒያሳ ሲወርድ የጉለሌ ክፍለ ከተማን የት ጋ እንደጨረሰ እና አራዳ ክፍለ ከተማ ከየት ጋ እንደሚጀምር አያውቅም። የአውሮፓ ሀገራት ድንበር ልክ እንደዚያ እንደሆነ ብዙ የቆዩበት ሰዎች የጻፉትን አንብበናል፤ የተናገሩትን ሰምተናል። የታዛቢዎች አገላለጽ ተጋነነ ቢባል እንኳን በ21ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓ ሀገራት የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ እንዳልሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ለምን? ስለተለወጡ!

እኛ ግን እያሰብን ያለነው ስለአሁኑ እና ስለወደፊቱ ሳይሆን መቶ ምናምን ዓመታትን ወደኋላ ተመልሰን ነው። ከ200 ዓመት በፊት በነበረ ጉዳይ ዛሬ ላይ እየተጣላን ነው። ከዚህ በፊት እንዳልኩት፤ ከዛሬ 200 ዓመት በፊት ከነበረ አንድ የእኛ ሰፈር ሰውየ ዛሬ ላይ በሕይወት ያለ አንድ የሩቅ ምሥራቅ ሀገር ዜጋ ይቀርበኛል። ለምን? የጋራ ዘመን ላይ ነው ያለነው። መሐል ሀገር ለምኖረው ለእኔ ከ100 ምናምን ዓመታት በፊት ከነበረ አንድ የሰፈራችን ሰው የኢትዮጵያ ጫፍ ላይ ያለ የአሁኑ ሰው ይቀርበኛል። ምክንያቱም ብዙ የጋራ ጉዳይ አለን። እያደረግን ያለነው ግን ወደኋላ በመመለስ የዛሬውን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን ትውልድ ጭምር ሕይወት ማበላሸት ነው። ይህን አመለካከታችንን እስካልቀየርን ድረስ እንደ ሀገር ለውጥ (ሪፎርም) አይኖረንም።

ወደ ተቋማት አሠራር ስንሄድ ደግሞ በተደጋጋሚ እንደታዘብነው ዛሬም አሰልቺ እና አታካች አሠራር ላይ ነን። ምንም እንኳን የቢሮ ንጽህና እና ሌሎች ለዓይን ማራኪ የሆኑ አካላዊ ገጽታዎች ላይ ለውጥ ቢኖርም አሠራር ላይ ግን አሁንም ብዙ ነገር ይቀራል። ይህ ችግር ግን የተቋማቱ ብቻ ሳይሆን እንደ ማህበረሰብ ያልቀረፍነው የአመለካከት ችግር ስላለ ነው። ከዚህ በፊት በሌላ አጋጣሚ የጠቀስኩት አንድ ማሳያ ልጥቀስ።

ከዓመት በፊት ከፓስፖርት ጋር ለተያያዘ ጉዳይ ስመዘገብ ያጋጠመኝ ነው። ክፍያው በሞባይል ባንኪንግ ብቻ ነው። የሞባይል ባንኪንግ ክፍያ አገልግሎት ከተጀመረ ቆይቷል። እናም የምዝገባ ቦታው ላይ ክፍያው በዚህ አማራጭ ብቻ መሆኑ ሲነገር በጣም ሲቆጡ እና ሲደነፉ የነበሩ የተማሩ የሚባሉ ሰዎች ነበሩ። ለመብታቸው ተቆርቋሪ እና መብታቸውን አስጠባቂ መስለው ሲደነፉ ዓለም የደረሰበትን ደረጃ ግን አያውቁም ነበር ማለት ነው። የያዙት ስልክ ግን ከመቶ ምናምን ሺህ በላይ የሚገዛ ነው። ይህ እንደ ሕዝብ ያለብን የአመለካከት ችግር ነው።

በተቋማት በኩል ደግሞ፤ አንድ ነገር ‹‹እንደዚህ አድርጉ›› ተብለው ትዕዛዝ ከተሰጣቸው ‹‹ለምን? እንዴት?›› ብሎ መጠየቅ የሚባል ነገር የለም። ዝም ብለው ተቀብለው ‹‹ከላይ መጣ ትዕዛዝ ነው›› በማለት ተገልጋዩን ሕዝብ ማጉላላት ነው። ‹‹ኧረ ይሄ ነገር እንዴት ይሆናል? ምን ነክቷችሁ ነው? ይህ እኮ የለም?›› ሲባሉ ‹‹እኛ ምንም ማድረግ አንችልም ከላይ የመጣ ትዕዛዝ ነው›› በማለት ያደፋፍኑታል።

ከላይ ትዕዛዝ ሲመጣ፤ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ አገናዝቦ ‹‹ይህ በዚህ ይስተካከል›› ብሎ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል። ለሕዝቡ ከላይኛው አካል ይልቅ የታችኛው አካል ይቀርባልና የሚፈጸሙ እና የማይፈጸሙ ሁኔታዎችን መለየት አለበት። ቢቻል ቢቻል የላይኛው አካል የሚባለው ራሱ በጥናት የተደገፈ እና ሀገራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ቢሆን። ከታች ያለውን አካልም ሃሳብ እንዲሰጥ ዕድል ቢሰጥ፤ አለበለዚያ ብዙ ጊዜና ገንዘብ ባክኖ የተጀመረ አዲስ አሠራር ተግባራዊ ሳይሆን ከንቱ ሆኖ ይቀራል ማለት ነው።

የአመለካከት ለውጥ በሰፊው ያስፈልገናል። ለሁሉም ነገር መሠረት የሚሆነው የአመለካከት ለውጥ ነው። ቅንነት ሲኖር ነው። አለበለዚያ ስምን ማደስ፣ ስምን መለወጥ፣ ስምን ማሻሻል አይቻልም። አሁንም የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አሠራር ምሳሌ አድርገን እንታዘብ።

የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ እናውቃለን፤ ተቋማት ሁሉ ነገር የተሟላላቸው ላይሆን ይችላል። ቢያንስ ግን በራሳቸው የሚያዝዙበትን የአዕምሯቸውን ቅንነት ቢጠቀሙ ምን ችግር ነበረው? አንድ አገልግሎት ለማግኘት አስፈላጊ የሚባሉ ሰነዶችን ይዘን እንሄዳለን። የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ሲጠይቁን ግን በትህትና ሳይሆን በቁጣ ድምጸት ‹‹ምንድንትስ ያስፈልጋል!›› ልያዝ አልያዝ ሳያውቅ/ሳታውቅ ልክ እንዳልያዝኩ በሚመስል ድምጸት መናገር ለምን አስፈለገ? ይሄ ማለት አገልግሎት ሰጪው ‹‹አይቻልም!›› የሚባልበት ሰበብ ይፈልጋል ማለት ነው። ይሄ ስንፍና ብቻ ሳይሆን ተንኮል ጭምር ነው።

ለጉዳዩ የሚያስፈልገውን ነገር ሳላሟላ አገልግሎቱን ካላገኘሁ አልልም፤ ቢያንስ ግን አለማሟላቴን ካረጋገጡ በኋላ እንደማይቻል በትህትና መናገር ምን ይከብዳል? ግዴለም! ትህትናውንም ቢሆን ‹‹አንተን አልለማመጥም!›› ብሎ መተው ይቻላል፤ ቢያንስ ግን መቆጣት ያለበት/ያለባት አለመሟላቴን ካረጋገጡ በኋላ ነው። ለዚያውም እኮ ደግሞ ምን እንደሚያስፈልግ እንኳን በትክክል ሳይናገሩ ነው። በየጊዜው በሚቀያይሩት አሠራር ደንበኛውስ ቢሆን የሚያስፈልጉትን በሙሉ በምን ያውቃል?

በአጠቃላይ ሀገራዊ ለውጥ (ሪፎርም) የሚኖረን እንደ መንግሥትም ሆነ እንደ ሕዝብ ዘመኑ የደረሰበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አሠራር ሲኖረን ነው፤ ለዚህ ደግሞ ዘመናዊ አመለካከት ይኑረን!

## ዓለም አቀፍ



### ደቡብ ሱዳን አዲስ የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ለመገንባት ከቻይና ጋር ተስማማች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ደቡብ ሱዳን በኢትዮጵያ በኩል የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ለመገንባት ከቻይና ጋር ተስማማች። የተትረፈረፈ የነዳጅ ሀብት ካላቸው የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ የሆነችው ደቡብ ሱዳን ከዚህ በፊት ነዳጇን በሱዳን በኩል አድርጋ ለዓለም ገበያ ስታቀርብ ቆይታለች።

ሱዳን በእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መሆኗን ተከትሎ እስከ ፖርት ሱዳን የተዘረጋው የደቡብ ሱዳን ነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር በጦርነቱ ወድሞባታል። በዚህም ምክንያት ሀገሪቱ በኢትዮጵያ በኩል እስከ ጅቡቲ ወደብ ድረስ የተዘረጋ የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ለመገንባት ማቀዷ ተገልጿል።

በቻይና አፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ ላይ የተሳተፉት ፕሬዚዳንት ሳልቫኪር ማያርዲት በኢትዮጵያ በኩል እስከ ጅቡቲ ወደብ ድረስ የሚዘረጋ የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ግንባታ ዙሪያ መክረዋል።

ፕሬዚዳንቱ ከቻይና ብሔራዊ ነዳጅ ኮርፖሬሽን ሃላፊ ዳይ ሁሊያንግ ጋር በቤጂንግ መምከራቸውን የደቡብ ሱዳን ዜና አገልግሎት ዘግቧል።

እንደ ዘገባው ከሆነ የቻይናው ነዳጅ ኮርፖሬሽን ከደቡብ ሱዳን ተነስቶ በኢትዮጵያ በኩል አድርጎ ጅቡቲ ወደብ ድረስ የተዘረጋ የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ለመገንባት ፈቃደኛ የሆነ ሲሆን በግንባታ ወቅት ለሠራተኞች ደህንነት ጥበቃ እንዲደረግለት ጠይቋል።

ስምምነቱ ከነዳጅ ማስተላለፊያ ግንባታ ባለፈም አዲስ የነዳጅ ጉድጓድ ፍለጋንም እንደሚያካትት በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።

ደቡብ ሱዳን 90 በመቶ ኢኮኖሚዋ በነዳጅ ሽያጭ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የሱዳን እርስ በርስ ጦርነት በዚህ ገቢዋ ላይ ከፍተኛ የተባለ ጉዳት ማድረሱ ተገልጿል።




### በኬንያ አዳሪ ትምህርት በተከሰተ የእሳት አደጋ የ 17 ተማሪዎች ሕይወት አለፈ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በማዕከላዊ ኬንያ በአዳሪ ትምህርት ቤት በተማሪዎች ማደርያ ውስጥ በተቀሰቀሰ እሳት የ 17 ተማሪዎች ሕይወት አለፈ፡፡

ሂልሳይድ ኢንዳርሻ በተባለ የመጀመርያ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት የተከሰተው እሳት መንስኤ ላይ ምርመራዎች እየተደረጉ መሆኑን የገለጸው ፖሊስ የሟቾች ቁጥር ከዚህም በላይ ሊያሻቅብ እንደሚችል አስታውቋል፡፡

በአደጋው ሕይወታቸው ካለፈው ተማሪዎች ባለፈ 13 ሰዎች ከፍተኛ ቃጠሎ ደርሶባቸው ሆስፒታል ውስጥ እንደሚገኙ ቢቢሲ ዘግቧል፡፡ የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ አደጋውን አስከፊ እና አሳዛኝ ሲሉ ገልጸውታል፤ በአደጋው መንስኤ ዙርያም አፋጣኝ ምርመራ እንዲጀመር አዘዋል፡፡

በተጨማሪም ለእሳት አደጋው መከሰት ተጠያቂ የሚሆኑ ግለሰቦች ለፍርድ እንደሚቀርቡ ነው ያስታወቁት፡፡ የፖሊስ ቃል አቀባይ ርሲላ ኦንያንጎ በአደጋው ሕይወታቸው ያለፉ ተማሪዎች ለመለየት በሚያስቸግር ሁኔታ በቃጠሎው እንደተጎዱ ተናግረዋል፡፡

የኬንያ ቀይ መስቀል ማህበር በአደጋው ድንጋጤ እና ኀዘን ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ የተማሪ ወላጆች እና መምህራን ከሚገኙበት የሥነልቦና ጫና እንዲያገግሙ የኀዘን ጊዜ ማማከር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ሂልሳይድ ኢንዳርሻ የተባለው የመጀመሪያ ደረጃ የግል አዳሪ ትምህርት ቤት ከዋና ከተማዋ ናይሮቢ በሰሜናዊ አቅጣጫ 150 ኪሎሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ እድሜያቸው ከ5-12 የሚደርሱ ህጻናት ተማሪዎችን የሚያስተምር እንደሆነም ታውቋል፡፡

በኬንያ በአዳሪ ትምህርት ቤቶች የሚከሰቱ የአሳት አደጋዎች በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ሲሆን በ2017 በዋና ከተማዋ በሚገኝ የሴቶች አዳሪ ትምህርት ቤት በተፈጠረ አደጋ የ 10 ተማሪዎች ሕይወት ማለፉ ይታወሳል፡፡

በተመሳሳይ ከ20 ዓመት በፊት በደቡብ ምስራቅ ናይሮቢ በደረሰ ቃጠሎ 67 ተማሪዎች ሲሞቱ በሀገሪቱ ታሪክ አስከፊው የእሳት አደጋ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

# ለውጥ ከራስ ይጀምራል!



**አስናቀ ፀጋዬ**

ለውጥ አስፈላጊና ተፈጥሮአዊ ሂደት ቢሆንም ቀላል ደግሞ አይደለም። ሁሉም ነገር በለውጥ ሂደት ላይ ነው። በተፈጥሮ፣ በቴክኖሎጂ፣ በማህበራዊ ሕይወት፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በዕድሜ፣ በግንኙነት ወ.ዘ.ተ ለውጦች አሉ። ለውጥን ማስቀረት አይቻልም። በዚህ ክፍለ ዘመን በቴክኖሎጂና በሳይንስ ረገድ ብቻ ሳይሆን በሰው ልጆች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሕይወት ላይ ዘርፈ ብዙ፣ መጠነ ሰፊና እጅግ ፈጣን ለውጥ ከመካሄዱ የተነሳ ለውጥ ራሱ በሰዎች ዘንድ ምንነቱና ይዘቱ በሳይንሳዊ መንገድ እንዲጠና ግድ ብሏል።

በ2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ በርካታ የተቋም ግንባታና የሪፎርም ስራዎች ተከናውነዋል። እነዚህ ስራዎች ጅምር ቢሆኑም በአዲሱ 2017 ዓ.ም በስፋት አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል። ምክንያቱም ጠንካራ ተቋማት ሲገነቡና የሪፎርም ስራዎች በተጠናከረ ሁኔታ ሲከናወኑ ነው ሀገራዊ ብልፅግናን ማረጋገጥ የሚቻለው። ለዚህ ደግሞ ከግለሰብ እስከ ሀገር ድረስ ሁለንተናዊ ለውጥ ማድረግ ያስፈልጋል። ለውጥ ደግሞ ከራስ ነው የሚጀምረው። ግለሰብ ሲለወጥ ቤተሰብ ይለወጣል። ቤተሰብ ሲለወጥ አካባቢ ይለወጣል። አካባቢ ሲለወጥ ወረዳዎች ይለወጣሉ። ወረዳዎች ሲለወጡ ደግሞ ከተሞች ይለወጣሉ። ከተሞች ሲለወጡ ሀገር ትለወጣለች።

ስለዚህ ለውጥ ማለት ከተለመደው፣ ከታወቀው፣ ከኖረው ወዘተ አሰራርና ሁነት ወደ አዲስ፣ያልተለመደና እንግዳ ወደ ሆነ አሰራር፣ ሁነት ወዘተ የመቀየር ሂደት ነው። ለውጥ ሲታሰብ እና ተግባራዊ ሊደረግ ሲሞከር ሶስት አይነት አስተሳሰቦች ጎልተው ይወጣሉ። የመጀመሪያው አስተሳሰብ የለውጥ እንቅፋት በሆኑ የቀጣይ ሀገራዊና ከባቢያዊ ራዕይ በሌላቸው፤በነበሩ አሰራር ያለአግባብ ተጠቃሚ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የሚቀነቀን ለውጥ አያስፈልግም የሚል አስተሳሰብና አቋም (Reactionary force) ነው።

ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ በነባሩ ስርዓት አሰራሮችና የህጎች ማዕቀፎች እንዲሁም አጠቃላይ ሁለንተናዊ አካሄዶች ላይ ፍፁም ጥላቻ ባላቸው፣ ስልጣን የማግኘት ወይም የመጋራት እድል ካጋጠማቸውም ለበቀል በሚነሳሱ ኃይሎች በብዛት የሚቀነቀን አስተሳሰብ ሲሆን ለውጡ መሰረታዊና ስር-ነቃል (Revolutionary change) ሊሆን ይገባል የሚል ነው።

የዚህ አስተሳሰብ ዋነኛው ጉድለት ከነበሩ ስርዓት ምንም የሚጠቅም ነገር የለም ብሎ በጅምላና በጥላቻ እይታ ውሳኔ መስጠት ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው። ይህ አስተሳሰብ በአብዛኛው ገና ታዳጊ በሆኑ ሀገራት የሚዘወተር ነው። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሁለት ጊዜ ስር-ነቀል ለውጥ (Revolutionary change) በ1966 እና 1983 በመካሄዱ ብዙ ነገሮች ተፈጥረዋል።

ሶስተኛው አስተሳሰብ የበሰለና ያደገ አመለካከት ባላቸው የለውጥ ኃይሎች፣ሚዛናዊና አርቆ አሳቢ በሆኑ ዜጎች ፣ጥልቅ የፖለቲካ እውቀት ባላቸውና በተግባር በብዙ ነገር በተፈተኑ የለውጥ አራማጆች የሚቀነቀን አስተሳሰብ ነው። ለውጡ አስፈላጊና አይቀሬ መሆኑን የሚያምኑ ሲሆን ለውጡ ግን ስር- ነቀል (Revolutionary change) ሳይሆን ጥገናዊ (Reform) መሆን ይኖርበታል የሚሉ ናቸው።

እንደ ፖለቲካል ሳይንስ ተመራማሪዎች ለአንድ ሀገር አስተማማኝና ዘላቂ ሰላም እንዲሁም ልማት እንዲረጋገጥ ከተፈለገ ለውጥ ያስፈልጋል የሚለው አስተሳሰብ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። ለውጡ ግን ሁሌ እንደ ጭቃ ቤት አፍርሶ በመስራት ሳይሆን በቡሎኬት እንደተገነባ ቤት በፅኑ መሰረት ላይ ተገንብቶ አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ መሰረታዊ ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል በሚል አስተሳሰብ አብዛኞቹ ይስማሙበታል።

ከዚህ አንፃር ወደ ስልጣን የመጣው አዲሱ የለውጥ መንግስት ከዚህ በፊት በነበረው የኢህአዴግ መንግስት የተከናወኑ ስራዎችን ወደማፈራረስ አልገባም። ጥገናዊ ለውጥ ነው ያደረገው። ቀደም ሲል የነበሩ ጠንካራ ስራዎችን ተቋማዊ በማድረግና በማሻሻል ማስቀጠል ችሏል። በተቃራኒው የሀገርን እድገት የሚጎትቱና ወደኋላ የሚያስቀሩ አሰራሮችን በማስወገድ የተሻሉና ሀገራዊ ብልፅግናና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያስቀጥሉ ሪፎርሞችን አካሂዷል። በዚህም የሚታዩ ሁለንተናዊ ለውጦች መጥተዋል።

ስለዚህ አሁንም ቢሆን የተጀመሩ ተቋማዊ ግንባታዎችንና የሪፎርም ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠሉ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም። አሁንም ቢሆን ለኢትዮጵያ ለውጥ ያስፈልጋታል። ለውጥ ግን ከራስ ይጀምራል። መንግስት እንዲሁ በባዶ ሜዳ ተቋማዊ ግንባታና የሪፎርም ስራ ቢል ሰዎች በራሳቸው መለወጥ ካልቻሉ የታሰበው ሁለንተናዊ ሀገራዊ ለውጥ ሊመጣ አይችልም። ሰዎች እንዲለወጡ ደግሞ መንግስት የለውጥ አራማጅ ሆኖ ከፊት በመቅደም የለውጡን መንገድ ለዜጎች ማሳየት ይጠበቅበታል።

ለውጥ ሁሉም ነገር ባለበት እንደማይቀጥል ነገር ግን ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላው ደረጃ መሸጋገሩ አይቀሬ ነው። "የማይለወጥ ነገር ቢኖር ለውጥ ራሱ ነው" እንደሚባለው፣ ከለውጥ በቀር ሁሉም ነገር የሚለወጥ ነው። ለውጥ ባይኖር ሕይወት ትርጉም አይኖረውም። ሕይወትን አጓጊና አስደሳች የሚያደርገው ለውጥ በመኖሩ ነው። ስለዚህ ለውጥ የመኖር ተስፋ ነው። የለውጥ መኖር ሊፋቅ የማይችል ተፈጥሮአዊ ሕግ ቢሆንም ለውጥ ሁሉ ደግሞ ጠቃሚ ነው ማለት አይደለም።

አዎንታዊ ለውጥ የለውጡ መምጣት በኑሮአችንና በወደፊታችን ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አለው። አሉታዊ ለውጥ ደግሞ በኑሮአችንና በወደፊታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል። ስለዚህ አንድ ጤናማ ማህበረሰብ የሚፈልገው ለውጥን ብቻ ሳይሆን አዎንታዊ ለውጥን ጭምር ነው። ከዚህ አንፃር መንግሥት አሉታዊውን ትቶ አወንታዊውን ለውጥ አጠናክሮ ማስቀጠል ይኖርበታል። ሕዝብም ቢሆን አሉታዊ ለውጦችን በመንቀፍ መንግሥት የሚያደርጋቸውን አወንታዊ ለውጦችን መደገፍና ማበረታታት ይኖርበታል።

ሁሌም ቢሆን ለውጥ ውጤት አለው። ለውጥ ውጤት እንዲኖረው ግን መጀመር አለበት። ለውጥ ደግሞ የሚጀምረው ከራስ ነው። የተጀመረ ለውጥ ሂደት ውስጥ ይገባል። ውጤት ከጅማሬና ከሂደት በኋላ የሚመጣ ነው። ለውጥ በሚፈጠርበት ጊዜ ታዲያ ሦስት አይነት ቡድኖች ይኖራሉ። እነዚህም የለውጡ አራማጆች፣ የለውጡ ታዛቢዎችና የለውጡ ተቃዋሚዎች ናቸው። ማንኛውም ለውጥ እንዲህ ዓይነት ሦስት ቡድኖችን መፍጠሩ አይቀርም።

የለውጡ አራማጆች፤ ለውጡ ይመጣ ዘንድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉና ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ሁሌም ቢሆን ለመለወጥ ዝግጁ የሆኑና አዳዲስ ለውጥ ይመጣ ዘንድ ጥረት የሚያደርጉ ናቸው። ስለዚህ የለውጥ አራማጆች ሁሌም ቢሆን መንግሥት የሚያከናውናቸውን የሪፎርም ስራዎች የሚደግፉ ናቸውና ብዙም ችግር የሚፈጥሩ አይደሉም።

የለውጡ ታዛቢዎች የለውጡ አዎንታዊነትና አሉታዊነት ጥርት ብሎ ያልታያቸው፣ አቋም ለመያዝ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልጉ እንደመሆናቸው ስለለውጡ በቂ ግንዛቤ አግኝተው ከለውጡ ተራማጆች ጎን እንዲሰለፉ እያንዳንዱ የሪፎርምና የተቋም ግንባታ ስራ ግልፅና በተጠያቂነት መከናወን አለበት። የለውጡ ተቃዋሚዎች ደግሞ የለውጡ አሉታዊነት ያመዘነባቸው እንደመሆናቸው ሃሳባቸውን በመቀበል ከአሉታዊነት ወደ አወንታዊነት እንዲሸጋገሩ የለውጡን አሳማኝ ሃሳቦችን ማቅረብ ተገቢ ነው።

ህዝብ ምክንያታዊ ሲሆን ከለውጥ ደጋፊነት ወደ ለውጥ አራማጅነት ይሸጋገራል። ህዝቡ የለውጥ አራማጅ ሲሆን በለውጡ ውስጥ ያለውን ድርሻ በመለየት ራሱን በአዕምሮና በድርጊት አሳታፊ ያደርጋል። በርግጥ አሁንም ቢሆን ህዝቡ በቅድሚያ እንዲለወጥ የሚፈልገው ነገር ይኖራል። ነገር ግን በቅድሚያ ሕዝቡ በአስተሳሰብና በንቃተ ህሊና ራሱን መለወጥ እንዳለበት መገንዘብ ይኖርበታል። ህዝቡ ሳይለወጥ የሚለወጡ ነገሮች እንደሌሉ ሊያስብ ይገባል። ስለዚህ የሚለወጥ ነገር መኖሩን የምንናፍቀውን ያክል ቢያንስ በአስተሳሰብ ልንለውጣቸው የሚገቡ ነገሮች ሊታዩን ይገባል።

በኢትዮጵያ እየተካሄደ ባለው ሁሉን አቀፍ ለውጥ የጋራ መግባባት እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህ ለውጥ ከዳር እንዲደርስ እርስ በእርስ መስማማት ባይቻል እንኳን እርስ በእርስ መግባባት ግን ይገባል። ከመስማት ይልቅ መናገር እየቀደመን ወደ መግባባት ልንመጣ አንችልም። መስማት የመግባባት መሠረት ነው። ከመስማት ይልቅ መናገር ከቀደመ፣ ማን ማንን ሊሰማ ነው? ስለዚህ እንደ ሀገር የመስማት ባህላችን ሊጎለብት ይገባል። ብዙ ጊዜ ከሌሎች ጋር የማንስማማው ሳይገባን ነው። ባንስማማ እንኳን ገብቶን አንስማማ።

ይህንን የለውጥ ጊዜ ራሳችንንና አስተሳሰባችንን እያየን ለመለወጥ እንጠቀምበት። እኛ እስካልተለወጥን ድረስ እየተለወጠ ያለው ነገር ብዙም ዘላቂነት አይኖረውም። ‹‹ከሚሰማ ይልቅ የሚያዳምጥ ብፁዕ ነው›› እንደሚባለው መስማት ከመናገር ይበልጣል፤ ማዳመጥ ደግሞ ከመስማትም በላይ ነውና ከፍረጃና ለውጥን ከመኮነን በፊት አድማጭ መሆን ተገቢ ነው።

የፊዚክስና የማህበራዊ ሳይንስ ሊቁ ኩርት ሌዊን የለውጥ ሞዴልን በተመለከተ እ.ኤ.አ በ1940 ማቅለጥ - መለወጥ - ማቀዝቀዝ በሚል ያስቀመጠው ጠቃሚ የለውጥ ሞዴል ይጠቀሳል። ይህን ሞዴል ለማብራራት አራት ማዕዘን በረዶን ወደ ሦስት ማዕዘን ለመለወጥ ያለውን ሂደት መመልከት ይቻላል። በመጀመሪያ አራት ማዕዘኑ በረዶ እንዲቀልጥ ይደረጋል። ቀጥሎ በረዶው በቅርፅ መለወጥ ይችላል። ከዛ አራት ማዕዘኑን በረዶ በሦስት ማዕዘን ቅርጽ ይደረጋል። በረዶው ሶስት ማዕዘን ሆኖ እንዲቀር ግን እንደገና ማቀዝቀዝ ያስፈልጋል።

ይህንን ሞዴል የማኔጅመንት ኤክስፐርቶች በአንድ የቢዝነስ ወይም የድርጅት መዋቅር ላይ ለውጥ ለማምጣት ይጠቀሙበታል። እንደ ሀገርም እንዲቀልጥ የተደረገ ብዙ ነገር አለ። የቀለጠው ነገር ለለውጥ አመቺ የሆነ ከባቢ ፈጥሯል። የሕዝብ ስሜት መነሳሳት፣ የነበረው ተቃውሞና እንቅስቃሴ የነበረው ነገር እንዲቀልጥ አድርጎታል። ይህ መቅለጥ ደግሞ በሀገሪቱ ላይ ባልተለመደ ሁኔታ የአመራር ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል። በዚህ የአመራር ለውጥ አብዛኛው ሕዝብ ደስተኛ ነው። ነገር ግን ይህ ለውጥ ውጤታማ፣ የጸናና ከዳር የሚደርስ እንዲሆን ማቀዝቀዝ ያስፈልጋል። በተለይ አሁን የተጀመረው ሁሉን አቀፍ የሪፎርም ሥራ ወደኋላ እንዳይመለስ በተጠናከረ መልኩ መቀጠል አለበት። ተቋም የመገንባት ሥራውም እንደዛው።

ምናልባት ጥያቄው የቀለጠውን ማን ያቀዝቅዘው? የሚል ይሆናል። ስናቀልጥ የነበርን ሰዎች ሁሉ በማቀዝቀዙ ላይ ድርሻ ሊኖረን ይገባል እንጂ ይህንን የማቀዝቀዝ ሂደት ከመንግሥት ብቻ መጠበቅ አይገባም። ስለዚህ የተጀመረው የሪፎርም ሥራ ከዳር እንዲደርስ የሕዝቡን ያልተቆጠበ ድጋፍ ይፈልጋል። ከመንግሥት ሠራተኞችና ሹመኞች ደግሞ ሌት ተቀን ሥራ ይጠይቃል። ሌሎች ባለድርሻ አካላትም የሪፎርም ሥራውን ለማስቀጥል በየደረጃው ተሳትፏቸውን ማሳየት አለባቸው። ያኔ የሚታሰበውን ብልጽግና በኢትዮጵያ ማረጋገጥ ይቻላል!!

# ርዕሰ አንቀፅ

## የምንፈልገውን አገልጋይ ትውልድ ለመፍጠር

ሪፎርም በሀገራችን በተለያዩ ወቅቶች ብሔራዊ አጀንዳ የሆነ ርዕሰ ጉዳይ ነው። እንደ ሀገር አዳዲስ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ የለውጥ አስተሳሰቦች በመጡ ቁጥር አስተሳሰቦቹን በሕዝብ ውስጥ ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ በማስረጽ ለለውጡ ስኬት አቅም እንዲሆኑ ለማስቻል ከሚደረጉ ጥረቶች አንዱና ዋናው ነው።

በተለይም ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ሪፎርሞች፣ በሕዝብ ውስጥ ያሉ በአገልግሎቶች ያለመርካት ጥያቄዎችን በፍጥነት ለዘለቄታው ለመፍታት የሚደረጉ ስትራቴጂክ ጥረቶች ናቸው። ዋነኛ ግባቸውም ጥራት ያለው ፈጣን አገልግሎት በማቅረብ በአገልግሎት የረካ ተገልጋይ መፍጠር ነው።

ከዚህም ባለፈ መሠረታዊ የሆነውን የለውጥ አስተሳሰብ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ በመተግበር አስተሳሰቡ አካል ለብሶ እንዲያገኝ፣ በዚህም መላው ሕዝብ /የለውጡ ባለቤት/ በለውጡ ላይ አመኔታ ኖሮት ለውጡን የራሱ አድርጎ እንዲወስድ እና የሚፈለግበትን ድጋፍ እንዲያደርግ የሚያስችል የለውጥ ትግበራ አንድ ምዕራፍ ጭምር ነው።

በኢትዮጵያ መንግሥታዊ አገልግሎት መሰጠት ከጀመረ የረጅም ዘመን ታሪክ ያለው ነው፣ ይህም ሆኖ ግን አገልግሎቱ እስካሁን ድረስ በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ይገኛል። በየወቅቱ ችግሮቹን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችም የሚፈለገውን ያህል ውጤት ባለማምጣታቸው ከአገልግሎት አሠጣጥ ጋር የተያያዙ የሪፎርም ጉዳዮች ዛሬም ሀገራዊ አጀንዳነታቸው እንደቀጠለ ነው።

በርግጥ የሪፎርም ጉዳይ በሆነ ወቅት ተጀምሮ የሚያበቃ አይደለም፣ ቀጣይነት ባለው መንገድ የሚከወን ሁሌም አገልግሎቶችን በፍጥነት እና በጥራት ለአገልግሎት ፈላጊው ማድረስ የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶችን መፍጠርንና መተግበርን ያካተተ፣ እንደየዘመኑ ተለዋዋጭነት ያለው እና ዘመኑ ከሚጠይቀው አገልግሎት ጋር የሚታይ ነው።

አሁናዊው ዓለም ከደረሰበት የቴክኖሎጂ እና የእውቀት ደረጃ አንፃር አገልግሎትን ለተገልጋይ በተሻለ መንገድ የማድረስ ሁኔታ ስለመኖሩ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። በተለይም ቴክኖሎጂ በፈጠረው ቅርርቦሽ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ በሆነ መንገድ በዝቅተኛ ወጪና በአጭር ጊዜ ማቅረብ የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።

ሀገራችን የዚሁ ዓለም አቀፋዊ እውነታ አካል ከመሆኗ አኳያ፣ ተገልጋዮች ጥራት ያለው ቀልጣፋ አገልግሎት በፍጥነት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን ማከናወን ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል። በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተግባራዊ እየሆኑ ካሉ ሪፎርሞች አንዱ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ የሚደረገው ነው።

በለውጡ ማግስት የአገልግሎት አሰጣጥን በሁለንተናዊ መልኩ ለማዘመን የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎች ከፍ ባለ ሀገራዊ መነቃቃት ተጀምረዋል፤ እንደ ሀገር ካጋጠሙን ፈተናዎች አንጻር በተጀመሩበት ልክ ማስቀጠል ባይቻልም ተስፋ ሰጭ ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው።

ሀገራዊ አገልግሎት አሰጣጡ ውስብስብ በሆኑ ችግሮች ውስጥ ረጅም ዓመታትን ማስቆጠሩ በራሱ ችግሮቹን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶችን ፈታኝ አድርጓቸዋል። ከሁሉም በላይ በዘርፉ ሲደረጉ የቆዩ ሪፎርሞች መሠረታዊ የሆነውን የአስተሳሰብ ተሐድሶ ማምጣት ባለመቻላቸው፣ ችግሩን ለዘለቄታው መፍታት የሚያስችል አቅም መፍጠር አልተቻለም።

የሪፎርም ሥራዎች ስኬታማ ለመሆን ከሁሉም በላይ፣ የሪፎርም አስተሳሰቦች በአገልግሎት ሰጪው የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ ሰርጸው የአገልጋይነት ባሕሪ እንዲላበስ ሊያደርጉት ይገባል። ይህንን ባሕሪ መፍጠር ባልተቻለበት ሁኔታ በእውቀት፣ በቴክኖሎጂም ሆነ የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶች ተግባራዊ በማድረግ የሚያመጡት ለውጦች በራሳቸው ምሉዕ አይደሉም።

የአገልጋይነት መንፈስ መፍጠር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚገኝ እውቀት ብቻ እውን የሚሆን አይደለም። ይህን መንፈስ ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት ከአስተዳደግ ሥነ ምግባር ጋር አብሮ የሚታይ እና ሊሠራ እንዲሁም በማንነት ግንባታ ውስጥ አንድ ትልቅ አጀንዳ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ነው።

የአገልጋይነት መንፈስ የተገልጋይነት ሌላው ገጽታ መሆኑን እያወቀ ያደገ ትውልድ መፍጠር፣ በዘርፉ እያጋጠመን ያለውን ዓመታት ያስቆጠረ የገነገነ ሀገራዊ ፈተና መሻገር የሚያስችል ዘላቂ መፍትሔ ነው። ይህ በአገልጋይነት ባሕሪ የተገነባ ማንነት በሙያዊ እውቀት፣ በቴክኖሎጂ እና በተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶች ሲደገፍ የምንፈልገውን አገልጋይ ትውልድ መፍጠር እንችላለን። የአገልግሎት አሰጣጣችንም አርኪ ይሆናል።


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአገልጋይነት ባሕል ለመፍጠር

ሰው መሆን

የአንድን ሀገር እድገት ወደኋላ ከሚጎትቱ ጉዳዮች መካከል የቢሮክራሲ ጥራት መጓደል ዋንኛው ምንጭ መሆኑን አምናለሁ። በዋናነት ይህ ስር የሰደደ ችግር የሚፈጠረው ደግሞ በመንግሥት ተቋማትም ይሁን በግል መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች አገልጋይነት ባሕሪ አለመላበስ ነው።

ኢትዮጵያ የነደፈቻቸውን የልማት ግቦች ለማሳካት በመንግሥትም ሆነ በግሉ ዘርፍ የሕግ፣ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማድረግ፣ የተሟላ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ መሠረተ ልማት ማሟላት፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል።

እነዚህ መሠረታውያን መሟላታቸው ብቻ የሚጠበቀውን ለውጥ አያመጣም። ይልቁንም የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ፣ በሥነ ምግባሩ የተመሰገነና በፍፁም ቅንነት ማኅበረሰቡን የሚያገለግል ሠራተኛ ሊፈጠር ይገባል። ለመሆኑ ከዚህ አንፃር ሲመዘን የሀገራችን የአገልግሎት ዘርፍ ምን መልክ ይኖረው ይሆን? ኢትዮጵያዊ ባሕላችንስ ስለ ‹‹ማገልገል›› ምን ይለናል?

ከላይ ባነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ ምክንያት ለዛሬ የአገልጋይነት ባሕላችን ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ (በተለይ በግልና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶቻችን) በጥቂቱ ለመመልከትና የግል ምልከታዬን ለማጋራት ወድጃለሁ። ለመሆኑ ዘመናትን አብሮን የዘለቀው እንግዳ ተቀባይነታችን እና ጎንበስ ቀና ብሎ የማገልገል ልምዳችን ከወዴት ነው? ዛሬስ አብሮን ይሆን? ይህንን እሴታችንን በአገልግሎት ሰጪ ተቋማቶቻችን ውስጥ ለምን ተግባራዊ ማድረግ ተሳነን? እነዚህን ጥያቄዎች በዛሬው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰፊ ቦታን የሚይዙ ይሆናሉ።

በሀገራችን የቢሮክራሲ ተቋማት፤ ማኅበራት፣ የግል መሥሪያ ቤቶች ውስጥ (በሁሉም ባይሆን በአንዳንዶቹ) ለተገልጋይ የሚሰጠው ስፍራ እጅጉን አናሳ እንደሆነ የሁልግዜም የብዙኃን መወያያ ጉዳይ ነው። አንድ ግለሰብ ጉዳዩን ይዞ በአንድ ቢሮ አሊያም መሥሪያ ቤት ውስጥ ቢገኝ ያሰበውን ለመፈፀም በተደጋጋሚ (ለቀናት፣ ለሳምንታት ሲያልፍም ለዓመታት) ደጅ መጥናት እንደሚኖርበት፤ አሊያም ሙስና እስከመስጠት እንደሚደርስ ይነገራል።

ይህን መሰል ብልሹ አሠራር የፈጠረው በተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ተቀጣሪዎች የአገልጋይነት ባሕል ደካማ መሆን፣ የሥነ ምግባር ጉድለትና፣ የአቅም ማነስ እንደምክንያትነት ይጠቀሳሉ። በጥቅሉ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት (የግልም ሆነ የመንግሥት) ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች የአገልጋይነት ስሜት ደካማ መሆን ቀዳሚው መንስኤ ነው።

ይህ እሳቤ በመንግሥት ሠራተኛውም ይሁን በእያንዳንዱ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ መታየት ማኅበረሰቡ ጥራት፣ ቅልጥፍና እንዲሁም አርኪ ግልጋሎት እንዳያገኝ ከማድረጉም ባሻገር እንደ ሀገር የተያዘውን ልማት እና እድገት የሚገታ የገነገነ ችግር ነው።

እያንዳንዱ ግለሰብ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የግል ጉዳይ ለማስፈፀም ወደ ልዩ ልዩ የግልና የመንግሥት ተቋማት መሄዱ አይቀርም። እርሱም እንደዚያው በሚሠራበት ቦታ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ደንበኞች ይኖራሉ። ይህ ማለት ሁሉም ሰው የአገልጋይነት (በቅንነት የመታዘዝ፣ ደንበኞችን የማክበር፣ ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ በቅልጥፍና ጉዳይን የመፈፀም የመሳሰሉትን ባሕሪያት) ባሕልን ቢያዳብር ጥቅል ውጤቱ ፍፁም አስደሳችና ይሆናል። የምንፈልጋትን የተረጋጋ ኢኮኖሚ ያላት ሀገር ለመገንባት ያስችለናል።

ለሁሉም ግልፅ እንደሆነው በምንኖርበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ቴክኖሎጂ የሰው ልጆችን ውስብስብ ችግር በማቅለል፣ የአሠራር ሥርዓትን በማቀላጠፍ ግዜና ገንዘባችንን ይቆጥብልናል። የአሠራር ሥርዓታችንን በልዩ ልዩ መልኩ ማሻሻላችንም እንዲሁ የሚፈለገውን ውጤት እንድናስመዘግብ ሊረዳን ይችላል።

ይሁን እንጂ ቴክኖሎጂና ዘመናዊ አሠራር ብቻ በቂ አይደለም። የእኛ ማኅበረሰብን በምንሠራበት የሥራ መስክ ላይ (በተመደብንበት የአገልግሎት ቦታ ሁሉ በቅንነት፣ በሥነ ምግባር ለማገልገል ቁርጠኛ ሊሆን ይገባል። የእነዚህ ጥቅል ድምር የተሟላና ሁለንተናዊ እድገትን ያረጋግጣል።

አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ዜጎች የአገልጋይነት ባሕሪን እንዲላበሱ፣ በሀገር ወዳድነትና በእኔነት ስሜት ለጋራ እድገትና ብልፅግና እንዲሠሩ፣ አዲስ ባሕል፣ አዲስ እሳቤ እንዲፈጠር ተግባራዊ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል።

ለዚህ አስረጂ የሚሆነው ዜጎች በተለይ አገር ተረካቢ ወጣቶች (ስለሚከፈላቸውና ገንዘብን ስለሚያገኙበት ሀብት ብለው ሳይሆን) ለሀገራቸውና ለማኅበረሰባቸው እውቀትና ጉልበታቸውን ያለስስት በበጎ ፍቃድ በነፃ እንዲሰጡ ሰፊ ንቅናቄ ተደርጓል።

በዚህ ጥረትም እጅግ ውጤታማ የሆኑ በርካታ ሥራዎችን ተሠርተዋል። የዜጎች የአገልጋይነት ስሜት እንዲዳብር ቀስ በቀስም ይህ ቀድሞም ከነበረው ባሕላችን ጋር (እንግዳን ተቀብሎ፣ አልጋ ለቅቆና ተንከባክቦ በክብር የመሸኘት ባሕልን ጭምር) እንዲቀናጅና እንዲሰናሰን ተከታታይ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በበጎ ፍቃድ ማኅበረሰብን ከማገልገል በተጨማሪ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት በውስጣቸው የያዟቸው ሠራተኞች እውቀትን፣ ቅልጥፍናን ከምንም በላይ ደግሞ የሙያ ሥነምግባርን በተሟላ መልኩ እንዲተገብሩ ተከታታይ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል። መንግሥት ይህንን ለማስተግበር እየሠራ መሆኑን ይፋ አድርጓል። ይህ እርምጃ በሂደት በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚታየውን ብልሹ የአገልጋይነት ስሜትን እንደሚያስተካክለው ይጠበቃል።

ችግሩ በመንግሥት በሚወሰድ ጥብቅ ቁጥጥርና እርምጃ ብቻ የአገልጋይነት ስሜት ሊገነባ አይችልም። ማኅበረሰብን ተመድበው በሚሠሩበት ማንኛውም ቦታ ላይ ለማገልገል ፍላጎት የምናሳድረው ለሀገራችን በሚኖረን ጥልቅ ፍቅርና ቀናዒነት ነው። የሀገር ፍቅራችንን ማሳየት የምንችለው ደግሞ ከውስጣችን ሊፈጠር በሚገባው የአገልጋይነት ስሜት ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሀገር ፍቅሩን በዚህ ልክ ሊገልፅና በተግባር ሊያሳይ ይገባዋል።

የአገልጋይነት ስሜት በውስጣችን ለመገንባት የመጀመሪያው እርምጃ ተነሳሽነትን በውስጣችን መፍጠር ነው። ቀጥሎ ደግሞ በየግዜው እራሳችንን በእውቀትና ማዳበር እና ለአዳዲስ አሠራሮች ተጋላጭ ማድረግ ነው። ሌላውና መሠረታዊው ጉዳይ በጉልበታችንና በእውቀታችን ከምናገኘው ጥቅም በተለየ የማግበስበስ ባሕሪያችንን መግታት ያስፈልጋል።

ለምንሰጠው እያንዳንዱ ግልጋሎት ተገቢ ያልሆነ ዳረጎትን መጠበቅ የአገልጋይ ሠራተኛ ባሕሪ አይደለም። ለማኅበረሰብ ልማትና እድገት ሌት ተቀን መሥራት ነገ ለምንፈጥራቸው ሀገር ተረካቢ ልጆች ጠንካራ መሠረት የሚጥል መሆኑን ልንዘነጋ አይገባም።

በእርግጥ በአሁኑ ግዜ በሀገራችን ወጥነት ያለው፤ ፍፁም ሙያዊ ሥነ ምግባርን የተከተለ አገልጋይ ሠራተኛ በተሟላ ሁኔታ ማግኘት ይከብዳል። ይህንን ባሕል ግን በቁርጠኝነት ከሠራን እንቀይረዋለን። ለዚህ ማሳያው ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት የታዩት እመርታዎች ናቸው።

መንግሥት ሪፎርም ለላቀ አገልግሎት በሚል እሳቤ በሲቪል ሰርቪሱ ላይ ተከታታይ ማሻሻያዎችን እያደረገ ይገኛል። የግሉ ዘርፍም መሰል እርምጃዎችን መውሰድ ይገባዋል። በመንግሥት በኩል እያንዳንዱ ሠራተኛ ማኅበረሰብን በሙያዊ ብቃትና ሥነ ምግባር የማገልገል ቁመና ላይ የሚገኝ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡ አሠራሮችን እየዘረጋ ነው።

ይህ ተግባር በሠራተኛው ውስጥ አዲስ እሳቤ የሚፈጥር እንደሆነ ይታመናል። ነገር ግን አገልጋይነት በሕግ አስገዳጅነት ብቻ እንደማይመጣ ተረድቶ ሁሉም ዜጋ በውስጥ ፍላጎት ሊያዳብረው የሚገባ ባሕል መሆን አለበት። ሰላም!!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## አምና ይህን ጊዜ ...

መልካምሥራ አፈወርቅ

### እንደመነሻ ...

ዕለቱ አዲስ ዓመት ሊገባ በጣት የሚቆጠሩ ቀናት የቀሩት የዓውደ ዓመት ዋዜማ ነው። ሁሌም ዓመት በዓል ሲደርስ የሚኖረው ግርግርና ዝግጅት ዛሬም ቀጥሏል። አዎ! ዓውደ ዓመት ነው። ለዚያውም አዲስ ዓመት። ይህን ጊዜ ሙስሊም ክርስቲያኑ በእኩል ይጋረዋል። አዲስ ዓመት የእከሌ ብቻ አይባልም። ሁሉም በአንድ ያከብረዋል።

ዘመን መለወጫ ለብዙዎች የአዲስ ብስራት ምልክት፣ የመኖራቸው ብሩህ ተስፋ ነው። በርካቶች አሮጌውን ሸኝተው አዲሱን ሲቀበሉ ውስጣቸው ለሌላ ዕቅድ ይዘጋጃል። አዲስ ዓመት ሲመጣ ከፊት ከጀርባው መልካም ትርጉም ይዞ ነው። ይህ ጊዜ ከበዓላት ሁሉ ይለያል። ከዓውደ ዓመቶች ልቆ ደምቆ ይታያል።

ይህን እውነት በውስጤ ይዤ ከአንድ ዓመት በፊት ወደ ሆነው ጉዳይ በሀሳብ ተመላለስኩ። አሁንም ድረስ የማልረሳው ነውና ጊዜው ጊዜ ላይ ሲያቆመኝ ሐቁ ትውስ ሊለኝ ግድ ሆነ። እናም በወቅቱ ያየሁትን እማኝነት ዛሬም ዳግም ላወሳው መዝገቤን ገላለጥኩ። እነሆ ትውስታዬን ተጋሩት።

አምና በአዲስ ዓመቱ ዋዜማ በዕለተ ‹‹በጎ ፈቃድ ቀን›› ከፊቴ የቆሙት ወገኖች የተስፋ ጭላጭል ውስጣቸው ያለ አይመስልም። በሁሉም ገጽታ ኃዘን ከጉስቁልና ይነበባል። አብዛኞቹ በትካዜ እንደተዋጡ ነው። ገሚሶቹ የውስጣቸውን እያወጉ ስለብሶታቸው ማልቀስ፣ ማንባት ይዘዋል።

ከወላጆቻቸው ጋር የመጡት ሕጻናት ይህ እውነት የገባቸው አይመስልም። የወላጆቻቸውን ጭንቀት እየተጋሩ አይደለም። እንደ ልጅነታቸው ከወዲያ ወዲህ ይቦርቃሉ፣ ይሮጣሉ። ነፍስ ያወቁት ደግሞ የእናቶቻቸው ስሜት ተጋብቶባቸዋል። ፊታቸው ላይ ፈገግታ አልባ ገጽታ ይነበባል።

ዕለቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ታስቦ የሚውለው ‹‹የበጎ ፈቃድ ቀን›› ነው። በዚህ ቀን በርካቶች ሌሎችን በበጎነት ስሜት ይጎበኛሉ፣ የአቅማቸውን አካፍለው፣ የውስጥ ስሜትን ይጋራሉ። አሁን ላይ ይህ የአብሮነት ባሕል መለመድ ጀምሯል። በየቤቱ ዕንባን የሚያብሱ፣ ችግርን የሚጋሩ ወገኖች እየበረከቱ ነው።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የመሰብሰቢያ አዳራሽ የታደሙት ሴቶች ለቤቱ እንግዶች አይደሉም። ከዓመት በፊትም ይህን ጊዜ በዚህ ስፍራ ተገኝተው የቀኑን ትርጉም ተጋርተዋል። አሁን ደግሞ ለየት ባለ ዝግጅት የተቋሙ ሠራተኞችና አመራሮች ከዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጋር በመቀናጀት ‹‹አለናችሁ›› ብለዋቸዋል።

ለዓውደ ዓመቱ ጓዳ ለእያንዳንዳቸው ሀምሳ ኪሎ ዱቄት፣ ማካሮኒና ፈሳሽ ዘይት ለስጦታ ተዘጋጅቷል። አብዛኞቹ ዓይናቸውን አላመኑትም። በአድናቆት የሚያስተውሉ፣ በሆነላቸው ሁሉ አብዝተው የሚያመሰግኑ ወገኖች ገጽታቸው ወገግ ብሏል።

ሕጻናት ልጆቻቸው ለእነሱ የሚበጁ የትምህርት ቁሳቁሶች በመኖራቸው ተደስተዋል። ሁሉም የዝግጅቱን መጀመር በጉጉት እየጠበቁ ነው። የበጎ ቀን ስጦታዎች ከመበርከታቸው በፊት በአዳራሹ የተገኙት ወገኖች የልባቸውን ይተነፍሱ ዘንድ ዕድል ተሰጣቸው። ሁሉም የውስጣቸውን ሚስጥር፣ የኑሯቸውን ገመና ለመተንፈስ ተሽቀዳደሙ።

በዝግጅቱ ከታደሙት መሐል የመጀመሪያዋ ተናጋሪ በፍጥነት ከነበረችበት ተነስታ ስትወጣ አየኋት። አወጣጧ ድንገቴ ነበር። አስቀድማ አምርራ እያለቀሰች መቆየቷን አስታውስኩ። ልክ እንደኔ ሁሉ ሌሎች ዓይኖች አተኮሩባት።

ወደ መሐል ቀርባ ንግግር ከመጀመሯ ፊቷ በአንዴ መለዋወጥ ያዘ። ኀዘን ያጠላው ገጽታዋ በዕንባ ሊታጠብ አልዘገየም። በምስጋና የታጀበው ቃል ደግሞ ብቻውን አልተገለጸም። የሕይወትን ምስጢራት፣ የኑሮ ፈተናዎችን አንድ በአንድ ሊያሳየን መዝገቡ ተገለጠ።

ወጣቷ ተናጋሪ የታዳሚው ውስጠት በኀዘን አስደፋች። ከአንደበቷ የሚፈልቁ እውነታዎች የእያንዳንዱን አድማጭ ስሜት ሊፈትኑት ግድ ሆነ። በዕንባ የታጀበ ሐቅ፣ በኀዘን የተሰበረ እውነታ እንዲህ መሰማት ጀመረ።

‹‹አንድ ወር ሙሉ የደከምኩበትን ገንዘብ ያገኘሁት ዛሬ

#### ‹‹እማዬ! ዱቄቱ ላይ ተኝተን ፎቶ እንነሳ ››

ነበር። አንድ ሁለት ብዬ ሰባት መቶ ብር ቆጠርኩ። ይህ የላቤ ወዝ፣ የጉልበቴ ዋጋ ነው። አማራጭ የለኝም። ገንዘቡ ውሎ ካደረ ይጠፋብኛል። በዚህ ብር ላደርግ የምችለው ደግሞ ጤፍ መግዛት ብቻ ነው። ሰባት መቶ ብሩን ይዤ ከገበያ ሄድኩ። አምስት ኪሎ ጤፍ ተመዝኖልኝ ይዤው ወጣሁ። ወዲያው ምን እንደማደርገው ጨነቀኝ።

ጤፉን ማበጠር ፣ማነፊስ አልፈለኩም። ይህን ከሞከርኩ ብን ብሎ ሊያልቅብኝ ነው። አሁንም ጭንቅ ጥብብ አለኝ። ስጋት ቢይዘኝ ጤፉን ማበጠር ተውኩት። በዚህ ስሜት ሳለሁ በድንገት አንድ የስልክ ጥሪ ለጆሮዬ ደረሰ። ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ወይዘሮ ብርሃኔ ደመቀ ነበረች።

የደወለችበትን ምክንያት ስትነግረኝ በእጅጉ ደነገጥኩ። ልክ እንደአምናው ርዳታ ሊሰጠኝ መሆኑን ስሰማ በእጅጉ ገረመኝ። ውስጥ ደርሼ ሃምሳ ኪሎ ዱቄቱን ስመለከት ደግሞ ሽርተት ያልኩ እስኪመስለኝ ውስጤ ካደኝ። ዓይኔን አላመንኩም።

‹‹ኧረ ጉድ ፈላ!›› ስል ጮህኩ አሁንም አላመንኩም። እውነት ይህ ሁሉ ዱቄት እኔ ቤት ሊገባ ነው? ስል ራሴን ጠየቅሁ። መለስ ብዬ ማኮሮኒውን፣ አምስት ሊትሩን ዘይት አየሁት። እሱም የኔ ነው። ስቅስቅ... ብዬ አለቀስኩ።

ከጎኔ የነበሩት እማማ ለምን ታለቅሻለሽ ሲሉ ተቆጡኝ። በእርግጥ ዛሬ ማልቀስ አልነበረኝም። ግን ምን ላድርግ እጅግ ደስ ብሎኝ ነው። አዎ! ዛሬ አለኝ፣ ሀብታም ነኝ። ወግ ደርሶኛል። ቡና አፍልቼ ጎረቤቶቼን እጠራለሁ። እኔ አስተዳደጌ በድርጅት ውስጥ ነው። ቤተሰብ የለኝም። ዘመዶቼን አላውቅም።

በሕይወቴ ሁለት ጊዜ ‹‹ሰርፕራይዝ›› ሆኛለሁ። አንዱ ባደኩበት ድርጅት አብሮ አደጎቼ ‹‹ዛሬ ልደትሽ ነው›› ብለው ኬክ የቆረሱልኝ ቀን ነው። ዛሬ ደግሞ በእናንተ ፊት የተደረገልኝ ታላቅ ስጦታ ሁለተኛዬ ሆኗል። ከጎኔ ያለችው ልጄ በሆነው ሁሉ ተገርማለች። እሷም እንደኔ ዓይኗን አላመነችም። እናም ደጋግማ እንዲህ አለችኝ ‹‹እማዬ ዱቄቱ ላይ ተኝተን ፎቶ እንነሳ››

እኔም እውነትሽን ነው ልጄ ቤታችን ስንገባ ሁላችንም ተሰባስበን ፎቶ እንነሳበታለን›› አልኳት። የሁሉም ታዳሚ ስሜት እንደተረበሸ ቀጣይዋ እናት ከወንበሯ ተነሳች።

ይህቺ ሴት በአካል እራሷን ከምትመስል ልጅ ጋር አይቻታለሁ። አዎ! አልተሳሳትኩም ልጇ ነች። እናት ጎስቋላ ፊቷ ብዙ ይናገራል። ከንግግሯ በፊት ዕንባ እያነቃት ነው። ሆድ በባሰው አንደበቷ የውስጧን ለመተንፈስ ሞከረች። ሳግ የያዘው ድምፅ እንደምንም አሸንፎ ለብዙኃን መሰማት ጀመረ።

#### ‹‹ልጄ ሲደፍሯት ባሉ ሰዎች በጩቤ ተወግታለች››

እኔ ቤተሰቦቼን አላውቅም። ያደኩት በሌሎች እጅ ነው። አስራ አንደኛ ክፍል ሳለሁ ከአንድ ሰው ጋር ተዋወቅሁ። አብረን መኖር ጀመርን። አረገዝኩ። ሴት ልጅም ወለድኩ። ይህን ያወቀው ባለቤቴ አብሮኝ መዝለቅ አልፈለገም። በድንገት ከነልጄ ትቶኝ ጠፋ። ከዚህ በኋላ የነበረው ሕይወት የፈተና ሆነ። እሷን ይዤ ጎዳና ለጎዳና መንከራተት ያዝኩ።

መኖሪያችን ጎዳና ቢሆንም ልጄ እንደምንም በውጣ ውረድ መሐል አደገች። የጎዳና ሕይወት ግን ብዙ ችግር አመጣብን። ልጄ ሊደፍሯት በሞከሩ ጎረምሶች በጩቤ ተወጋች። ይህን ችግር ያስተዋለው ወረዳ ዘጠኝ እንደ ቤተሰብ ሆነኝ።

በአሁኑ ግዜ የወረዳው ሴቶችና ሕጻናት በቀን የመደብ መኝታ እየከፈለልኝ በቤት ውስጥ አድራለሁ። እኔ እስካሁን ወገን ዘመድ እንደሌለኝ አስብ ነበር። አሁን ግን በእናንተ ሁሉን አግኝቻለሁ። ስላደረጋችሁልኝ በጎነት ሁሉ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

#### ‹‹ተጠልቼ የኖርኩ ሰው ነኝ››

ያለአባት የሚያድጉ የሁለት ልጆች እናት ነኝ። የአስራ ስድስት ዓመቱ ልጄ በድንገት ወድቆ የነርቭ ታማሚ ሆኗል። ከዚህ ቀድሞ በሰዎች እገዛ በዊልቸር ይሄድ ነበር። አሁን ግን በመጠኑ ተሽሎት በእግሩ እየተራመደ ነው። በኑሮዬ ችግረኛ ነኝ። የእኔ አቅም ጨው በርበሬ ከመግዛት አያልፍም። ጓዳዬን የምታውቅ አንዲት ሴት ግን ሙሉ የቤት ወጪዬን ትሸፍናለች።

ማንኛውንም ሥራ አልንቅም። ወንዶች የሚሠሩትን ሁሉ እየተሸከምኩ ልጆቼን አሳድጋለሁ። ዕውቀት የሚያስፈልገውን ግን ትምህርት ስለሚጠይቅ አልሞክረውም። እንዲያም ሆኖ ሰዎች ሊቀርቡኝ አይፈልጉም። ሕመሜ ስለሚታወቅ ተገልዬ፣ ተጠልቼ የኖርኩ ሰው ነኝ።

ዛሬ መንግሥት ቤት ሠርቶ አስረክቦኛል። ይህ ሲታወቅ ትናንት በሩቁ የሚሸሹኝ ሁሉ ለሰላምታ እጃቸውን ይዘረጋሉ። በሕይወቴ ብዙ ሰዎች ቤቴን አንኳኩተዋል። እናንተ ደግሞ በዛሬው ቀን ለበዓል የሚያስፈልገኝን አሟላችሁልኝ። እጅግ በጣም አመሰግናለሁ ።

#### ‹‹ዘንድሮም አስታወሳችሁን ››

ይህች ሴት ተናግራ እንደገባች አንዲት ትልቅ እናት ወደ መድረኩ ብቅ አሉ። ከመምጣታቸው አስቀድሞ ከአንዲት ልጃቸው ጋር ተቀምጠው ይጫወቱ ነበር። የእናትና ልጅ ቀረቤታ ዓይን ይስባል። ልጅ በየምክንያቱ እያቀፈች ትስማቸዋለች። እሳቸውም በተለየ ስስትና ፍቅር ያስተውሏታል።

ወይዘሮዋ ሰውነታቸው ወፍራም በመሆኑ ችግር አይቷቸው የሚያውቅ አይመስልም። ገጽታቸው ፈገግ፣ ፈካ ያለ ነው። ያያቸው እንዲህ ይገምት እንጂ ንግግር ከመጀመራቸው የታዳሚውን አንገት በኃዘን አስደፉት ።

‹‹አንቆርጫ›› ከሚባለው ሰፈር ተከራይቼ እኖራለሁ። የስኳር ታማሚ ነኝ። በየቀኑ ለበሽታው መድኃኒት መውሰድ ግዴታዬ ነው። እኔ ግን አንዳች መተዳደሪያ የለኝም። ለነፍስ ያሉ አጉርሰው ያለብሱኛል። ልጆቼን የማልስ የማቀምሰው የለኝም። እነሱን ለማኖር ስል ግን ‹‹ቡሌ›› እየወሰድኩ አሳድጋቸዋለሁ።

ከዚህ በፊት ሠርቼ ለመብላት ጉልበቴ የበረታ፣ ውስጤ የጠነከረ ነበር። አሁን ሕመሙ አቅሜን አዳክሞታል። ከቀናት በፊት የምቀምሰ፣ የምልሰው አልነበረም።በቀደም በባዶ ሆዴ ከቤት ወጣሁ። ከመንገድ በድንገት ራሴን ብስት አንዲት ሴት ስኳር ሰጥታኝ ሕይወቴ ተረፈ።

ልጆቼን ይዤ በኪራይ እኖራለሁ። ለቤቱ ግን እምከፍለው የለም። ይህች ትንሽ ልጅ ግን ማስቲካ እየሸጠች የወር ኪራዩን ትሸፍናለች። አምና ይህን ጊዜ ለልጆቻችን ደብተር ሰጥታችሁን ነበር። አሁንም ጊዜው ትዝ ብሎኝ ሳስባችሁ ቆይቻለሁ። እናንተ ግን ፈጽሞ አልረሳችሁንም። ዘንድሮም አስታወሳችሁን። ከምስጋና ውጭ ምን ልል እችላለሁ? ብድሩ ይግባችሁ እንጂ።

#### ‹‹የሃያ አምስት ዓመት ፀበልተኛ ነኝ››

ያመኛል። ለሕመሜ ፈውስ ለመሻት እንጦጦ ማርያም መጠመቅ ከጀመርኩ ከሃያ አምስት ዓመት በላይ ሆኗል። አንዲት ልጅ አለችኝ። ይዣት ስመጣ የሦስት ዓመት ሕጻን ነበረች። የምኖረው በቤት ኪራይ ነው። አከራዮቼ እንዳሻቸው ‹‹ውጭ ፣ ግቢ›› ይሉኛል። እንዲያም ሆኖ ኪራይ የምከፍልበት ቋሚ ገቢ የለኝም። ዛሬ ይህ ድርጅት ድጋፉን ሲሰጠኝ ከልብ ተደሰትኩ። በሆነልኝ ሁሉ ከልብ አመሰግኛለሁ።

#### የሴና እናት ሌሊሴ

ፈገግታ ያበራው ገጽታ ጆሮን ከሚስብ አንደበት ሲዳመር የሌሊሴ ውበት ይበልጥ ይጎላል። ሌሊሴን የማያውቅ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሠራተኛ የለም። እሷ የፕሬስ የቅርብ ቤተሰብ ሆናለች። ደስተኛ ልጇ ሴና በሠራተኛው ዕቅፍ ያደገች እንቦቃቅላ ናት። እንደ እናቷ ፍልቅልቅ የሆነች ሳቂታ ሕጻን ።

ሌሊሴ ከዓመታት በፊት ከድርጅቱ አጥር በአጭር ርቀት ተቀምጣ ትውል ነበር። የእሷ መቀመጥ የሚለውጥ ሥራ አልነበረም። አላፊ አግዳሚው ያለውን እንዲጥልላት ለመለመን እንጂ። ደግነቱ በርካታው መንገደኛ አይቶ አያልፋትም። ቆንጆዬዋን ሕፃን ያየ ሁሉ በኃዘኔታ የእጁን ይጥልላታል።

የሌሊሴ ሕይወት ግን በዚህ መስመር አልቀጠለም። ከቀናት በአንዱ በአንዲት መልካም ሴት ዓይኖች ተጎበኘች። ይህች ሴት ቀረብ ብላ ስለሥራ፣ ስለራስን መቻል አዋየቻት። ይህ እውነት የሌሊሴም ነበርና ዓይኗን አላሸችም። ከቀናት በኋላ የድንች መጥበሻና አስፈላጊ ቁሶች ከእጇ ደረሱ። ይህ ይሆን ዘንድ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቅርብ አጋሯ ሆነ። ሌሊሴ ልመናን ተጠይፋ ወደ ሥራ ፈጥና ገባች።።

ትናንት ለምፅዋት እጃቸውን የዘረጉላት ዛሬም ገንዘብ ይዘው የላቧን ዋጋ ገዟት፣ ቀመሱላት። ደንበኞቿ በረከቱ። ስለሆነው ሁሉ ‹‹አድናቂዎቿ ቃል አጠራቸው። ትንሽዬዋ ሴና ከድርጅቱ የሠራተኛ ልጆች አንደኛዋ ሆና በሕጻናት ማቆያ መዋል ጀመረች። ሌሊሴ ታሪኳ ፍጹም ተቀየረ። በየጊዜው ጥሩ ትርፍ ማግኘት ያዘች። ዕቁብ ገባች። ገንዘብ ቆጠበች ።

ዛሬ ሌሊሴ ከእንግዶቹ መሐል አንደኛዋ ሴት ሆናለች። እሷ ግን እንደሌሎቹ የከፋ ችግሯን እያወራች አይደለም። በጣፋጭ አንደበቷ ደግማ ደጋግማ ‹‹አመሰግናለሁ›› እያለች ነው።

አዎ! ዘንድሮ የትናንትናዋ ሴና ተማሪ ልትሆን ወግ ደርሷታል። ለዚህ ሕጋዊነት አስፈላጊውን ሁሉ ያሟላላት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ነው።

ፕሬስ እንደ እናት በሚጠራቸው እማማ ግምጃ ዋስትና የሴናን ሕጋዊ የትምህርት መታወቂያ ለማውጣት ችሏል። ወደፊት በትምህርት ዓለም ለሚኖረው ማንኛውም ድጋፍም ከጎኗ አይርቅም።

ይህ ብቻ አይደለም። ሌሊሴ አሁን እየሠራችበት ከሚገኘው የፕሬስ ድርጅት አካባቢ ያለአንዳች ችግር በሥራው እንድትቀጥል በሰነድ የተደገፈ ሕጋዊ ማረጋገጫ አግኝታለች። ዛሬ የሌሊሴ ድምፅ ከሌሎች ሁሉ ይለያል። የትናንት ታሪኳ ከዛሬው ፍጹም ተቀይሯል። ስለነገው አሁን ላይ ቆማ በብሩህ ተስፋ ትሮጣለች ።

#### ዘንድሮ...

ዘንድሮ ሌላ አዲስ ዓመት ነው። አምና ይህን ግዜ እነዚህን ድምፆች ያሠሙን ወገኖች ሕይወት ምን እንደሚመስል አይታወቅም። ዘንድሮ ጊዜ ወስዶ የጎበኘ፣ የጠየቃቸው የለም። የኑሮ ውድነቱ ጫንቃቸውን ያገበጣቸው፣ ወላጆች በትምህርት አምሮት የሚሰቃዩ ሕጻናት የወገኖችን ድጋፍ ይሻሉ። ልክ እንደዓምናው በረከት። መልካም ዓዲስ ዓመት።

> ‹‹ከቀናት በአንዱ በአንዲት መልካም ሴት ዓይኖች ተጎበኘች። ይህች ሴት ቀረብ ብላ ስለሥራ፣ ስለራስን መቻል አዋየቻት። ይህ እውነት የሌሲሴም ነበርና ዓይኗን አላሸችም። ከቀናት በኋላ የድንች መጥበሻና አስፈላጊ ቁሶች ከእጇ ደረሱ። ይህ ይሆን ዘንድ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቅርብ አጋሯ ሆነ። ሌሊሴ ልመናን ተጠይፋ ወደ ሥራ ፈጥና ገባች››

# መሠረተ ልማት

# የትራንስፖርት አገልግሎትን የሚያሳልጡ መኪና ማቆሚያዎች በኮሪደር ልማቱ



**በኃይሉ አበራ**

በመዲናዋ የመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራዎች በስኬት ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን፤ የምዕራፍ ሁለት የኮሪደር ልማት ሥራውም ተጀምሯል። የኮሪደር ልማቱ ለከተማዋ ካስገኘላት ጥቅሞች መካከልም ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች፣ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ የብስክሌት መንገዶች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች፣ የመዝናኛ ስፍራዎች፣ ፏፏቴዎች (ፋውንቴኖች) ተጠቃሽ ናቸው። በተለይም የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች (ፓርኪንጎች) በስፋት ተገንብተዋል፣ አሁንም እየተገነቡ ነው።

በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች የተገነቡ የመኪና ማቆሚያዎች አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። ቀደም ብለው ግንባታቸው የተከናወኑ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ወይም የፓርኪንግ አገልግሎት መስጫዎች መካከል የመስቀል አደባባይ ከምድር በታች የተገነቡት፣ እንዲሁም የታላቁ ቤተመንግሥት የፓርኪንግ ግንባታ እና የአብርሆት ቤተመጻሕፍት የመኪና ማቆሚያ የሚጠቀስ ነው። እነዚህን ጨምሮ በሂደት የከተማዋን የፓርኪንግ አገልግሎት እያሰፉ እና መንገድ ላይ ይቆሙ የነበሩ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር እየቀነሱ በዚያው ልክ ይፈጠሩ የነበሩ የትራፊክ መጨናነቆችንና የደህንነት ችግሮችን ማቃለል ተችሏል።

በመዲናዋ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች በበቂ ሁኔታ ባለመገንባታቸው ባለጉዳዮች መኪናቸውን መንገድ ዳር አቁመው ወደ ጉዳያቸው ለመሄድ ሲገደዱ ቆይተዋል። ይህም ለንብረት ደህንነት ችግር ሲያጋልጥ ይስተዋላል። ከዚህም ውጭ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በበቂ ባለመኖራቸው በትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መንገዶች የሚቆሙ ተሽከርካሪዎች መንገዶችን ሲያጣብቡ እና እግረኞችን ጭምር መንቀሳቀሻ ሲያሳጡ ቆይተዋል። ይሁንና የኮሪደር ልማቱ ይዟቸው ከመጡ በረከቶች አንዱ በመሆኑ በአሁን ወቅት የኮሪደር ልማቱ በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች ይህን ችግር መቅረፍ ተችሏል። ነገር ግን የኮሪደር ልማት ሥራው ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ችግሩ ባልተጀመረባቸው በአብዛኛው የመዲናዋ አካባቢዎች ችግሩ በስፋት ይታያል።

ይህንን ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ የትራፊክ ጭንቅንቆችን የሚያስቀሩ በርካታ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ተርሚናሎች ተገንብተው ለአገልግሎት እየበቁ ነው፤ በግንባታ ላይ የሚገኙ ከምድር እስከ ፎቅ ያሉ የመኪና ማቆሚያ ሥራዎች አሉ። ከመንገድ ገባ ያሉ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች ትኩረት አግኝተው በየአካባቢው እየተከናወነ ሲሆን የትራፊክ መጨናነቆችን የሚያስቀሩ የተለያዩ ድልድዮች እና አቋራጭ መንገዶች ግንባታም እየተስተዋለ ይገኛል። በአራት ኪሎ አራዳ ክፍለ ከተማ አካባቢ፣ በፒያሳ ዓድዋ ሙዚየም የተገነባው የአውቶቡስ ማቆሚያ ተርሚናል፣ በሜክሲኮ ዋቢሸበሌ ሆቴል አጠገብ፣ እንዲሁም በቦሌ እና መገናኛ አካባቢዎች እየተገነቡ የሚገኙና የፓርኪንግ አገልግሎት መሰጠት የጀመሩ ማቆሚያዎች ወይም ተርሚናሎች ይገኙበታል።

ከእነዚህም መካከል በአራዳ ክፍለ ከተማ ፊት ለፊት በሰባ ደረጃ በኩል የሚገኘው ፍቅር የተሽከርካሪ ማቆሚያ አንዱ ነው። ፓርኪንጉ ወይም የተሽከርካሪ ማቆያው በራማ ኮንስትራክሽን የተገነባ ሲሆን፤ በአንድ ጊዜ የሚሰጠው የፓርኪንግ አገልግሎት እስከ 100 ለሚደርሱ መኪኖች ነው። በመሆኑም በአንድ ጊዜ ለ100 መኪኖች አገልግሎት በመስጠት በአካባቢው ያለውን የትራፊክ መጨናነቅ መቅረፍ ተችሏል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሚኪያስ ፋንታዬ የፓርኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው። እንደ አቶ ሚኪያስ አሁን ያለው የፓርኪንግ አገልግሎት በፊት ከነበረው በውበትም በፅዳትም በተደራሽነት ጭምር የተሻለ ነው። ከመንገድ ገባ ብለው የተሰሩት የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች መንገድ ዳር ላይ ይቆሙ የነበሩ መኪኖችን ስለሚያነሳ መንገዱ ነፃ ሆኖ ለትራንስፖርት አገልግሎቱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የፓርኪንግ አገልግሎቱ ለተሽከርካሪ ባለንብረቶችም የተሻለ ደህንነት ይኖረዋል። በግንባታ ላይ የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎቶችን ጨምሮ ሥራ ሲጀምሩ ወደ የክፍያ አሰራር ሲገቡ ተጠቃሚውም ከደህንነቱ አኳያ በአገልግሎቱ የመጠቀም ፍላጎት እንዲያድርበት ከህብረተሰቡ አቅም ጋር የተገናዘበ መሆን አለበትም። ቀደም ሲል ከአራት ኪሎ ጫፍ እስከ ፒያሳ ለመድረስ ከፍተኛ መጨናነቅ እንደነበረና ጊዜ የሚወስድ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ግን በማንኛውም ሰዓት ቢሆን ይህ ችግር ተቀርፎ መንገዱ ነፃ ሆኖ ለማሽከርከርም ምቹ ሆኖ ይገኛል። በዚያው ልክ ደግሞ አሽከርካሪዎች ከአደጋ ነፃ ለመሆን በኃላፊነት ማሽከርከር ይገባቸዋል።

አንዳንድ አካባቢዎች መስተካከል ይገባዋል ሲሉ እንደገለፁትም የተሽከርካሪ መመለሻ መንገዶች በሲሚንቶ፣ በብረት ተሰርቶ ከተዘጋጀ በኋላ ዝግ የሚደረግበት ሁኔታ መታየት አለበት። ለምሳሌ ከቄራ ቀለበት መሻገሪያው ወደ ወሎ ሰፈር ሲኬድ ወንጌላዊት ጋር ዞሮ መመለሻ መንገድ ተዘግቶ ይገኛል። አንድ ጊዜ መሻጋገሪያው ላይ ከወጣ ኢንሳን አልፎ ወደ ወሎ ሰፈር ዋናው አደባባይ ለመድረስ ከተቃረበ በኋላ ነው ተመልሶ መምጣት የሚቻለው። በዚህም ብዙ ጊዜ መጨናነቆችን የሚፈጠረው መመለሻ መንገድ በሚፈልገው ሰው ነው። የዚህ ዓይነት ችግሮች በኮተቤ ካራ፣ በወሰን እና መገናኛ አካባቢዎች ማስተዋላቸውን ጠቁመው በዚህ ላይ ማሻሻያ በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎቱን የተሳለጠ ማድረግ እንደሚገባ አመልክተዋል።

አሽከርካሪው መዞር እየፈለገ እስከ ጫፍ 500 እና 600 ሜትር ያህል ከሄደ በኋላ ዞሮ ለመመለስ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች አሉ። በዚህም አምስት እና ስድስት ደቂቃዎችን ለመቆየት እና ከፍተኛ መጨናነቆችን ለመፍጠር ይገደዳል። ይህም ተጨማሪ የተሽከርካሪ መጨናነቆችን የሚፈጥር ነው። በኮሪደር ልማቱ የተገነቡት የተሽከርካሪ እና የብስክሌት መንገዶች ለትራንስፖርት አገልግሎቱ የተመቻቹ ናቸው፤ የእግረኛ መሄጃዎቹም ለእይታ ምቹ ከመሆኑም ባለፈ ህብረተሰቡ በቀላሉ በእግሩ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችሉ ናቸው። ማየት ለተሳናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል ነው። ለመላው ኢትዮጵያውያን አዲሱ ዓመት የሰላም የብልጽግና እንዲሆን ምኞታቸውን ገልጸውም የሀገር ሀብት ፈስሶባቸው አገልግሎት እንዲሰጡ የተገነቡ የኮሪደር ልማቱ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን አሽከርካሪዎችን ጨምሮ ሁሉም እንዲጠብቅ ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የፓርኪንግ አገልግሎት ሲጠቀሙ ያገኘናቸው ሌላኛዋ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ ቲዮቢስታ ኃይለማርያም ለአምስት ዓመታት ያህል አሽከርካሪ ሆነው ቆይተዋል። በእነዚህ ጊዜያት በጥንቃቄ ማሽከርከራቸውንና ምንም ችግር እንዳልገጠማቸውም ጠቅሰዋል። ይሁንና መኪናቸው መንገድ ዳር ሲያቆሙ የደህንነት ስጋት እና ጥርጣሬ ይሰማቸው እንደነበርና ብዙ ምቾት አይሰማቸውም ነበር። አሁን ግን ራሱን የቻለ የመኪና ማቆሚያ ቦታ በመዘጋጀቱ ሃሳብ ሳይገባቸው መኪናን አቆይቶ ወደ ጉዳይ ሄዶ መመለስ ይቻላል። በአራት ኪሎ አካባቢ ለ15 ቀን ያህል የሚከታተሉት ጉዳይ ስለነበራቸው ያለምንም ችግር መኪናቸውን በፍቅር የተሽከርካሪ ማቆሚያ እየተገለገሉ ናቸው። በማቆሚያው የሚጠብቁትም የደህንነት ስጋት ሳይኖር በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ጠቁመዋል።

በፓርኪንጉ ከሁለት ሰዓታት በላይ አቆይተው 20 ብር ብቻ መክፈላቸውን ጠቅሰው አገልግሎቱ መንገዶችን ነፃ ከማድረግ፣ ከመኪና እና የመኪና ስፖኪዮ መሰረቅ ችግሮች ያድናል። በከተማዋ የተሰሩት የመኪና ማቆሚያ ሥራዎችንም አድንቀው በቀጣይም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በሁሉም የከተማዋ አካባቢዎች መስፋት እንዳለባቸው አመልክተዋል። በአዲስ ዓመቱ ለመላው ኢትዮጵያውያን መልካም ምኞታቸውን ገልጸው በማንኛውም አጋጣሚዎች በጥንቃቄ ማሽከርከር እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ ነዋሪ አቶ ብሩክ ፍቃዱ ቸሩ በበኩላቸው በፍቅር የፓርኪንግ አገልግሎት መስጫ ማህበር በመንግሥት የሥራ እድል ከተፈጠረላቸው መካከል አንደኛው ናቸው። በማህበሩ 15 ያህል ሆነው የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ሲሆን፤ ከራሳቸው አልፈው ቤተሰብ የሚያስተዳድሩም ይገኙበታል። አሮጌና አዲስ መኪና ሳይሉ ሁሉንም ተሽከርካሪዎች ታርጋ ሳይለዩ ያለ አድልኦ እንደስሙ በፍቅር እንደሚያስተናግዱ ጠቁመዋል።

ቀደም ሲል ከኮተቤ አንስቶ በመገናኛ አድርጎ፣ በፒያሳ ወደ አውቶብስ ተራ ወደ ቀጨኔ ለመሄድ በተለይ በምሳ ሰዓት፣ በተማሪዎች እና በሠራተኛ መውጫ ሰዓት ላይ ለመተላለፍ ከፍተኛ ጭንቅንቅ እንደነበር አስታውሰዋል። አሁን ግን በኮሪደር ልማቱ በተሰሩ ሥራዎች አንድም መኪና መንገድ ላይ ቆሞ አይታይም። በርካታ ደረጃቸውን የጠበቁ የመኪና ማቆሚያዎች እየተሰሩ ናቸው፤ መንገዶች ሰፍተዋል፤ አማራጭ መንገዶች ተፈጥረዋል። ይህ መሆኑ ለባለንብረቱም ሆነ ለወጣቶች የሥራ እድል ከመፍጠር አኳያ በመንግሥት የተሰራው ሥራ አበረታች እንደሆነ በአድናቆት ገልጸዋል።

በፓርኪንግ አገልግሎቱ በተለይ በሰንበት ቀን እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት መኪናቸውን ትተው የሚያመሹ እንዳሉ ጠቁመው ከአራዳ ክፍለ ከተማ እና ከአካባቢው ፖሊሶች ጋር በመሆን በንቃት እንደሚጠብቁም ጠቁመዋል። ቅዳሜ ምሽት አልኮል ጠጥተው መኪናቸውን ለመውሰድ የሚመጡ እንዳሉ የጠቆሙት አቶ ብሩክ፤ በዚህ ጊዜ ታዲያ ለደህንነታቸው ሲባል መኪናቸውን እንዳይወስዱ በማድረግ ሰኞ ቀን መጥተው ይቅርታ ጠይቀው እና አመስግነው መኪናቸውን የሚወስዱ መሆኑን አስታውሰዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በፓርኪንግ አገልግሎቱ የተለያዩ አጋጣሚዎች የሚገጥሙ እንደሆነ በማንሳት መኪና ያቆመው ሰው ብቻ መውሰድ እንደሚገባውም አመላክተዋል።

ምሽት ላይ የአካባቢው ማህበረሰብም ሮንድ በመውጣት በትብብር የሚሰራ ሲሆን፤ ለዚህም ሲሉም በኮሪደር ልማቱ የተገጠሙ ዘመናዊ መብራቶች አጋዥ እንደሆኑና ችግሮች እንደማያጋጥሙ ተናግረዋል። በአንድ ጊዜ ብቻ ሰባት ያህል ሆነው እንዲሁም ከሁለት ጥበቃዎች ጋር ዘጠኝ ሆነው የመኪና ጥበቃ ሥራውን ያከናውናሉ። አሁን ላይ ዘመናዊ አሰራሮች እየተስፋፉ አጥር እየቀረ መሆኑንም በማስታወስ በቀጣይ በመሰል የፓርኪንግ አገልግሎቶች ከሰዎች በተጨማሪ በካሜራ መታገዝ እንደሚገባቸው እና አንዳንድ የስርቆት አጋጣሚዎችን መከታተል እንደሚገባም አመላክተዋል።

በመጨረሻም የዚህ ዓይነት የፓርኪንግ አገልግሎቶች በየቦታው ተስፋፍተው ለወጣቶች የሥራ እድል እንዲፈጠር ወጣቱም ሥራ ሳይመርጥ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሰርቶ ሀገሩን እና ሕዝቡን እንዲያገለግል ሲሉም አመላክተዋል። እንዲሁም ወታደሩም በድንበሩ ዜጋውም በሀገሩ ጉዳይ ሁሉም በየተሰማራበት አንድ ሆኖ ሀገሩን እንዲያገለግል፤ በሰላም በመተሳሰብ አዲሱን ዓመት በፍቅር እንዲቀበል መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

በራማ ኮንስትራክሽን የቢሮ ምህንድስና ክፍል ኃላፊ ኢንጂነር ሄኖክ ቢያደርገው በበኩላቸው በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ሕንፃ ፊት ለፊት የተሰራው የተሽከርካሪ ማቆሚያው በከተማ አስተዳደሩ አቅጣጫ መሠረት በራማ ኮንስትራክሽን የግንባታ ሥራው ተከናውኖ ለአገልግሎት የበቃ ነው። ይህም ከዚህ ቀደም የነበረውን ሳይጨምር 1300 ካሬ ያህል ቦታ ላይ ተገንብቶ በአንድ ጊዜም ከ100 በላይ መኪኖችን ለማስተናገድ የተዘጋጀ ነው። ለአካባቢው ወጣቶችም የሥራ እድል ከፍቷል፤ መኪኖችም በአካባቢው መንገድ ዳር መቆም ስለማይችሉ በማቆሚያ ፓርኩ እየተስተናገዱ ነው። የመኪና ማቆሚያው የተሰራበት ደረጃም አፈሩ ተስተካክሎ፣ ሰብቤዝ ማቴሪያል፣ ቤዝኮርስ ማቴሪያል እና አስፓልት ንጣፍ ተሰርቶለት ነው። እንዲሁም ከርብ ስቶን ሥራም በተጨማሪ ተሰርቶለታል። ተጨማሪ የመንገድ ዳር መብራቶችም ለመኪና ማቆሚያው ተጨማሪ ሰዓታት አገልግሎት ለመስጠት ያስቻለ ነው። በመኪና ማቆሚያው የመፀዳጃ ቤት ግንባታ እና የሻወር አገልግሎትን ጨምሮ የዊልቸር ተጠቃሚዎችን ታሳቢ ተደርጎ ለአገልግሎት ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ኢንጂነር ሄኖክ የራማ ኮንስትራክሽን ለማህበረሰቡ የተሻለ እና ምቹ አገልግሎት የሚሰጡ የግንባታ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል። እንደ እሳቸው ከአራዳ ክፍለ ከተማ እስከ ሲኒማ አምፒር ያለውን መንገድ እና በመሃል የሚሰራውን 120 ሜትር ድልድይ ግንባታ እያከናወነ ይገኛል። ድልድዩ ሀገር ውስጥ ብዙም ባልተለመደ እና ወጥ በሆነ መልኩ የሚገነባ በኬብል የሚሰራ ነው። መንገጫገጭ በማይኖረው መልኩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚሰራ ነው። በዚህ ረገድ ከዝናቡ በስተቀር ተግዳሮት አልገጠመም። ከሁሉም ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው ሲሉም በሜጋ ፕሮጀክት በኩል፣ በአማካሪነት በመነጋገር እና በመግባባት 24 ሰዓት እየተሰራ ነው ብለዋል።

እስካሁንም የመሠረት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው እስከ ቀጣይ አራት ወራት ለማጠናቀቅ እየተሰራ መሆኑንም አስታውቀዋል። ድልድዩንና መንገዱን አጠቃሎም ከ300 ሰው በላይ የሥራ እድል መፈጠሩን ገልጸዋል። አቋራጭ መንገዱ ሲጠናቀቅ ከቅድስት ማሪያም እንደ መጣ ወደ ፒያሳ የሚሄደውን መንገድ የሚያሳጥር ነው። ቀደም ሲል ከራስ መኮንን ድልድይ እስከ አምፒር ድረስ የነበረውን የትራፊክ መጨናነቅ ያስቀራል። ቀጥታ ወደ ጣይቱ መንገድ ካስፈለገም በአምፒር በመሄድ የትራፊክ ፍሰቱን የሚያስተካክልና ለማህበረሰቡም የተቀላጠፈ አገልግሎት የሚያሰፋ መሆኑን አመላክተዋል።

# ስፖርት





## መሠረታዊ ለውጥ የሚሻው የስፖርት ዘርፍ

ብርሃን ፈይሳ

በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው 2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ ስፖርት በርካታ ጉዳዮች ተከስተዋል። እነዚህ ክስተቶች የተለያዩ ቢሆኑም፤ አብዛኛዎቹ የሚያመላክቱት ግን የኢትዮጵያ ስፖርት አሁንም ለውጥ የሚያስፈልገው ነው። የየትኛውም ስፖርት ስኬትም ሆነ ውድቀት ጀርባ ታሪክ ቢጠና ሀገር አቀፍ አሠራርና መዋቅር የራሱ ሚና እንዳለው እርግጥ ነው። በመሆኑም ስፖርቱን የሚመራው አካል ከዘመኑ ጋር የሚሄድ እና ሀገርን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያስጠራ በሚችል መልኩ የተቃኘ ስርነቀል የአሠራር ሪፎርም ያስፈልገዋል።



የኢትዮጵያ ስፖርት በዘመናዊ መልኩ ከተደራጀ አንድ ምዕተ ዓመት አስቆጥሯል። ይሁንና አሁንም ድረስ ከወቅቱ ጋር መጓዝ አለመቻሉና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተተገበሩ የሚገኙ ግልጽ የዘመኑ አካሄዶችን መከተል ባለመቻሉ ለውጥ ሳይታይበት ባረጀና ባፈጀ መንገድ መዝለቁን የስፖርት ባለሙያዎች እንዲሁም ሰነዶች ይጠቁማሉ። ሀገራት በስፖርታዊ የውድድር ተሳትፎ ውጤታማ መሆን ባይችሉም ሌሎች ስፖርታዊ ሁነቶችና ስፖርት ነክ ጉዳዮች ላይ አተኩረው በመሥራታቸው ከዘርፉ እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ በማግኘት ኢኮኖሚያቸውን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ። በአንጻሩ የኢትዮጵያ ስፖርት ከ100 ዓመታት በፊት እንደነበረው ዛሬም የመንግሥትን እጅ እየጠበቀ ቀጥሏል።

ስፖርቱ ላለፉት ዓመታት ሲመራበት የቆየው መዋቅራዊ እና አስተዳደራዊ ስልት ለስፖርቱ ውጤታማነት ያበረከተው አስተዋጽኦ እምብዛም ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሀገር አቀፍ የስፖርት ፖሊሲ ተቀርጾ በሥራ ላይ ከዋለ ወደ 27ኛ ዓመት እየተንደረደረ ቢሆንም በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ግን በትክክል ሊተገበርም ሆነ ሊሻሻል አልቻለም። ስፖርቱ በሕዝባዊ እና መንግሥታዊ አካላት የተደራጀና ኃላፊነታቸውንም በግልጽ ያስቀመጠ ቢሆንም የሁለቱም አካላት ሥራ አሁንም ድረስ መደበላለቅና አንዱ የሌላኛው ላይ ጫና ማሳረፉቸው አልቀረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብሄራዊ ቡድን ውስጥ ቀድሞ ይታይ የነበረው ሀገራዊ ስሜት መሸርሸርና የውጤት ቀውስ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከዚሁ ጋር ሊያያዝ የሚል ነው።

በቅርቡ በተካሄደው የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ የተከሰተው ጉዳይ ለዚህ በቂ ማሳያ ይሆናል። በተለይ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ወጥ የሆነ የብሄራዊ ቡድን አሠራር አለመኖር፣ የአትሌቶችና የፌዴሬሽኑ ግንኙነት፣ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ያልተለመደው የአትሌቶች እጅ መስጠት፣ በፌዴሬሽኑ በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እንዲሁም በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር መካከል ያለው ግንኙነት፣ የተጠያቂነት አካሄድ ወዘተ ለውጥ ፈላጊ ጉዳዮች መሆናቸው ታይቷል። ነገር ግን ክስተቱ የእነዚህ አካላት ብቻም ሳይሆን በሌሎች የስፖርት ማህበራትም በተለያየ መጠን መሰል አግባብነት የሌለው ሁኔታ መኖሩን የሚያንጸባርቅ ነው። ይኸውም የኢትዮጵያ ስፖርት ሁለንተናዊ ሪፎርም ግድ እንደሚለው በቂ ማሳያ ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን በመጠቀም ሁሉን አቀፍ የስፖርት ልማት ምዘና በማድረግ እንዲሁም ጥናት ላይ በመመሥረት ሀገራዊ የስፖርት ሪፎርም ሰነድ ተዘጋጅቶ ነበር። ይህንን ተከትሎም በአጠቃላይ መንግሥታዊ የስፖርት አደረጃጀት ላይ ለውጥ ሊያመጣ ያስችላል የሚል አሠራር ተግባራዊ ሊሆን ችሏል። በሥራ ላይ ከዋሉት መካከል አንዱ የሆነው የስፖርት ማህበራት ከመንግሥት በጀት ጠባቂነት ተላቀው ራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ሙከራው በአንጻራዊነት የተሻለ ቢሆንም ውጤታማ ሊያሰኘው በሚል ሁኔታ ላይ ይገኛል ለማለት ግን አያስደፍርም። በሌላ በኩል ስፖርቱን በሚመራው ሕዝባዊ እና መንግሥታዊ አካል መካከል ያለው ግንኙነትና አስተዳደራዊ አቋም አሁንም ድረስ አጠያያቂ በሆነ ሁኔታ መጣረሱን ቀጥሏል።

በታዳጊና ወጣቶች ስፖርት ልማት፣ ዓለም አቀፍ የውድድር ተሳትፎ፣ የስፖርት ማህበራት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ምርጫና የአመራረጥ ሂደት፣ ስፖርቱን በሚመራው መንግሥታዊ አካል ክልሎች እና የስፖርት ማህበራት ኃላፊነት፣ ለአሠራርና አፈጻጸም ምቹ ያልሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች፣ የበጀት እጥረትና ክፍፍል ወዘተ አሁንም ለውጥ ፈላጊ ጉዳዮች ናቸው። ስፖርቱን እንደሚፈለገው ወደፊት እንዳይጓዝ መሰናክል የሆኑ ጉዳዮችን የተዘጋጀው የሪፎርም ሰነድ አመላካች ቢሆንም በቀጥታ ሥራ ላይ አለመዋሉና የተጠያቂነት ሂደቱም ደካማ መሆኑን እንደምክንያት ማንሳት ይቻላል።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ስኬታማ ውጤት እንድታስመዘግብ፣ ታላላቅ የስፖርት ሁነቶችን እንድታዘጋጅ፣ የስፖርት ማህበራት ከመንግሥት እገዛ ተላቀው ራሳቸውን እንዲችሉ፣ ከሀገር አልፎ አህጉር እና ዓለም አቀፍ የስፖርት ማህበራትን የሚመሩ ሥራ አስፈጻሚዎችን እንድታፈራ፣ ኢኮኖሚውን የሚደግፍ ገቢ እንዲመነጭ፣ ለሚከሰቱ የአሠራር ጥሰቶች ተጠያቂነት እንዲሰፍን ወዘተ ዘርፉ መሠረታዊ የሆነ ሪፎርም ያስፈልገዋል። ለዚህም አስፈጻሚው አካል በትኩረት ሊሠራ ይገባዋል።